የወንጀል ሕግ እና ሕገ መንግሥቱ

(ክፍል ሁለት)

አዘጋጅና አቅራቢ
ዩሱፍ ጀማው
ሀምሌ 2000 ዓ/ም

የወንጀል ሕግ እና ሕገ መንግሥቱ

(ክፍል ሁለት)

1. የቅጣት አወሳሰን መሠረታዊ ዓላማዎችና ሕገ መንግስቱ

1.1. የቅጣት መሠረታዊ ዓላማዎችና ግቦች

ወንጀል የሕብረተሰቡን ግንኙነት የሚያዛባ ተግባር ሲሆን ቅጣት ደግሞ ይህን የተዛባ ግነኙነት መልሶ ማስተካከያ መንገድ ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል። ሆኖም አንድ የወንጀል ድርጊት የሚያስከትለው ጉዳት ሁሌም ቢሆን በገንዘብ ሊተመን የሚችል አይደለም። በተጨማሪም የወንጀል ሕጉ ጥበቃ የሚያደርግላቸው አንዳንድ መብቶች በምንም ዓይነት መንገድ ሊካሱ ወይም ወደ ቀድሞ ቦታቸው ሊመለሱ የሚችሉ አይደሉም። በመሆኑም ከፍትሐብሔር ጉዳዮች በተለዩ በወንጀል ምክንያት የሚጣል ቅጣት በመሠረቱ ጉዳቱን የማስተካከያ መፍትሔ ሳይሆን ሌሎች ማህበራዊ ግቦችን በስራ ላይ ለማዋል የምንጠቀምበት መሳሪያ ነው። ማለትም ቅጣት የወንጀል ተጎጂውን መካስን ዓላማ ያደረገ አይደለም።

በአጠቃላይ የቅጣት ዓላማዎች አንድ ሕብረተሰብ በወንጀልና በወንጀለኞች ላይ ያለውን አመለካከት የሚያሳይ እንደሆነ ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን በዚህም መሰረት በተለያዩ አገሮች እና በተለያዩ ጊዜያት በዋናነት ሕብረተሰቡ በወንጀል እና በወንጀለኞች ላያ ያለው አስተሳሰብ ግምት ውስጥ እየገባ የተለያዩ የቅጣት ዓላማዎች ሲቀመጡ ኖረዋል፤ አሁንም እንዲሁ ቅጣት በአንድ አጥፊ ላይ ሲጣል የተለያዩ የቅጣት ዓላማዎች በታሳቢነት ይወሰዳሉ።

በቀድሞው ጊዜ ወንጀል ፈጽሞ የተያዘ ሰው የሚቀጣው የጥፋተኝነቱ መጠንና የፈፀመው ድርጊት አደገኛነት ግምት ውስጥ ገብቶ ሳይሆን በተበዳዩ ላይ ባደረሰው ጉዳት መጠንና ዓይነት ጭምር ነበር። ይህም ዓይን ላጠፋ ዓይን፣ጥርስ ለሰበረ ጥርስ እንዲሁም የገደለ ይሙት የሚል አንድ ሰው ድርጊቱ ባስከተለው ጉዳት መጠንና ዓይነት በእርሱም

ጉዳት እንዲደርስበት የሚደረግበት በብዙ ማህበረሰቦች ዘንድ ሲሰራበት የነበረ የወንጀል ፍትሕ አካሄድ ነበር።[1]

ሆኖም ከሕብረተሰብ የአመለካከት ዕድገትና ስልጣኔ ጋር ተያይዞ ወንጀል በፈፀሙ ሰዎች ላይ ሊወሰድ የሚችለው እርምጃ መጠንና ዓይነት በየጊዜው እየተለወጠ በአሁኑ ወቅት ብቀላን እንደ ዋንኛ የወንጀል ቅጣት ግብ አድርጎ መውሰድ እየቀረ ያለበት ሁኔታ በስፋት የሚስተዋል ጉዳይ ሆኗል። ይህ ማለት ግን ዘመናዊው ሕብረተሰብ የሚከተለው የወንጀል ቅጣት ዓላማ ጉዳት የደረሰበትን ሰው ስነልቦናዊ ፍላጎት ሙሉ በሙሉ ወደ ጎን የተወ ነው ለማለት አይደለም።

በኢትዮጵያ የቅጣት መሠረታዊ ዓላማዎችና ግቦች ምን ምን ናቸው የሚለውን ለመረዳት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ[2] የመጀመሪያውን አንቀጽ ድንጋጌ በጥንቃቄ መመልከት ተገቢ ይሆናል። የድንጋጌው የአማርኛ ቅጂ እንደሚከተለው ይነበባል፦

> "አንቀጽ ፩ .ዓላማና ግብ
>
> የወንጀል ሕግ ዓላማ፣ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፣ የሕዝቦችን፣ የነዋሪዎቹን ሰላም፣ ደህንነት፣ ሥርዓት፣ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።
>
> የወንጀል ሕግ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፅሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው" ይላል።

---

[1] ፋሲል ናሆም (ዶ/ር)፣ ቅጣትና ጎብረተሰብ፤ዕድገታዊ አመለካከት፣የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት፣ቮልዩም 12፣ 1974፣ ገጽ 11

[2] በዚህ ጽሑፍ ውስጥ አዲሱ የወንጀል ሕግ፣ የወንጀል ሕግ፣ አንቀጽ ይህን ያህል ተብሎ ሲጠቀስ በ1996 የወጣውን የወንጀል ሕግ ማለታችን ሲሆን የቀድሞው የወንጀል ሕግ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ፣ ቁጥር ይህን ያህል ተብሎ ሲጠቀስ ደግሞ በ1949 የወጣውን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ማለታችን ነው።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ድንጋጌ ይዘት እንደምንገነዘበው የወንጀል ሕጉ ዓላማ የአገሪቱን መንግስት፣ የሕዝቦቿንና የነዋሪዎቿን ሰላምና ደህንነት እንዲሁም መብትና ጥቅም ማስጠበቅ ሲሆን ይህ የሚደረገውም ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል ነው። የአንደኛው ለምሳሌ የነዋሪዎች ሰላምና ደህንነት እንዲሁም መብትና ጥቅም መጠበቅና መረጋገጥ ለሌኛው ለምሳሌ ለመንግስት የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ሲሆን የአንደኛው ሰላምና ደህንነት አንዲሁም መብትና ጥቅም ሲነካም አንዲሁ የሌላኛው መነካቱ የማይቀር ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ የአንደኛውን ሰላምና ደህንነት እንዲሁም መብትና ጥቅም የሚጠብቀውና የሚያረጋግጠው ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል ነው። ማለትም በወንጀል ሕጉ የሚጠበቁት የአንደኛው የሕብረተሰብ ክፍል መብቶችና ጥቅሞች ከሌሎቹ የህብረተሰብ ክፍሎች መብቶችና ጥቅሞች ጋር የተቆራኙና ሊነጣጠሉ የማይችሉ ናቸው።

የወንጀል ሕጉን ዓላማ ለማሳካት ዋንኛ ግብ ተደርጎ የሚወሰደውም ወንጀል እንዳይፈፀም የመከላከል ተግባር ሲሆን ይህ አቅጣጫ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ከምንም በፊት ሕብረተሰቡ በወንጀልነት የተፈረጁ ድርጊቶችንና የሚያስከትሉትን ቅጣት አስቀድሞ እንዲያውቅ ሲደረግና ከእነዚህ በወንጀልነት ከተፈረጁ ድርጊቶች እንዲርቅ ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ ነው። በመሆኑም የወንጀል ሕጉ የመጀመሪያው ተግባር የተከለከሉ ድርጊቶችን ለይቶ በማመልከት ሕብረተሰቡ ከእነዚህ በሕግ ከተከለከሉ ድርጊቶች እንዲርቅ ማስጠንቀቅ ነው። አንድ ድርጊት ሕገ ወጥ መሆኑና በወንጀል የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ አስቀድሞ እንዲታወቅ ካልተደረገ ወንጀል የሕብረተሰቡን ጥቅም የሚጻረር ድርጊት መሆኑ አጠቃላይ ግንዛቤ ያለ በመሆኑ ይህን ግንዛቤ በመውሰድ ራሳቸውን የሚጠብቁ ሊኖሩ ቢችሉም አንድ ድርጊት ወንጀል ነው አይደለም የሚለው ጉዳይ ለእያንዳንዱ ግለሰብ ውሳኔ የተተወ ስለሚሆን ሰዎች የወንጀል ድርጊቶች ተብለው የተፈረጁትን ጉዳዮች አስቀድመው አውቀው ድርጊቶቹን ከመፈፀም እንዲቆጠቡ አያስችላቸውም።

ሆኖም ወንጀሎችንና የሚያስከትሉትን ቅጣት ዘርዝሮ ማስፈሩ ብቻ ሕበረተሰቡን ከጉዳት አይከላከልም። የተከለከሉ ድርጊቶችና ቅጣታቸው አስቀድሞ እንዲታወቅ ቢደረግም በየትኛውም የሕብረተሰብ ክፍል ውስጥ ክልከላውን ተላልፈው የወንጀል

ድርጊቶችን የሚፈፅሙ ሰዎች ይኖራሉ፡፡ በመሆኑም የወንጀል ሕጉ የሰጠውን ማስጠንቀቂያ በማክበር እንቅስቃሴያቸውን አስተካክለው ከተከለከሉ ድርጊቶች ራሳቸውን ያላራቁ ሰዎች ሲገኙ ተገቢው ቅጣት እንዲጣልባቸው ሊደረግ ወይም በተለያዩ በወንጀል ሕጉ ላይ በተመለከቱ ምክንያቶች ቅጣት ሊወሰንባቸው የማይችል ሲሆን ተጨማሪ ወንጀሎችን እንዳይፈጽሙ አስፈላጊው የጥንቃቄ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ስለዚህ የወንጀል ድርጊት በፈፀሙ ሰዎች ላይ ቅጣት የሚጣለው ከላይ በተጠቀሰው የወንጀል ሕጉ ድንጋጌ ላይ እንደተመለከተው አጥፊዎች ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡ፣ ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ ለማድረግ ነው፡፡

በዚህም መሰረት የወንጀል ሕጋችን የወንጀል ድርጊት በፈፀሙ ሰዎች ላይ ቅጣት እንዲጣል ማድረግን በራሱ ግብ አድርጎ አይወስደውም፡፡ በአጥፊዎች ላይ ቅጣት የሚጣለው በቅጣቱ አማካኝነት በዋናነት ሦስት ዓላማዎችን ለማሳካት ነው፡፡ እነርሱም፡-

1.1.1. <u>መቀጣጫ እንዲሆኑ</u>(Deterrence)

በሕጉ ላይ የተጻፈውን የቅጣት ማስፈራሪያ ችላ በማለት ወንጀል የፈፀመ ሰው ተይዞ በሕጉ ላይ የተመለከተው ቅጣት ሲፈፀምበት በማየት ሌላው ሕብረተሰብ ወንጀል ቢፈፅም በተመሳሳይ በሕይወቱ፣ በነጻነቱ ወይም በንብረቱ ዋጋ የሚከፍልበት መሆኑን እንዲገነዘብ ያደርጋል፡፡ በዚህም መሰረት ወንጀለኛው ለፈፀመው ጥፋት ቅጣት ሲጣልበት ይህ የሚደርስበት ቅጣት ለሌሎች መቀጣጫ ሆኖ መሰል ቅጣት እንዳይደርስባቸው በመፍራት የወንጀል ድርጊቶችን ከመፈፀም ይቆጠባሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይህ የቅጣት ዓላማ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ አንድ ላይ ቅጣት በአጥፊዎች ላይ የሚጣለው "...ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ..." ነው በሚል ተጠቅሶ የምናገኘው ሲሆን ታሳቢ ያደረገውም ወንጀል የፈፀመ ሰው ላይ ቅጣት ሲወሰን ሌሎች ሰዎችም ወንጀል ከፈፀሙ በተመሳሳይ ቅጣት የሚደርስባቸው ስለመሆኑ ትምህርት ያገኛሉ የሚለውን አስተሳሰብ ነው፡፡ ስለዚህም በአንድ ጥፋተኛ ላይ ቅጣት በሚጣልበት ጊዜ በወንጀል ሕጉ የሰፈረውን ይህን ዓላማ ከማሳካት አንጻር መታየት አለበት፡፡

1.1.2. **መከላከል፣ማስወገድ**(Prevention, Incapacitation, Disabling)

ይህ የቅጣት ዓላማ ወንጀለኛው ሁለተኛ ወንጀል ለመፈፀም የሚችልበት ዕድል እንዳይኖረው ወንጀል ለመፈፀም ያስቻሉትን ሁኔታዎች ለማስወገድ እርምጃዎች መውሰድን እንደ አቅጣጫ የተከተለ ሲሆን የሚወሰዱት እርምጃዎች እንደሁኔታው ህብረተሰቡ ውስጥ እንዳይቀላቀል ነጻነቱን ገድቦ ለረጅም ጊዜ ታስሮ እንዲኖር ማድረግ፣ ወይም ጥፋተኛውን በሞት በመቅጣት ጭራሽ ከሕብረተሰቡ እንዲወገድ ማድረግ፣ ወይም ከሙያ ሥራ ጋር በተያያዘ ለሚፈፀሙ ወንጀሎች ከሙያ ሥራው ማባረር ወይም የሥራ ፈቃዱን መንጠቅ የመሳሰሉትን ሁሉ ያካትታል። ይህ የቅጣት ዓላማ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ አንድ ላይ ቅጣት በአጥፊዎች ላይ የሚጣለው "...ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡ..." ነው በሚል ተጠቅሶ የምናገኘው ሲሆን ታሳቢ ያደረገውም አንዳንድ ጊዜ ወንጀለኞች ተመልሰው ወደ ሕብረተሰቡ ከተቀላቀሉ ወይም ከአሁን በፊት ወንጀል ለመፈፀም ያስቻላቸውን ሁኔታ በድጋሚ ዕድል ተሰጥቷቸው ካገኙት ወንጀል መፈፀማቸው ስለማይቀር ሕብረተሰቡን ከወንጀል ሥጋት ለማዳን ወንጀለኞቹ መወገድ አለባቸው ወይም አንደሁኔታው ከአሁን በፊት ወንጀል ለመፈፀም ያስቻላቸውን ሁኔታ መወገድ አለበት የሚል ነው።

1.1.3. **ማረም** (Reformative, Rehabilitative)

ይህ የቅጣት ዓላማ በወንጀለኛው ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን መሠረታዊ አቅጣጫውም በወንጀለኛው ላይ የሚጣለው ቅጣት ወንጀለኛው ወደ ሕብረተሰቡ ተመልሶ በሚቀላቀልበት ጊዜ መሰል ወንጀል እንዳይፈፅም የሚያስተምረውና የጥፋተኛውን የግል ሁኔታ ያገናዘበ መሆን ይገባዋል በሚለው አስተሳሳብ ላይ ነው። በዚህ መሰረት አንድን ወንጀለኛ ወንጀል ለመፈፀም ያነሳሱትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ለፈፀመው ወንጀል የሚጣልበት ቅጣት ወንጀለኛውን አስተካክሎ ወደ ሕብረተሰቡ በመቀላቀል ለሕብረተሰቡን የወንጀል ሥጋት ሳይሆን ጤናማ ሕይወት እንዲመራ የሚያስችለው መሆን አለበት። ይህ የቅጣት ዓላማ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ አንድ ላይ ቅጣት በአጥፊዎች ላይ የሚጣለው "...እንዲታረሙ ለማድረግ..." ነው በሚል ሰፍሮ እናገኘዋለን።

1.2. የወንጀል ቅጣት እና ሕገ መንግሥቱ

1.2.1. ቅጣት የመጣል ሥልጣን ያለው አካል

ከመንግሥት አካላት ውስጥ ድርጊቶችን በወንጀልነት ለመፈረጅ ሕገ መንግስታዊ ሥልጣን ያለው ሕግ አውጭው አካል ነው።[3] እያንዳንዳቸው በወንጀልነት ተፈርጀው በሕግ ተዘርዝረው የተቀመጡት ድርጊቶች የሚያስከትሉት ቅጣት ምን ያህል እንደሆነ የመወሰን ሥልጣን ያለውም እንዲሁ ሕግ አውጭው አካል ነው። ሕግ አውጭው ድርጊቶችን በወንጀልነት ለመፈረጅ የወንጀል ሕጉን ባወጣበት ወቅት በሕብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን ማህበራዊና የግብረ ገብነት እሴቶች ግምት ውስጥ ያስገባል ተብሎ የሚገመት ሲሆን እያንዳንዱ ወንጀል የሚያስቀጣውን የቅጣት መጠን ለመደንገግም እንዲሁ ሕብረተሰቡ ስለወንጀልና ወንጀለኞች ያለውን አመለካከት እንዲሁም በዘመኑ አስተሳሰብ ተቀባይነት ያላቸውን የቅጣት ዓላማዎች ግምት ውስጥ ያስገባል ተብሎ ይታመናል። ሆኖም ሕግ አውጭው ወንጀለኞችን በአካል አስቀርቦ የሚመረምርና የእያንዳንዱን ወንጀለኛ የአደገኛነት ዝንባሌ፣ ያለፈ ሕይወት ታሪክ፣ ወንጀል ለመፈፀም ያነሳሱትን ምክንያቶች፣ወ.ዘ.ተ. ለማረጋግጥ የሚያስችለው ሁኔታ የሌለ በመሆኑ የተወሰኑ መመዘኛዎችን በተለይም እያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት በሕብረተሰቡ ላይ የሚያስከትለውን የአደጋ ወይም የጉዳት መጠን ሚዛን ውስጥ በማስገባት ለተለያዩ ወንጀሎች የተለያዩ ቅጣቶችን ይደነግጋል።

በሌላ በኩል ግን አንድ የወንጀል ድርጊት በሕብረተሰቡ ላይ ያስከትለው የአደጋ ወይም የጉዳት መጠን ተመሳሳይ ቢሆንም አንድ ወንጀለኛ የሚቀጣው የቅጣት መጠን ሊወሰን የሚገባው የወንጀለኛው አደገኛነትና የጥፋተኛነቱ መጠን ግምት ውስጥ ገብቶ መሆን ስላለበት ለአንድ የወንጀል ድርጊት በሕግ አውጭው አማካኝነት የሚደነገገው የቅጣት መጠን አብዛኛውን ጊዜ ቁርጥ ያለ አንድ ቅጣት ሊሆን አይችልም። ስለዚህም ብዙ ጊዜ በሕግ አውጭው የሚደነገገው ቅጣት መነሻና ጣራ ቅጣቱን ወይም አማራጭ ቅጣቶችን የሚያስቀምጥ ይሆናል።

[3] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(5)

የወንጀል አድራጊውን የተለያዩ የግል ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት እና ሕግ አውጭው በሕግ የደነገጋቸውን መስፈርቶች በመጠቀም ለእያንዳንዱ ወንጀለኛ ተገቢውን ቅጣት መወሰን የሚችሉት ፍርድ ቤቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም በመርህ ደረጃ ለእያንዳንዱ በወንጀልነት ለተፈረጀ ድርጊት ቅጣት የመጣል ሥልጣን የሕግ አውጭው አካል ቢሆንም ፍርድ ቤቶች ሕግን ለመተርጎም በተሰጣቸው ሕገ መንግሥታዊ ሥልጣን መሰረት ሕግ አውጭው ያስቀመጣቸውን ገደቦች ሳያልፉ በሕግ የተቀመጡ መመዘኛዎችን በመጠቀም ለእንዳንዱ ወንጀለኛ ተገቢ ወይም ተመጣጣኝ ነው ያሉትን ቅጣት ይወስናሉ (ይፈርዳሉ)፡፡ ስለዚህ በቅጣት አወሳሰን ላይ ሕግ ተርጓሚውም የራሱ የሆነ ሚና አለው ማለት ነው፡፡

ሦስተኛው የመንግሥት አካል ተደርጎ የሚወሰደው የሕግ አስፈጻሚው አካልም እንዲሁ በቅጣት አወሳሰን ዙሪያ የራሱ ሚና አለው፡፡ ይህ ሚናው በተለይም ጥፋተኛው አመክሮ እንዲሰጠው በማድረጉ ሂደት ላይ ባለው ተሳትፎ እና ይቅርታ ለመስጠት ባለው ሥልጣን ዙሪያ የሚታይ ነው፡፡ አንድ በእስራት እንዲቀጣ የተፈረደበት ወንጀለኛ የተፈረደበት የእስራት ጊዜ ሳይጠናቀቅ ከእስር እንዲለቀቅ የሚወሰነው በፍርድ ቤት ቢሆንም ጥፋተኛው እስረኛ ሆኖ በቆየበት ወቅት ያሳየውን መልካም ጠባይ መሠረት በማድረግ ማረሚያ ቤቱ የሰጠው አስተያየት የውሳኔው ዋንኛ መሰረት ነው፡፡

እንዲሁም ሕግ አውጭው ያወጣውን ሕግ መሰረት በማድረግ ሕግ ተርጓሚው የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ ሕግ አስፈጻሚው አካል በሚሰጠው ይቅርታ ሙሉ በሙሉ ቀሪ ማድረግ፣ መጠኑን መቀነስ ወይም መለወጥ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩ ሕግ አውጭው አካል በቅጣት አወሳሰን ዙሪያ ያለውን መጠነኛ ሚና ያሳያል፡፡

1.2.2. <u>የወንጀል ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራ መሆኑ</u>

በሕግ በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር ለአንድ ወንጀል በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ከተደነገገው የቅጣት ወለልና ጣራ ውጭ ቅጣት ሊጣል አይችልም፡፡ እንዲሁም ለአንድ የወንጀል ድርጊት ሊጣል የሚችለው ቅጣት የሚወሰነው ወንጀሉ ከተፈፀመበት

ወቅት አስቀድሞ በተደነገገ የወንጀል ድንጋጌ በተመለከተው መሠረት ነው። ከዚህ አኳያ በአገራቱ የሕጎች ሁሉ የበላይ ሕግ የሆነው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 22 "ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙ ወይም አለመፈፀሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም። እንዲሁም ወንጀሉን በፈፀመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈጻሚ ከነበረው የቅጣት ጣራ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛውም ሰው ላይ አይወሰንም" ይላል። ይህ ድንጋጌ ሁለት ዓይነት መሠረታዊ ውጤቶችን ያስከትላል። እነዚህም አንድ ድርጊት በሚፈፀምበት ወቅት ድርጊቱ በጊዜው የማያስቀጣ ከነበረ ይኸው አስቀድሞ የተፈፀመው ድርጊት ከጊዜ በኋላ በወጣ ሕግ ወንጀል ነው ሊባል አይችልም። በተጨማሪም ድርጊቱ በተፈፀመበት ወቅት ወንጀል ቢሆንም እንኳ ወንጀለኛው መቀጣት ያለበት ድርጊቱ በሚፈፀምበት ወቅት ተፈጻሚነት የነበረው የወንጀል ሕግ በደነገገው የቅጣት ጣራ መሠረት መሆን አለበት። ስለዚህም ከድርጊቱ በኋላ የወጣ ሕግ የቅጣት ጣራውን ከፍ ቢያደርገው ይህ ቅጣት ሕጉ ከመታወጁ በፊት ለተፈፀመ ወንጀል ተፈጻሚ መሆን የለበትም።

አንድ የወንጀል ድርጊት ከተፈፀመ በኋላ የሚወጡ የወንጀል ድንጋጌዎች ለዚያ ዓይነት ወንጀሎች ቀደም ሲል ተደንግጎ የነበረውን ቅጣት በተለያዩ መንገድ ሊያከብዱት ይችላሉ። ይኸውም ድርጊቱ ቀደም ሲልም ሆነ አሁን ወንጀል ቢሆንም ከድርጊቱ በኋላ የወጣው የወንጀል ድንጋጌ የቅጣቱን ከፍተኛ ጣራ በማሳደግ፣ ወይም የቅጣቱን ዝቅተኛ ወለል ከፍ በማድረግ ወይም በአማራጭ ተቀምጠው የነበሩ የቅጣት ዓይነቶችን በማጣመር የወንጀል ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ ሕጉ ላይ ተመልክቶ የነበረውን ቅጣት አክብዶት ሊሆን ይችላል። ሆኖም በየትኛውም መንገድ ቅጣቱ እንዲከብድ የተደረገበት ሁኔታ ቢኖር ድርጊቱ በተፈፀመበት ወቅት ከተቀመጠው የቅጣት መጠን ውጭ በወንጀለኛው ላይ ቅጣት ሊወሰንበት አይችልም።

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 22 ድንጋጌ መሠረት አስቀድሞ ወንጀል መሆኑ ባልተደነገገ ድርጊት ማንኛውም ሰው ሊቀጣ አይችልም፤ እንዲሁም ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ከነበረው የቅጣት ጣራ በላይ ሊቀጣ አይችልም። ይህ ሕገ መንግሥታዊ መርሕ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 5 ላይም ተካትቶ

እናገኘዋለን፡፡ ከዚህም አንጻር የአዲሱ የወንጀል ሕግ ተፈጻሚነት ሕጉ ሥራ ላይ ከዋለበት ከግንቦት 01 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ለተፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶች ነው ማለት ነው፡፡

በዚህም መሰረት አንድ ድርጊት በአዲሱ የወንጀል ሕግ ወንጀል ነው ቢባልም በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ግን በወንጀልነት ያልተፈረጀ ድርጊት የነበረ ከሆነ ድርጊቱ የተፈፀመው ከግንቦት 01 ቀን 1997 ዓ.ም በፊት ከሆነ በወንጀል ሊያስጠይቅ አይችልም፡፡ እንዲሁም ድርጊቱ በቀድሞውም ሆነ በአዲሱ የወንጀል ሕግ ወንጀል ስለመሆኑ የተደነገገ ቢሆንም እንኳን ወንጀለኛው መቀጣት ያለበት ድርጊቱ በተፈፀመበት ወቅት ተፈጻሚነት የነበረው የወንጀል ሕግ በደነገገው የቅጣት ጣራ እና የቅጣት ወለል መሰረት መሆን አለበት፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ማለትም አንድ የወንጀል ሕግ ከመውጣቱ በፊት ለተፈፀመ ድርጊት ተፈጻሚነት የለውም የሚለው አጠቃላይ መርሕ ቢኖርም በተለዩ በሕግ በተፈቀዱ ልዩ ሁኔታዎች (exceptions) ግን የወንጀል ሕጉ ወደ ኋላ ተመልሶ ሊሰራ ይችላል፡፡ እነርሱም፡-

1. አዲሱ የወንጀል ሕግ ከቀድሞው ሕግ ይልቅ ለተከሳሹ ቅጣትን የሚያቃልልለት በሚሆንበት ጊዜ ተከሳሹ ወንጀሉን በፈፀመበት ወቅት ሥራ ላይ ያልነበረ ሕግ ቢሆንም ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

2. አዲሱ የወንጀል ሕግ ከወጣ በኋላ በቀድሞው ሕግ መሰረት ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚወሰኑት የቀድሞውን ሕግ መሰረት በማድረግ ሳይሆን በአዲሱ ሕግ መሰረት ነው፡፡ ማለትም የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመው የቀድሞው ሕግ ሥራ ላይ በነበረነት ጊዜ ቢሆንም ውሳኔው የተሰጠው አዲሱ የወንጀል ሕግ ወጥቶ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚወሰኑት በአዲሱ የወንጀል ሕግ መሠረት ይሆናል ማለት ነው፡፡

3. የቀድሞው ሕግ ሥራ ላይ በነበረበት ወቅት ለተፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶች የወንጀል ክስ የማቅረብና እና ቅጣት ቀሪ የመሆን የይርጋ ጊዜ የሚታሰበው (የሚሰላው) አዲሱ የወንጀል ሕግ በሚደነግገው መሠረት ነው።

4. በቀድሞው ሕግ መሠረት የተሰጡ ፍርዶች የሚፈፀሙት በአዲሱ የወንጀል ሕግ መሠረት ነው።

5. የቀድሞው ሕግ ሥራ ላይ በነበረበት ጊዜ ለተፈፀመ ወንጀል የሚሰጥ አስቀድሞ በገደብ ወንጀለኛን መልቀቅና በአመክሮ ከእስር መፍታት ውሳኔ የሚወሰነው አዲሱ የወንጀል ሕግ ያስቀመጣቸውን መመዘኛዎች በመጠቀም ነው። እንዲሁም

6. በቀድሞው ሕግ መሠረት የተፈረደባቸው ሰዎች የወንጀል ሪከርዳቸው የሚሰረዘውና የሚሰየሙት አዲሱ የወንጀል ሕግ ያስቀመጣቸውን መመዘኛዎች በመጠቀም ነው።

1.2.3. <u>ለአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ</u>

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 23 ላይ "ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግና ሥነ ሥርዓት መሠረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነጻ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም" በማለት ተደንግጓል። በአዲሱ የወንጀል ሕግም እንዲሁ በተመሳሳይ አንድ ሰው በአንድ ወንጀል ሁለት ጊዜ ሊከሰስም ሆነ ሊቀጣ እንደማይችል ተመልክቷል።

አንድ ወንጀል ከአንድ ጊዜ በላይ እንደማያስቀጣ በሕገ መንግሥቱም ሆነ በመሠረታዊ የወንጀል ሕጉ ውስጥ እንዲደነገግ ያስፈለገበት በቂ ምክንያት አለ። በአንድ የወንጀል ሕግ ውስጥ እያንዳንዱ ወንጀል ምን ዓይነት ቅጣት እንደሚያስከትል በዝርዝር የተደነገገ በመሆኑ አንዱ ለተፈፀመ ወንጀል የተለያዩ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ሕግ አውጪው በቂ ወይም ተመጣጣኝ ነው ብሎ የገመተውን ቅጣት በግልፅ

አስቀምጣል። ስለዚህም አንድ ወንጀለኛ በአንድ ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ቅጣት ተወስኖበትና ቅጣቱንም ፈፅሞ እያለ ያንኑ ሰው ለዚያው ወንጀል መልሶ መክሰሱ ወይም መቅጣቱ በሕብረተሰቡ ኑሮ ላይ ከፍ ያለ ቀውስን መጋበዝ ይሆናል። በዚህም መሰረት በአንድ ወንጀል ተከሰው ቅጣታቸውን የጨረሱ ወይም ተከሰው ነፃ የወጡ በዚያው ጉዳይ እንደገና ይከሰሱ ቢባል የወደፊት ኑሯቸውን ያለ ሥጋት መምራት አይችሉም። ይህ ከሆነ ደግሞ መሠረታዊ የሰው ልጆች መብቶች መጣሱ ስለማይቀር መርሁን በሕገ መንግሥቱና በመሠረታዊ የወንጀል ሕጉ ላይ መደንገጉ የዜጎችን መብት ለማስጠበቅ ይረዳል። ዜጎችም በሕጉና በሥርዓቱ ላይ አመኔታ እንዲኖራቸው ያደርጋል።[4]

2. ቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች

2.1. የወንጀል ቅጣቶች

ቅጣቶች በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ተለይተው ሊታዩ ይችላሉ፣

1/ ዋና ቅጣቶች፣ እና 2/ ተጨማሪ ቅጣቶች

2.1.1. ዋና ቅጣቶች

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው ሊጣሉበት የሚችሉ ዋና ቅጣቶች የሚባሉት መቀጮ፣ የማዬታ ሥራ ፣የእስራት ቅጣት እና የሞት ቅጣት ናቸው።

2.1.1.1. መቀጮ

መቀጮ ወይም የገንዘብ ቅጣት የወንጀል አድራጊውን የገንዘብ ወይም የንብረት ባለቤትነት መብት የሚነካ በፍትሐብሔር ጉዳይ ካለው ኃላፊነት ጋር የሚቀራረብ ቅጣት ነው። መቀጮ የሚከፈለው በጥሬ ገንዘብ ሲሆን ገቢ የሚደረገውም ለመንግሥት ነው። የገንዘብ ቅጣት በወንጀል የደረሰ ጉዳትን የማስተካከል ዓላማ የለውም፣ መጠኑም የሚለካው ከደረሰው ጉዳት አንጻር አይደለም። የሚለካው ከተፈፀመው ወንጀል ከባድነትና ከተቀጭው የመክፈል አቅም አንጻር ነው።

[4] የወንጀል ሕግ መሠረታዊ መርሆች፣ፀሐይ ወዳ፣ 1994፣ገጽ 29-30

መቀጮ ለብቻው ወይም ከሌሎች ቅጣቶች ጋር ሊወሰን ይችላል። ብዙውን ጊዜ ሕጉ መቀጮን ከቀላል እስራት ጋር በአማራጭ የሚደነግግ ሲሆን በሕጉ ልዩ ክፍል የሚገኙ አንቀጾች በግልፅ ባይደነግጉም መቀጮ የእስራት አማራጭ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ሁሉ ፍርድ ቤቱ አስፈላጊነቱን ካመነበት ሁለቱንም ዓይነት ቅጣት አጣምሮ መወሰን ይችላል (አንቀጽ 91)። አንዳንድ ጊዜ የመቀጮው ቅጣት የታች ወይም የላይ ወሰን በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል አንቀጾች ሊገለፅ የሚችል ሲሆን አንዳንድ ጊዜም የቅጣቱ ወሰን ሳይገለፅ ቅጣቱ መቀጮ መሆኑ ብቻ ይጠቀሳል። እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት የመቀጮ ቅጣቱ መነሻ አንድ ብር የላይ ጣራው ደግሞ አምስት ሺህ ብር ነበር (ቁጥር 88)።

በአዲሱ የወንጀል ሕግ መሠረት ግን ጥፋተኛው ግለሰብ ሲሆን እና የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ሲሆን መቀጮው የተለያየ እንዲሆን ተደርጓል። በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 34 መሠረት በሕግ የሰውነት መብት ያላቸው ድርጅቶች (የመንግስት አስተዳዳር አካላትን ሳይጨምር) ወንጀል ፈፅመው በተገኙ ጊዜ በወንጀል ይጠየቃሉ። ነገር ግን እነዚህ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች የሚጣልባቸው ቅጣት በተፈጥሮ ሰው ላይ ከሚጣለው ቅጣት በተለዬ በመቀጮ ብቻ ነው።

በዚህም መሰረት ጥፋተኛው ግለሰብ ከሆነ ከአስር ብር እስከ አስር ሺህ ብር ሊቀጣ የሚችል ሲሆን፣ ጥፋተኛው የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ሲሆን ደግሞ የሚወሰንበት የገንዘብ ቅጣት ከአንድ መቶ ብር አስከ አምስት መቶ ሺህ ብር ሊደርስ እንደሚችል ተመልክቷል።

የወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል የእስራትን ቅጣት አስቀምጦ መቀጮን በአማራጭ በሚደነግግበትና ተቀጪው የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ እስራት ወደ መቀጮ የሚለወጥበትን ሁኔታ የሚያመለክት አዲስ ድንጋጌም ተጨምሯል (አንቀጽ 90(3))። በዚህ መሠረት እስከ አምስት ዓመት ቀላል እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ አስር ሺህ ብር፣ እስከ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ሃያ ሺህ ብር፣ ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ሃምሳ

ሺህ ብር፣ ከአስር ዓመት በላይ ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል በሕግ የሰውነት በተሰጠው ድርጅት ላይ የሚወሰነው የገንዘብ ቅጣት እስከ አምስት መቶ ሺህ ብር እንዲሆን ተደርጓል፡፡

እንዲሁም ወንጀልን በሚያቋቁመው የወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ውስጥ መቀጮ ብቻ በተደነገገ ጊዜ እና ተቀጪው የሕግ ሰውነት ያለው አካል በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ የቅጣቱን መጠን የሚወስነው ለተፈጥሮው ሰው ከተቀመጠው ቅጣት አምስት እጥፍ በማድረግ ስለመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ ተደንግጓል፡፡

የተፈጥሮ ሰውን በተመለከተ ወንጀሉ የተፈፀመው በአፍቅሮ ንዋይ የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ እስከ 10 ሺህ ብር ሊደርስ ይችላል ተብሎ በቀድሞው ሕግ ላይ ተደንግጎ የነበረው (ቁጥር 90) በአዲሱ የወንጀል ሕግ ቅጣቱ እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር ሊደርስ ይችላል ተብሎ ተሻሽሏል (አንቀጽ 92)፡፡

በመሠረቱ የገንዘብ ቅጣት ወዲያውኑ መከፈል ይኖርበታል፡፡ ተቀጭው ገንዘቡን ወዲያው መክፈል ባይችል በቀድሞው ሕግ ከአንድ አስከ ሦስት ወር የመክፈያ ጊዜ ሊፈቀድለት ይችል የነበረ ሲሆን (ቁጥር 91(1))፣ በአዲሱ የወንጀል ሕግ የመቀጮው የመክፈያ ጣራ ወደ ስድስት ወር ከፍ እንዲል ተደርጓል(አንቀጽ 93(2))፡፡ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ተቀጭው መቀጮውን በየጊዜው እየከፈለ እንዲጨርስ ፍርድ ቤቱ በቀድሞው ሕግ ከሁለት ዓመት ላልበለጠ የመክፈያ ጊዜ ሊሰጠው ይችል የነበረ ሲሆን(ቁጥር 91(1))፣ በአዲሱ የወንጀል ሕግ ይህ ለተቀጪው የሚሰጠው የመክፈያ ጊዜ ወደ ሶስት ዓመት ከፍ እንዲል ተደርጓል (አንቀጽ 93(2))፡፡

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ አንድ ጥፋተኛ የተወሰነበትን መቀጮ መክፈል ካልቻለ ወደ እስራት እንደሚለወጥ ይደነግግ የነበረው /ቁጥር 94/ ተሠርዟል፡፡ ለመሠረዙ በምክንያትነት የተሰጠው ድህውን ወገን የሚጐዳ የቅጣት አፈፃፀም በመሆኑ ፍትሐዊ አይደለም የሚል ነው፡፡[5]

[5] የወንጀል ሕግ ሐተታ ዘምክንያት፣መስከረም 1998፣ገጽ 56(ያልታተመ)

2.1.1.2. <u>የግዴታ ሥራ</u>

የግዴታ ሥራ በወንጀል ጥፋተኛ የተባለ ሰው ሰርቶ የሚያገኘውን ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ የሚያደርግበትን ሁኔታ የሚመለከት ሲሆን ጥፋተኛው የፈፀመው ወንጀል የሚያስከትለው ቅጣት ከስድስት ወር የማይበልጥ ቀላል እስራት የሆነ እንደሆነና ጥፋተኛውም ለህብረተሰቡ አደገኛነት የሌለው መሆኑ ከታመነበት ፍርድ ቤቱ በእስራቱ ምትክ ከአንድ ቀን እስከ ስድስት ወር ለሚደርስ ጊዜ ወንጀለኛው የግዴታ ሥራ እንዲሰራ ለመወሰን ይችላል (አንቀጽ 103)።[6] በዚህም መሠረት እስራት ወደ ግዴታ ሥራ እንዲለወጥለት አንድ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው በይገባኛል የሚጠይቀው ጉዳይ ሳይሆን ፍርድ ቤቱ በሕግ የተቀመጠውን መመዘኛ ግምት ውስጥ በማስገባት እንደ አግባብነቱ እስራቱ ወደ ግዴታ ሥራ እንዲለወጥ ወይም እስራቱ እንዲፈፀም የሚያደርግበት ነው።

የግዴታ ሥራ የነገሩ ሁኔታን ግምት ውስጥ በማስገባት የተቀጪውን ነጻነት ከመገደብ ጋር እንዲፈፀም ፍርድ ቤቱ ሊወስን የሚችል ሲሆን በተለይም ደግሞ ተቀጪው ነጻነቱ ሳይገደብ የግዴታ ስራ እንዲሰራ ቅጣት ተወስኖበት ይህን የተወሰነበትን ቅጣት በአግባቡ ሳይወጣ ከቀረ ተቀጪው ከአንድ የስራ ቦታ፣ ከአንድ አሰሪ ዘንድ፣ ከአንድ የስራ ተቋም ሳይለቅ ወይም ከመኖሪያ ሥፍራው ሳይወጣ ወይም በመንግሥት ባለሥልጣኖች ከሚጠበቅ ከአንድ የተወሰነ ሥፍራ ሳይለይ የግዴታ ሥራውን እንዲያከናውን ፍርድ ቤቱ ሊያደርግ ይችላል።

በእስራት ምትክ በግዴታ ሥራ ጥፋተኛው እንዲቀጣ በፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ ከተቀጪው ገቢ ላይ እየተቀነሰ ለመንግሥት ገቢ የሚሆነውን የገንዘብ ልክ፣ የግዴታ ሥራው የሚፈፀምበትን ሥፍራ፣ ቅጣቱ የሚቆይበትን ጊዜ እንዲሁም በተቀጪው ላይ የሚደረገውን የቁጥጥር ዓይነት ማመልከት ያለበት ሲሆን ለመንግስት ገቢ እንዲሆን የሚወሰነው መጠን ከተቀጪው የድካም ዋጋ ወይም በሥራ ፍሬው

[6] የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 102 ወደ ግዴታ ሥራ እንዲለወጥ የሚፈቅደው የተፈፀመው ወንጀል የሚያስከትለው ቅጣት ከሦስት ወር ቀላል እስራት የማይበልጥ ከሆነ የነበረ የግዴታ ሥራው ሊቆይ የሚችልበት የጊዜ እርዝማኔም እንዲሁ ከሦስት ወር ሊበልጥ አይችልም ነበር።

ከሚያገኘው ጥቅም ከአንድ ሦስተኛ መብለጥ አይችልም። የቀድሞው ሕግ የሚከለክለው ተቀናሽ እተደረገ ለመንግስት ገቢ የሚሆነው መጠን ተቀጪው በሚሰራው ሥራ ከሚያገኘው ገቢ ከአንድ አራተኛ እንዳይበልጥ ነበር (ቁጥር 102(2))።

በእስራት ምትክ በግዴታ ሥራ እንዲቀጣ የተወሰነበት ወንጀለኛ በፍርድ ቤቱ የተጣለበትን ውሳኔ የጣሰ ወይም በውሳኔው መሠረት ለመፈፀም ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ ሳይፈፀም የቀረው የግዴታ ሥራ ወደ ቀላል እስራት ተለውጦ ቅጣቱን እንዲፈፅም ይደረጋል (አንቀጽ 104(2))። ይህም ማለት ለምሳሌ ከተወሰነበት የግዴታ ሥራ ዘመን ውስጥ ግማሹን በትክክል ፈፅሞ ከሆነ ይኸው ተይዞለት ላልፈፀመው የግዴታ ሥራ ዘመን ብቻ የቀላል እስራት ቅጣት ይጣልበታል ማለት ነው።

በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 96 ድንጋጌ መሠረት አንድ ጥፋተኛ የተወሰነበትን መቀጮ መክፈል ካልቻለ ወደ እስራት የሚለወጥ ሲሆን ነገር ግን ጥፋቱ ቀላል ከሆነ የግዴታ ሥራ እንዲሠራ ሊወሰንበት ይችላል። በአዲሱ የወንጀል ሕግ መሠረት ግን ጥፋቱ ቀላልም ይሁን ከበድ ያለ፣ የመቀጮው መጠን አነስተኛም ይሁን ከፍ ያለ የተወሰነበትን መቀጮ መክፈል ያቃተው ሰው የግዴታ ሥራ ሊፈረድበት ይችላል። ፍርድ ቤቱ ተቀጭው ለምን ያህል ጊዜ የግዴታ ሥራውን ሊሠራ እንደሚባው መግለፅ ያለበት ሲሆን የሚወሰነው ጊዜ በአዲሱ ሕግ መሰረት ከሁለት ዓመት ሊበልጥ አይችልም። በቀድሞው ሕግ ግን እንዲህ ዓይነት ገደብ አልተቀመጠም ነበር። በአዲሱ የወንጀል ሕግ ላይ የጊዜ ገደብ እንዲቀመጥ የተደረገው የጥፋተኛው ጉልበት ወይም አዕምሮ ለረጅም ጊዜ ያለአግባብ እንዳይበዘበዝ ለማድረግ እንዲሁም የተለያዩ የገንዘብ ማግኘት አቅም ባላቸው ሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት የተቻለውን ያህል ለመቅረፍ ታቅዶ ስለመሆኑ ተመልክቷል።[7]

2.1.1.3. <u>የእስራት ቅጣት</u>

እስራት በሦስት ይከፈላል። እነርሱም ፅኑ እስራት፣ ቀላል እስራት እና የማረፊያ ቤት እስራት ናቸው። የማረፊያ ቤት እስራት ደንብ ተላልፈው የተገኙ ሰዎች

[7] የወንጀል ሕግ ሐተታ ዘምክንያት፣ መስከረም 1998፣ ገጽ 56(ያልታተመ)

ሊጣልባቸው የሚችለው ዓይነት እስራት ነው። ይህ የእስራት ዓይነት በማረሚያ ቤት ሊፈፀም የማይችል ሲሆን ጠቅላላ አፈጻፀሙም ወንጀል ፈፅመው በእስራት እንዲቀጡ ከተፈረደባቸው ሰዎች የቅጣት አፈጻጸም የተለዬ ነው። ቀጥለን የምናያቸው ወንጀል አድራጊዎች መደበኛውን የወንጀል ሕግ ድንጋጌ ጥሰው በመገኘታቸው ምክንያት እንደ አግባብነቱ ሊወሰኑ የሚችሉትን ቀላል ወይም የፅኑ እስራት ቅጣቶች ይሆናል።

(ሀ) <u>ቀላል እስራት</u>

ከባድነታቸው መካከለኛ ለሆኑ ወንጀሎችና ለሕብረተሰቡ አደገኛ ላልሆኑ ወንጀሎች የተደነገገ የቅጣት ዓይነት ነው። የወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል የላይ እስራቱን የታች ወይም የላይ ወሰን በግልፅ የሚደነግግበት ጊዜ ያለ ሲሆን ይህ የማይሆንበት ሁኔታም አለ። አንዳንድ ጊዜ የቀላል እስራት ቅጣቱ የታች ወይም የላይ ወሰን በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል አንቀጾች ሊገለፅ የሚችል ሲሆን አንዳንድ ጊዜም የቅጣቱ ወሰን ሳይገለፅ ቅጣቱ ቀላል እስራት መሆኑ ብቻ ይጠቀሳል። እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግም ሆነ በአዲሱ የወንጀል ሕግ የቀላል እስራት ቅጣቱ መነሻ አስር ቀን የላይ ጣራው ደግሞ እስከ ሦስት ዓመት ይደርሳል። ምንም እንኳን በመርህ ደረጃ የቀላል እስራት ጊዜ ከአስር ቀን እስከ ሦስት ዓመት ቢሆነም በተለዩ ምክንያቶች የቀላል እስራት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ እንደሚችል ተመልክቷል(አንቀጽ 106(1))። እነዚህም ምክንያቶች፡-

1. ከወንጀሉ ከባድነት የተነሳ በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ተደንግጐ ሲገኝ ቀላል እስራት ከሶስት ዓመት ገደብ አልፎ እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል። ለምሳሌ አንቀጽ 541ን ብንመለከት የአስገዳጅ ሁኔታን ወሰን በመተላለፍ ወይም ህጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ አንድ ሰው “ቀላል የሆነ የሰው ግድያ” የፈፀመ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እንደሚቀጣ ተደንግጓል ።

በቀድሞው ሕግም ቢሆን የግልፅነት ችግር ቢኖረውም “በሕጉ የተለዬ ድንጋጌ ከሌለ በቀር” የቀላል አስራት ቅጣት ከአስር ቀን እስከ ሦስት ዓመት እንደሚደርስ

ተመልክቶ ነበር (ቁጥር 105)፡፡ ይህም የሚያሳየው ሕጉ በተለዬ በሚደነግግበት ጊዜ የቀላል እስራት ቅጣት ከሦስት ዓመት አይበልጥም በሚለው በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል ለእስራቱ ዓይነት በተደነገገው የቀላል እስራት የላይ ጣራ የማይገደብ መሆኑን ነው፡፡

2. በቀላል እስራት የሚያሰቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈፅመው ሲገኙ የቀላል እስራት ቅጣት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ ይችላል፡፡ አንድ ሰው ሁለትና ከዚያ በላይ በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎችን ፈጽሞ ሲገኝ ፍርድ ቤቱ ለተፈፀሙት ወንጀሎች ለእያንዳንዳቸው ተገቢ ነው የሚለውን የእስራት ቅጣት ይወስንና ሁሉም እንዲደመሩ በማድረግ ጥፋተኛው ሊፈፅም የሚገባውን አጠቃላይ የቀላል እስራት ዘመን ያስቀምጣል፡፡ በዚህ ሂደት ፍርድ ቤቱ የሚወስነው የቀላል እስራት ቅጣት የቀላል እስራት ዘመን ከሦስት ዓመት አይበልጥም በሚለው ለእስራቱ ዓይነት በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል በተቀመጠው ጣራ አይገደብም፡፡ በመሆኑም ይህን የቀላል እስራት የቅጣት የመጨረሻ ጣራ በማለፍ መወሰን ይችላል፡፡ ነገር ግን ድምሩ ከአምስት ዓመት ማለፍ አይችልም፡፡ የእስራቱን ዘመን ማርዘም እንዲቻል በማሰብም ቅጣቱን ከቀላል እስራት ወደ ፅኑ እስራት ፍርድ ቤቱ ሊቀይር አይችልም፡፡

3. በቀላል አስራት በሚያስቀጡ ወንጀሎች በተደጋጋሚ ሲቀጣየቀላል እስራት ቅጣት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ ይችላል፡፡ እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነጥብ በተደጋጋሚ ሲቀጣ ማለት ጥፋተኛው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ሲሆን ማለት አይደለም፡፡ አንድ ሰው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ነው ለማለት በቀድሞውም ሆነ በአዲሱ የወንጀል ሕግ ላይ ተሟልተው መገኘት ያለባቸው መስፈርቶች የተቀመጡ ሲሆን (መስፈርቶችን በሌላ ክፍል እናያቸዋለን) እነዚህ መስፈርቶች ተሟልተው ካልተገኙ ግለሰቡ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ሊባል ባይችልም ሁለት ሦስት ጊዜ ተቀጥቶ ከሆነ በተደጋጋሚ የተቀጣ ነው ሊባልና በልዩ ሁኔታም ባይሆን በመደበኛው ዓይነት ቅጣቱ ሊከብድበት ግን ይችላል፡፡ በተደጋጋሚ የተቀጣ የሚለው አገላለፅ በእራሱ ግን ደጋጋሚ ወንጀለኛን ጭምርም የሚሸፈን ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

ከቀላል እስራት ጋር በተያያዘ ሌላው ሊነሳ የሚገባው ነጥብ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ እስከ ሦስት ወር የሚደርስ የቀላል እስራት ቅጣት በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች ላይ ተመልክቶ በሚያጋጥምበት ጊዜ ሁሉ በቀላል እስራቱ ምትክ ፍርድ ቤቱ የግዴታ ሥራን መወሰን እንደሚችል ተመልክቶ የነበረ ሲሆን (ቁጥር 106) በአዲሱ የወንጀል ሕግ እስከ ስድስት ወር የሚደርስ የቀላል እስራት ቅጣት በግዴታ ሥራ ሊተካ እንደሚችል ተመልክቷል (አንቀጽ 107)።

(ለ) <u>ፅኑ እሥራት</u>

ፅኑ እስራት ለከባድ ወንጀሎችና ለሕብረተሰቡ አደገኛ በሆኑ ወንጀለኞች ላይ የሚወሰን የቅጣት ዓይነት ነው። የወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል የእስራቱን ጣራ ወይም የእስራቱን የታች ወለል ወይም ሁለቱንም በግልፅ የሚደነግግበት ጊዜ ያለ ሲሆን ይህ የማይሆንበት ሁኔታም አለ። አንዳንድ ጊዜ የፅኑ እስራት ቅጣቱ የታች ወይም የላይ ወሰን በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል አንቀጾች ሊገለፅ የሚችል ሲሆን አንዳንድ ጊዜም የቅጣቱ ወሰን ሳይገለፅ ቅጣቱ የፅኑ እስራት መሆኑ ብቻ ይጠቀሳል። እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግም ሆነ በአዲሱ የወንጀል ሕግ የፅኑ እስራት ቅጣቱ መነሻ አንድ ዓመት የላይ ጣራው ደግሞ እስከ ሀያ አምስት ዓመት ይደርሳል። ሆኖም በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል በግልፅ ተደንግጎ በተገኘ ጊዜ የፅኑ እስራት ዘመን እስከ ወንጀለኛው የዕድሜ ፍፃሜ ድረስ ሊቀጥል ይችላል። የዕድሜ ልክ እስራት ርዝመቱ አይታወቅም። እስረኛው በአመክሮ ካልተለቀቀ በቀር አርባ ወይም ሀምሳ አመት ታስሮ ሊቆይ የሚችለበት ሁኔታ ይኖራል።

በፅኑ እስራት የተቀጣ ወንጀለኛ አደገኛ ነው ተብሎ ስለሚገመት እስራቱ በተለይ በመጨቆንና በመጠበቅ ይፈፀማል በማለት የቀድሞው ሕግ ይደግግ የነበረ ሲሆን (ቁጥር 107(1)) አዲሱ ሕግ ደግሞ የፅኑ አስራት ቅጣት የአፈፃፀም ሁኔታ ከቀላል እስራት የአፈፃፀም ሁኔታ በይበልጥ ይከብዳል በማለት ደንግጓል (አንቀጽ 108(2))። በዚህም መሠረት በቀላል እስራት የተቀጣ ሰው በፅኑ እስራት ከተቀጣ ወንጀለኛ የተሻለ

የመንቀሳቀስና ሌሎች መብቶች ባለበት ሁኔታ የተፈረደበትን እስራት እንዲፈፅም ይደረጋል ወይም ሊደረግ ይገባል፡፡

በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ላይ ቀላል እስራት የሚፈፀመው በእስር ቤቶች፣ ፅኑ እስራት የሚፈፀመው ደግሞ በወህኒ ቤቶች ስለመሆኑ ተመልክቶ የሚገኝ ሲሆን (ቁጥር 105(2) እና ቁጥር 107(2))፤ አዲሱ ሕግ ደግሞ እስረኞቹ በተለያዩ ሥፍራ መታሰር ያለባቸው መሆኑና በእስራቱ አፈጻጸም ላይ ልዩነት ያለ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ቀላልም ሆነ ፅኑ እስራት የተወሰነባቸው ወንጀለኞች ቅጣታቸውን የሚፈፅሙት ለዚሁ ሥራ በተሰናዱ ማረሚያ ቤቶች ስለመሆኑ ደንግጓል (አንቀጽ 106(2) እና አንቀጽ 108(2))፡፡

በቀላልም ሆነ በፅኑ እስራት እንዲቀጡ የተወሰነባቸው ወንጀለኞች የመስራት ግዴታ አለባቸው፡፡ በዚህም መሠረት ሥራ የየትኛውም ዓይነት የእስራት ቅጣት አፈጻጸም አካል ነው፡፡

የታመመ እስረኛ ወደ ሀኪም ቤት ሲገባ ሆስፒታል የቆየበትን ጊዜ መቁጠርን በተመለከተ በቀድሞው ሕግ ቁጥር 115(1) ላይ እስረኛው በሀኪም ቤት ገብቶ የታከመው ከመታሰሩ በፊት በደረሰበት ህመም ወይም ሌላ ምክንያት ከሆነ ይህ ጊዜ ከእስራቱ ዘመን ውስጥ ላይታሰብለት እንደሚችል የሚደነግግ ሲሆን አዲሱ የወንጀል ሕግ ግን ህመሙ የደረሰበት በእራሱ ጥፋት እስካልሆነ ድረስ በሀኪም ቤት የቆየበት ጊዜ በሙሉ ከሚፈፅመው ቅጣት ጋር ሊታሰብለት ይገባል ይላል (አንቀጽ 116(1))፡፡

2.1.1.4. <u>የሞት ቅጣት</u>

የሞት ቅጣት የሰውን ህይወት የሚያሳጣ ፍርድ ነው፡፡ የሞት ፍርድ በአጠቃላይ በተለዩ ሁኔታ ከባድ ተብለው ለሚገመቱ ወንጀሎች የሚደነገግ የቅጣት ዓይነት ነው፡፡ የሞት ቅጣት ብቸኛ ቅጣት እንዲሆን በሕጉ ልዩ ክፍል ውስጥ ወንጀሉ በሞት ሊያስቀጣ የሚችል ስለመሆኑ ተደንግጎ መገኘት ያለበት ከመሆኑ በተጨማሪ የተለዩ ማክበጃ

ምክንያቶች ተሟልተው መገኘት ያለባቸው ስለመሆኑ በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል ላይ ተመልክቷል። በዚህም መሠረት የሞት ቅጣት የሚወሰነው፡-[8]

- የተፈፀመው ወንጀል የሞት ቅጣት የሚያስቀጣ ስለመሆኑ ወንጀሉን በሚያቋቁመው የሕጉ ልዩ ክፍል በግልፅ ተደንግጐ በተገኘ ጊዜ፣
- ለወንጀለኛው ቅጣትን የሚያቃልልለት ምክንያት በማይኖርበት ጊዜ፣
- ወንጀሉ ፍፃሜ ያገኘ ማለትም በሙከራ ደረጃ ላይ ያልተገታ ሲሆን /የቀድሞው የአማርኛ ቅጅ በዚህ ነጥብ ላይ ግልፅ አልነበረም/፣
- የተፈፀመው ወንጀል እጅግ በጣም ከባድና ወንጀለኛው በተለይ አደገኛ ሲሆን /በቀድሞው ሕግ ላይ ያልነበረ/፣ እንዲሁም
- ወንጀለኛው ወንጀሉን በፈፀመበት ጊዜ ዕድሜው ቢያንስ አስራ ስምንት ዓመት የሞላው ሲሆን ነው።

በድሮው ዘመን የሞት ቅጣት በጎራዴ ጭንቅላትን በመቅላት፣ ብረት ላይ ወይም እንጨት ላይ አጋድሞ በመጋዝ በመቁረጥ፣ ከግንድ ጋር አስሮ በእሳት በማቃጠል፣ አንድን ሰው ከነሕይወቱ በመቅበር፣ በርሀብ ተሰቃይቶ እንዲሞት ጉድጓድ ውስጥ በመጣል እና በመሳሰሉት አሰቃቂ መንገዶች ይፈፀም እንደነበር ይነገራል።[9] የሞት ቅጣትን አፈጻጸም በተመለከተ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር 116 የሞት ቅጣት ያለአንዳች ጭካኔ፣ የአካል መቆራረጥ ወይም ሌላ ዓይነት የአካል ጉዳት መፈፀም አለበት ይላል። በሌላ በኩል ግን የሞት ቅጣት በሕዝብ ፊት ወይም በአደባባይ በስቅላት እንደሚፈፀም ይደነግግ ነበር።

አዲሱ የወንጀል ሕግ ግን ከቀድሞው ሕግ በተቃራኒ የሞት ቅጣት በሕዝብ ፊት፣ በአደባባይ በስቅላት ወይም በሌላ ኢሰብአዊ በሆኑ ዘዴዎች መፈፀም እንደሌለበት ደንግጓል(አንቀጽ 117(3))። የአፈፃፀም ዘዴው ግን ጉዳዩ በሚመለከተው የፌዴራል ወይም የክልል ማረሚያ ቤት የበላይ ሕግ አስፈፃሚ አካል እንዲወሰን ተደርጓል። ይህም

[8] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 117፣1997
[9] ፋሲል ናሆም(ዶ/ር)፣ ቅጣትና ጎብረተሰብ፤ዕድገታዊ አመለካከት፣የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት፣ቮልዩም 12፣ 1974፣ ገጽ 16

የሆነው ጉዳዩ የሚመለከተው የማረሚያ ቤቶች የበላይ ሕግ አስፈፃሚ አካል በየአካባቢው ባሉት ሁኔታዎች መሠረት አቅም በፈቀደ መጠን ሰብአዊ በሆነ መንገድ የሞት ፍርድ የሚፈፀምበትን ዘዴ እንዲወስን ለማስቻል ታስቦ ስለመሆኑ ተመልክቷል።[10]

የሞት ፍርድ የተፈረደበት ሰው በፍፁም ኢ-ኃላፊነት ወይም ከፊል ኃላፊነት ላይ የሚገኝ ከሆነ የአዕምሮ ሁኔታው እስኪስተካከል ማለትም የማመዛዘን ችሎታው እስኪመለስ ድረስ፣ በፅኑ የታመመ ሰው ከሆነ ሕመሙ እስኪሻለው (እስኪፈወስ) ድረስ፣ ያረገዘች ሴት ከሆነች እስክትወልድ ድረስ አፈጻጸሙ ታግዶ ይቆያል።

እንዲሁም የሞት ቅጣት ሊለወጥ የሚችላባቸው ሁኔታዎች አሉ። ይኸውም ያረገዘች ሴት በእርግዝናዋ ወቅት ፍርዱ ሳይፈፀም ታግዶ የሚቆይ ብቻ ሳይሆን ህይወት ያለው ልጅ የወለደች እንደሆነና ልጁን መመገብና ማሳደግ የሚኖርባት የሆነ እንደሆነ ቀደም ሲል ተፈርዶባት የነበረው የሞት ቅጣት ወደ ዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ይቀየርላታል። ከዚህ በተለዬ ደግሞ የሞት ፍርድ በሚመለከተው አካል በሚሰጥ ይቅርታ ቅጣቱ ሊለወጥ ወይም ሙሉ በሙሉ ቀሪ ሊሆን የሚችል ሲሆን እንዲሁም ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው ሰው በመንግስት የተሰጠ ምህረት ተጠቃሚ ከሆነ ቅጣቱ ሊቀርለትና ጥፋተኛ የተባለበትን ወንጀል ጭራሽ እንዳልፈፀመ ሊቆጠር ይችላል።

2.1.2. ተጨማሪ ቅጣቶች

ተጨማሪ ቅጣቶች የሚባሉት ማስጠንቀቂያ፣ ወቀሳ፣ ተግሳፅ፣ ጥፋተኛው ተበዳዩን ይቅርታ እንዲጠይቅ ማድረግ፣ ከመብት መሻር እና ወታደራዊ ማዕረግን መግፈፍ ናቸው። በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር 120 ለአንዳንድ ከባድ ወንጀሎች ግርፋት በተጨማሪ ቅጣትነት ተደንግጎ ነበር። እንዲሁም ግርፋት በተጨማሪነት ቅጣትነት ሊጣልባቸው የሚችሉ የወንጀል ዓይነቶችን ዝርዝር በድንጋጌ ቁጥር 45/1953 ወጥቶ ነበር። ሆኖም ግርፋት በተግባር ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ተፈጻሚ ሳይደረግ የቆየ የቅጣት ዓይነት ነው።

[10] የወንጀል ሕግ ሐተታ ዘምክንያት፣ መስከረም 1998፣ ገጽ 68(ያልታተመ)

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ የግርፋት ቅጣትን ሰርዞታል። በወንጀል ሕጉ ሐተታ ዘምክንያት ላይ እንደተመለከተው የግርፋት ቅጣት ከአዲሱ የወንጀል ሕግ እንዲወጣ የተደረገው ተግባሩ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት ላይ የሰፈሩትን መሠረታዊ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች የሚፃረር ሆኖ በመገኘቱ ነው።[11] በእርግጥም እንዲህ ዓይነት ቅጣት በሕገ መነግስቱ አንቀጽ 18 ላይ "ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት፣ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው" በሚል የተደነገገውን ክልከላ የሚጥስ ከመሆኑም ባሻገር ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን ወይም የተቀበላቻውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና መግለጫዎች የሚጻረር ተግባር ነው።

በመሠረቱ ተጨማሪ ቅጣቶች ዋና ቅጣቶችን የሚተኩ አይደሉም። ስለዚህም በተከሳሹ ላይ ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ቅጣቶችን ከመወሰኑ በፊት አስቀድሞ ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ ለተገኘበት ወንጀል ተገቢ የሆነውን ዋና ቅጣት መወሰን አለበት።

ምንም እንኳን በመርህ ደረጃ ተጨማሪ ቅጣቶች ዋና ቅጣቶችን የሚተኩ ተደርገው የሚወሰዱ ባይሆንም ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘበት ወንጀል በጣም ቀላል የሆነ ዓይነት ወንጀል ከሆነ ፍርድ ቤቱ ለወንጀሉ የተመለከተውን ዋና ቅጣት በመተው ተግሳፅ፣ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወይም ጥፋተኛው ይቅርታ ተበዳዩን እንዲጠይቅ በማድረግ ሊያልፈው ይችላል።[12] ይህ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ውስጥ የነበረው አካሄድ በአዲሱ የወንጀል ሕግም የተካተተ ሲሆን ነገር ግን የወንጀለኛ መቅጫ ህጉ "እጅግ ቀላል የሆኑ ወንጀሎች" የሚባሉት ምን ዓይነት ወንጀሎች ናቸው የሚለውን በሚመለከት በግልጽ ያስቀመጠው መስፈርት አልነበረም። በመሆኑም ከማስጠንቀቅ ጋር ፍርድ ቤቱ በየትኞቹ የወንጀል ዓይነቶች ጥፋተኛውን በወቀሳ ወይም በተግሳጽ ሊያልፈው እንደሚችል በሕግ ባለሙያዎች መካከል አከራካሪ የሆነ ጉዳይ ነበር።

በአዲሱ የወንጀል ሕግ ግን "በጣም ቀላል የሆኑ ወንጀሎች" የሚባሉት የትኞቹ ዓይነት ወንጀሎች እንደሆኑ በዳኞች እንዲወሰን አልተተወም። በዚህም መሰረት "በጣም ቀላል የሆኑ ወንጀሎች የሚባሉት ከሦስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከአንድ

[11] የወንጀል ሕግ ሐተታ ዘምክንያት፣መስከረም 1998፣ገጽ 71(ያልታተመ)
[12] የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 87፣ 1949፤ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 89፣1997

ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ የሚያስቀጡ ወንጀሎች ናቸው" ተብሎ በአንቀጽ 89 ሁለተኛ ፓራግራፍ ላይ ተደንግጎ ይገኛል።

አንድ ወንጀል አድራጊ ለፈፀመው ወንጀል ከሚወሰንበት ዋና ቅጣት በተጨማሪ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሌሎች ተደራቢ ቅጣቶችም ሊወሰኑበት ይችላሉ። ማለትም ለተፈፀመው ወንጀል አግባብነት ያለው ድንጋጌ ላይ ባይመለከትም ፍርድ ቤቶች አስፈላጊ ሆኖ ባገኙት ጊዜ ሁሉ ተጨማሪ ቅጣቶችን ሊወስኑ ይችላሉ። "ፍርድ ቤቶች አስፈላጊ ሆኖ ባገኙት ጊዜ ሁሉ" ሲባል በዘፈቀደ ዳኞች ተጨማሪ ቅጣቶችን መወሰን ይችላሉ ለማለት አይደለም። ዳኞች ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ ለተገኘበት ወንጀል ተገቢ የሆነውን ዋና ቅጣት ከወሰኑ በኋላ ተከሳሹ ጥፋተኛ በተባለበት አንቀጽ ላይ ባይመለከትም በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ተጨማሪ ቅጣቶች ሊወሰኑ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎችና መስፈርቶች ግምት ውስጥ በማስገባት "አስፈላጊ ሆኖ ባገኙት ጊዜ ሁሉ" ከዋናው ቅጣት በተደራቢ ተጨማሪ ቅጣቶችን መወሰን ይችላሉ ለማለት ነው።

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ሁሉም የወንጀል ጥፋቶች ተጨማሪ ቅጣቶችን አያስከትሉም። በተለይም ደግሞ አንድ ጥፋት የመብት መሻር ተጨማሪ ቅጣትን በአጥፊው ላይ ያስከትል እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ፍርድ ቤቱ የሚወስነው የጥፋቱን ዓይነትና ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት አጥፊው በመብቶቹ መገልገሉን ሊቀጥል የሚገባው ሰው መሆን አለመሆኑን በማመዛዘን ነው። ሆኖም ጥፋተኛው በፈፀመው የወንጀል ተግባር ምክንያት የሞት ወይም የዕኑ እስራት ቅጣት የሚጣልበት ከሆነ ጥፋቱ ከዋና ቅጣቱ በተጨማሪ ከሕዝባዊ መብት መሻር ውሳኔን በግድ ማስከተል አለበት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 124(2))። ሌሎች ዋና ቅጣቶች ግን እንደ ሁኔታው ከሕዝባዊ መብት መሻርን ሊያስከትሉም ላያስከትሉም ይችላሉ። በዚህም መሰረት ፍርድ ቤቱ የጥፋቱን ዓይነትና ወንጀሉ የተፈፀመበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ጥፋቱ እንደ አግባብነቱ የመብት መሻር ሊያስከትል ይገባ ወይም አይገባ እንደሆነ ይወስናል።

ፍርድ ቤቱ በሚወስነው ተጨማሪ ቅጣት መሠረት ሊሻሩ የሚችሉት የወንጀለኛው ሕዝባዊ መብቶች የሚባሉት በምርጫ በመምረጥ ወይም በመመረጥ ተካፋይ መሆን፣ ለሕዝብ አገልግሎት ወይም ለማዕረግ መመረጥ፣ በሰነድ ወይም የውል ስምምነት ላይ

ምስክር ወይም ዋስ መሆን፣ ለፍርድ ሥራ ልዩ አዋቂ ወይም ካባሪ ሆኖ የመስራት መብቶችን ሁሉ የሚመለከት ሲሆን ሌሎች መብቶች ደግሞ አጥፊው ወላጅ በመሆኑ ያለው የወላጅነትና የአስተዳዳሪነት ሥልጣን፣ ሞግዚት የመሆን፣ በሙያው የመሥራት፣ ፈቃድ የሚያስፈልገውን የንግድ ድርጅት ወይም ኢንዱስትሪ አቋቁሞ የመስራት መብቶቹን ሁሉ ያካትታል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 123)።

ከመብት መሻር ጋር በተያያዘ በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 122(ለ) ላይ ወንጀለኛው በመብቶቹ ሊሠራባቸው ያልተገባ ሰው መሆኑ ሲታወቅ የአባትነት ሥልጣንን ከመያዝ ችሎታው ፍርድ ቤቱ ሊሽረው እንደሚችል ተመልክቶ የነበረ ሲሆን ወንጀለኛ አባት ብቻ ሳይሆን እናትም ልትሆን ስለምትችል በሁለቱም ሁኔታዎች ሊያስኬድ በሚችል አገላለጽ በአዲሱ የወንጀል ሕግ ላይ "የወላጅነት ሥልጣንን ከመያዝ ችሎታው" ተብሎ እንዲሻሻል ተደርጓል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 123(ለ))።

ማናቸውም ዓይነት ከመብት የመሻር ተጨማሪ ቅጣት ለጊዜው ወይም ለዘወትር ማለትም እስከ ጥፋተኛው በህይወት እስካለ ድረስ እንዲዘልቅ ተደርጎ ሊወሰን የሚችል ሲሆን የሞት ወይም የዕድሜ ልክ ዕኑ እስራት ቅጣት ፍርድ የሚያስከትለው ከመብት መሻር ግን ለዘወትር ፀንቶ መቆየት ያለበት ስለመሆኑ ተመልክቷል።[13] ይህ ሲባል ግን ለወንጀለኛው በመንግስት የሚሰጡ የይቅርታ ወይም የምህረት ውሳኔዎች እንዲሁም በፍርድ ቤት በኩል ሊሰጥ የሚችለው የመሰየም ውሳኔ ውጤት በጥፋተኛው ላይ በተሰጡ የመብት መሻር ተጨማሪ ቅጣቶች ላይ የሚኖረው ውጤት እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው። በዚህም መሰረት በአንድ ጥፋተኛ ላይ የዕድሜ ልክ ዕኑ እስራት ቅጣት ቢፈረድና በሕጉ መሰረት እንዲህ ዓይነት ቅጣት የሚያስከትለው ከመብት መሻር ለዘወትር እንደሚሆን የተመለከተ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ የተቀጪው መብት እስከ መጨረሻው እንዲሻር በተጨማሪ ቅጣትነት ቢወስንም መንግስት ለተቀጪው ይቅርታ ቢሰጠውና ይቅርታው ዋና ቅጣቱን ብቻ ሳይሆን ተጨማሪ ቅጣቶችን ጭምር የሚመለከት ቢሆን "ለዘወትር" ተብሎ በፍርድ ቤቱ የተጣለው ቅጣት ቀሪ ሆኖ ጥፋተኛው በፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽረው በነበሩት መብቶች ይቅርታ ከተሰጠው ጊዜ ጀምሮ መጠቀም ይችላል። እንዲሁም በተመሳሳይ ጥፋተኛው ላይ የዕድሜ ልክ ዕኑ

[13] የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 123(2)፤ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 124(2)

እስራት ቅጣት ቢፈረድና በሕጉ መሰረት እንዲህ ዓይነት ቅጣት የሚያስከትለው ከመብት መሻር ለዘወትር እንደሚሆን የተመለከተ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ የተቀጪው መብት እስከ መጨረሻው እንዲሻር በተጨማሪ ቅጣትነት ወስኖ እያለ ጥፋተኛው በአመክሮ ከእስር ተፈትቶ በሕጉ የተወሰነው ጊዜ (አምስት ዓመት ካለፈ) እና ሌሎች በሕጉ የተቀመጡትን መስፈርቶችን ካሟላ በፍርድ ቤት ውሳኔ ሊሰየም የሚችል በመሆኑ "ለዘወትር" ተብሎ በፍርድ ቤቱ የተጣለው ቅጣት ቀሪ ሆኖ ጥፋተኛው በፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽረው በነበሩት መብቶቹ የመሰየም ውሳኔ ከተሰጠው ጊዜ ጀምሮ መጠቀም ይችላል፡፡

ለጊዜው ብቻ ተብለው በፍርድ ቤት በጥፋተኛው ላይ የሚጣሉ ከመብት የመታገድ ወይም የመከልከል ውሣኔዎች በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 123(1) ከአንድ ዓመት አያንስም ተብሎ የተደነገገው የጊዜ ገደብ በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 124(1) ላይ ከስድስት ወር አያንስም በሚል ተተክቷል፡፡በሁለቱም ሕጎች ለጊዜው ብቻ ተብለው በፍርድ ቤት በጥፋተኛው ላይ የሚጣሉ ከመብት የመታገድ ወይም የመከልከል ውሣኔዎች ከአምስት ዓመት ደግሞ ሊበልጡ አይችሉም፡፡

2.2. <u>የጥንቃቄ እርምጃዎች</u>

በመሠረቱ በወንጀል አድራጊዎች ላይ የሚወሰዱ ማናቸውም እርምጃዎች አጠቃላይ የሕብረተሰብን ደህንነትና ሰላም ከመጠበቅ ሌላ መሠረታዊ ምክንያት ሊኖራቸው አይችልም፡፡ ይህን ለማስጠበቅ አንዳንድ ጊዜ በወንጀለኛው ላይ ቅጣትን መጣል ብቻ በቂ ላይሆን ወይም ደግሞ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡ የወንጀለኛውን አደገኛ ባህሪ፣ የወንጀሉን ጠባይ፣ ወንጀለኛው ወንጀሉን እንዲፈፅም ያነሳሱትንና ወንጀሉ የተፈፀመበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት እንደሁኔታው በወንጀለኛው ላይ ከቅጣት በተጨማሪ ወይም በቅጣቱ ምትክ አግባብነት ያላቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች መወሰን አስፈላጊ ነው፡፡

ስለዚህም አንድ ወንጀል አድራጊ ለፈፀመው ወንጀል ከሚወሰንበት ቅጣት በተጨማሪ ወይም በቅጣቱ ምትክ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የተለያዩ የጥንቃቄ እርምጃዎች ሊወሰኑበት ይችላሉ፡፡ ማለትም ለተፈፀመው ወንጀል አግባብነት ያለው ድንጋጌ ላይ

ባይመለከትም ፍርድ ቤቶች አስፈላጊ ሆኖ ባገኙት ጊዜ ሁሉ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሊወስኑ ይችላሉ፡፡ “ፍርድ ቤቶች አስፈላጊ ሆኖ ባገኙት ጊዜ ሁሉ” ሲባል በዘፈቀደ ዳኞች የጥንቃቄ እርምጃዎችን መወሰን ይችላሉ ለማለት አይደለም፡፡ ዳኞች ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ ለተገኘበት ወንጀል ተገቢ የሆነውን ቅጣት ከወሰኑ በኋላ ወይም እንደ አግባብነቱ ምንም ዓይነት ቅጣት በወንጀል ፈጻሚው ላይ ሳይጥሉ ተፈፀመ የተባለው ወንጀል የሚሸፈንበት አንቀጽ ላይ ባይመለከትም በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል የጥንቃቄ እርምጃዎች ሊወሰኑ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎችና መስፈርቶች ግምት ውስጥ በማስገባት “አስፈላጊ ሆኖ ባገኙት ጊዜ ሁሉ” በወንጀል አድራጊው ላይ የጥንቃቄ እርምጃዎችን መወሰን ይችላሉ ለማለት ነው፡፡

የጥንቃቄ እርምጃዎች በመሠረቱ ዋና ወይም ተጨማሪ ቅጣቶች አይደሉም፡፡ ዋና ዓላማቸው ወንጀለኞች እንደ አደገኛነታቸው መጠን በተለዬ ሁኔታ ቅጣታቸውን እንዲፈጽሙ ማስቻልና ወንጀለኞች ወይም ወደፊት ወንጀል ሊፈፅሙ ይችላሉ ተብለው የሚጠረጠሩ ሰዎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ መከላከልና መቆጣጠር ነው፡፡ የጥንቃቄ እርምጃዎች ለአጠቃላይ ሕብረተሰቡ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ጊዜ ለወንጀለኛውም ጠቀሜታ አላቸው፡፡ በዚህም መሰረት ወንጀለኞች ለወደፊት ወንጀል ለመፈፀም እንዳይችሉ ወንጀል ለመፈፀም እድል ይሰጣቸው የነበረ ሁኔታን በማስቀረት ለምሳሌ ወንጀሉ የተፈፀመው በሙያ ስራቸው ላይ ተሰማርተው በሚሰሩበት ጊዜ ከሆነ ሕጉ ያስቀመጠውን መመዘኛ ተከትሎ እንደ አግባብነቱ የሙያ ፈቃዳቸውን በመሰረዝ ወይም በመንጠቅ፣ የወንጀል ተግባር ለመፈፀም ምክንያት ከሆነው ወይም አዲስ ጥፋት ለመሥራት ከሚረዳው ከአንዳንድ ሥፋራዎች ለምሳሌ ከመሸታ ቤት፣ ከሆቴል ቤት፣ ወ.ዘ.ተ እንዳይደርስ በመከልከል እና በመሳሰሉት መንገዶች ወደፊት ሊፈፀሙ የሚችሉ ወንጀሎችን አስቀድሞ በመከላከል የሕብረተሰቡን ደህንነት ለማያረጋገጥ የሚወሰዱ የጥንቃቄ እርምጃዎች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ወንጀል አድራጊው በተለያዩ ምክንያቶች የአዕምሮ መቃወስ የደረሰበት ዓይነት ሰው የሆነ እንደሆነ እንደሁኔታው ተስማሚ በሆነ ተቋም ውስጥ ተለይቶ እንዲቀመጥ ወይም ሕክምና እንዲደረግለት በማድረግ፣ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ወንጀል አድራጊ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ በጠባቂ ስር ሆኖ ቁጥጥር እየተደረገበት ትምህርትና

መልካም አስተዳደግ እንዲኖረው በማድረግ ወይም ወደ ሕክምና ወይም ወደ ጠባይ ማረሚያ ተቋም በመላክ በሚደረግ የጥንቃቄ እርምጃ የህብረተሰቡን ደህንነት ከመጠበቅ ባሻገር ወንጀል አድራጊው ከችግሩ ተፈውሶ ወደ ሰላማዊ ኑሮ የሚመለስበት ዕድል የሚፈጠርበት ሁኔታ እንዲኖር ጠቀሜታ አለው፡፡

ሕብረተሰብ በሚጥላቸው ቅጣቶች ሊያስተላልፍ የሚሞክረው ማንኛውም መልዕክት በትክክል ከወንጀለኛው ሊደርስ የሚችለው ወንጀለኛው አስተዋይ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር በአንድ ሰው ላይ የሚፈፀመው ቅጣት ሊያስተውል የሚችለውን ያህል መሆን አለበት፤ የሚሰራውን ለማወቅ የማይችል ወይም የፈፀመው ተግባር ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት ለመረዳት የማይችል ሰው የጥንቃቄ እርምጃዎች ሊወሰኑበት ቢችልም ቅጣት ግን ሊፈፀምበት አይገባም፡፡ ስለዚህም በአዕምሮ መቃወስ ምክንያት ፍፁም ኃላፊነት የሌለባቸው ወንጀል አድራጊዎች በቀጣይ ሌላ ወንጀል እንዳይፈፅሙ የጥንቃቄ እርምጃዎች ይወሰኑባቸዋል እንጅ ቅጣት ሊጣልባቸው አይችልም፡፡ በመቀጠል በወንጀል ሕጋችን ውስጥ የተካተቱ አንዳንድ የጥንቃቄ እርምጃዎችን በአጭሩ እንቃኛለን፡፡

<u>የመልካም ጠባይ ዋስትና</u> - አንድ ወንጀለኛ ድጋሚ ወንጀል ለመስራት ማሰቡን ካሳወቀ ወይም አዲስ ወንጀል ይሰራል የሚል እርግጠኛ የሆነ ሥጋት ካለ ወንጀለኛው በመልካም ጠባይ የሚመራ ስለመሆኑ የማረጋገጫ ቃል እንዲገባና ቃሉ የሚጠበቅ ስለመሆኑም በቂ የሆነ ዋስትና እንዲሰጥ ፍርድ ቤት ሊያስገድደው ይገባል፡፡ ወንጀለኛው ዋስትናውን የሚሰጠው እንደነገሩ ሁኔታ ንብረት በማስያዝ፣ በሰው ዋስትና ወይም በራሱ ዋስትና ሊሆን ይችላል፡፡

በዚህ መሰረት የመልካም ጠባይ ዋስትና እንዲያቀርቡ በፍርድ ቤት ሊገደዱ የሚችሉት ከአሁን በፊት ወንጀል ሰርተው ለዚህም ጥፋተኛ ሆነው የተገኙና በቀጣይም ሌላ ወንጀል የመፈፀም ሀሳብ ያላቸው ስለመሆኑ በይፋ የገለፀ ወይም አዲስ ወንጀል እንደሚፈፅሙ በእርግጥ የሚያሰጉ ሰዎች ናቸው እንጅ ማናቸውም ወንጀል ሊፈፅም ይችላል ተብሎ የሚታሰብ ወይም ወንጀል የሚፈፅም ስለመሆኑ ያሳወቀ ሰው ለመልካም ጠባይ አመራር ማረጋገጫ ዋስትና እንዲያቀርብ ሊጠየቅ አይችልም፡፡ ሆኖም በወንጀል

ሕጉ አንቀጽ 141 ላይ እንደተደነገገው ማንም ሰው ከመከሰሱ በፊት ወይም ጉዳዩ በፍርድ ቤት በሚታይበት ጊዜ ገና ሳይፈረድበት በጋራ ወይም በግል ፀጥታ ላይ አደጋ ለማድረስ ዝቶ ከተገኘ የመልካም ጠባይ ማረጋገጫ ዋስትና እንዲሰጥ በፍርድ ቤት ሊገደድ ይችላል፡፡

በመልካም ጠባይ ለመመራት የሚሰጥ ዋስትና የሚቆይበት ጊዜና የዋስትናው መጠን በፍርድ ቤት የሚወሰነው የዛቻውን ዓይነት፣ ከባድነትና አደገኛነቱን እንዲሁም የወንጀለኛውንና የዋሶቹን የግል ኑሮ ደረጃና የሀብት ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገበት መሆን አለበት፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን በማናቸውም ሁኔታ የዋስትና ማረጋገጫው የሚቆይበት ጊዜ ከአንድ ዓመት ሊያንስ ወይም ከአምስት ዓመት ሊበልጥ አይችልም፡፡[14]

<u>አደገኛ የሆኑ ነገሮችን መውረስ</u> - ለወደፊት ወንጀል ለመስራት ሊያገለግሉ የሚችሉ ወይም ወንጀል ለመፈፀም ተግባር የዋሉ ነገሮች ወይም የአንድ ወንጀል ተግባር ፍሬ የሆኑ ማናቸውም ነገሮች የሕዝብን ሰላማዊ ኑሮ፣ ሥርዓት፣ ጤና ወይም መልካም ጠባይ ሊጎዱ የሚችሉ ከሆኑ ፍርድ ቤት ንብረቶቹ በመንግሥት እንዲወረሱ ማዘዝ ይኖርበታል፡፡

እንዲሁም ማንም ሰው ሊከሰስ ወይም ሊፈረድበት ባይችልም እንኳ በእጁ የተገኘ አደገኛ ነገር ሁሉ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ሁሉ በመንግሥት እንዲወረስ ፍርድ ቤቱ ሊያዝ ይችላል፡፡[15]

<u>የግል ነጻነትን መገደብ</u> - ለአንድ ወንጀል መፈፀም መንስኤ ሊሆኑ ከሚችሉት ምክንያቶች አንዱ ከወንጀለኛው የግል ባህሪ አንጻር በተወሰኑ ቦታዎች መገኘት ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም አንድ ወንጀለኛ ወደ ተወሰኑ ቦታዎች በነጻነት ቢሄድ ወይም ቢመላለስ ሌላ አዲስ ወንጀል ይፈፅማል ተብሎ ከተገመተ ከሦስት ወር እስከ አንድ

[14] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 135
[15] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 141

ዓመት ድረስ ከነዚህ ስፍራዎች እንዳይደርስ ሊከለከል ይችላል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 145(2))።

እንዲሁም በአንድ በሆነ ስፍራ ባይኖር ወይም በአንድ በተወሰነ ሥፍራ ብቻ ቢኖር ወይም መደበኛ ሥራውን እየሰራ በተወሰኑ ጊዜያት ውስጥ ወይም በተጠራ ቁጥር በአንድ ባለስልጣን ፊት እየቀረበ ሪፖርት ቢያደርግ፣ ለወንጀለኛው በሚመለከታቸው አካላት ተሰጥተው የነበሩ ወረቀቶች ወይም የፓስፖርት ሰነዶችን ለጊዜው ቢያዙ (ቢነጠቅ) ወይም ከአገር እንዲወጣ ቢደረግ ወደፊት ወንጀል ሊሰራ የሚችልባቸውን አጋጣሚዎች መቀነስ ወይም ማስቀረት ይቻላል ተብሎ በፍርድ ቤቱ ዘንድ ከተገመተ እንደ ነገሩ ሁኔታ ከነዚህ የጥንቃቄ እርምጃዎች አንዱን ወይም ሁለቱን ፍርድ ቤቱ በጥፋተኛው ላይ ሊወስን ይችላል።

አንድ ወንጀለኛ በእንድ በተወሰነ ከተማ፣ መንደር፣ ወይም በአንድ የተወሰነ አካባቢ እንዳይኖር ወይም ውሎ እንዳያድር በፍርድ ቤት የሚወሰን የክልከላ የጥንቃቄ እርምጃ በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሰረት ለዘወትር ማለትም እስከ ወንጀለኛው ዕድሜ መጨረሻ ድረስ ሊቆይ እንደሚችል ተደንግጎ ነበር። በአዲሱ የወንጀል ሕግ መሰረት ግን እንዲህ ዓይነት የእገዳ ውሳኔ ሊቆይ የሚችለው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እንጅ ለዘወትር (ለዕድሜ ልክ) ሊሆን አይችልም። ድንጋጌው እንዲሻሻል በምክንያት የተነሳው እንዲህ ዓይነት ለዘወትር የሚጣል ክልከላ በተከለከለው ወንጀለኛ ነጻነት እና ለመታረም ባለው ዕድል ላይ ከባድ ችግር ያስከትላል የሚል ነው።[16] በዚህም መሰረት በእንድ በተወሰነ ቦታ እንዳይኖር ወይም ውሎ እንዳያድር በወንጀለኛው ላይ የሚጣለው የእገዳ ትእዛዝ ከአንድ ዓመት እስከ አስር ዓመት ድረስ ብቻ ሊቆይ እንደሚችል ተደንግጓል(የወንጀል ሕግ አንቀጽ 146(2))።

<u>የሥራ እንቅስቃሴን መገደብ</u> - የሕግ ሰውነት ያላቸውን ድርጅቶች ጨምሮ ማናቸውም ሰው ልዩ ልዩ ሥራዎችን ለማካሄድ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት የተሰጠውን ፍቃድ በመጠቀም በሚያከናውነው ስራ ከፍ ያለ አደጋ የሚያደርስ ወይም የተደጋጋመ ከባድ ወንጀል የሰራ እንደሆነ ለፈፀመው ወንጀል ከሚጣልበት ቅጣት ጋር ተጨማሪ

[16] የወንጀል ሕግ ሐተታ ዘምክንያት፣ መስከረም 1998፣ ገጽ 82(ያልታተመ)

በማድረግ ሥራውን ለመካሄድ የተሰጠው ፈቃድ እንደሁኔታው ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ለሚደርስ ጊዜ ሊያዝበት (ሊታገድበት) ይችላል፡፡ የተፈፀመው ወንጀል ብዙ ጊዜ የተደጋገመ ወይም በተለይ ከባድ ከሆነ ደግሞ የተሰጠው ፈቃድ እስከ መጨረሻው ሊወሰድበት ይችላል፡፡

አንድ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ወንጀል ለመፈፀም ወይም የወንጀል ዓላማን ለማራመድ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነና ወንጀሉም በሕዝብ ፀጥታ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ ድርጅቱ ሥራ እንዲያቆምና እንዲዘጋ ፍርድ ቤቱ መወሰን ይችላል፡፡ እንዲሁም በሕግ ሰውነት ባለው ድርጅት አማካኝነት የተፈፀመው ወንጀል ከአንድ ዓመት በበለጠ ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ ዓይነት ከሆነ ድርጅቱ እንዲፈርስና ንብረቱም እንዲጣራ ፍርድ ቤቱ ማዘዝ ይችላል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 143)፡፡

<u>የፅኑ ግዞት</u>/internment/- ፅኑ ግዞት በእስራት ቅጣት ሥር ሊመደብ የሚችል ቢሆንም ለየት የሚያደርገው የራሱ የሆነ ባህሪ አለው፡፡ ይኸውም እስራቱ ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ልዩ የግዞት ቦታ የሚፈፀም መሆኑ ነው፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር 129 ላይ እንደተመለከተው ይህ የግዞት ቦታ ጥብቅ ቁጥጥር ያለበትና እስረኞችም የጉልበት ስራ እንዲሰሩ የሚገደዱበት ቦታ ነው፡፡ የፅኑ ግዞት በአንድ ወንጀለኛ ሊወሰን የሚችለው ወንጀለኛው ከዚህ በፊት ወንጀል ፈፅሞ የተጣለበትን የእስራት ቅጣት አጠናቆ ከወጣ በኋላ አስቦ ሌላ አዲስ ወንጀል ከፈፀመና የወንጀል አፈጻፀሙ የወንጀል አድራጊውን አደገኛነት የሚያመለክት ከሆነ ወይም ወንጀለኛው ልማደኛ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ከሆነ ነው፡፡

ምንም እንኳን የፅኑ ግዞት በወንጀለኛ መቅጫ ሕጋችን ውስጥ እንደ አንድ የጥንቃቄ እርምጃ ተመልክቶ የነበረ ቢሆንም አዲሱ የወንጀል ሕጋችን ግን ይህን የጥንቃቄ እርምጃ አስመልክቶ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ከቁጥር 128-132 ተመልክተው የነበሩትን ድንጋጌዎች ሰርዟቸዋል፡፡ ለመሰረዙ ምክንያቶች ተብለው የተጠቀሱት ጉዳዮችም የፅኑ ግዞት ውሣኔ በፍርድቤቶች ተግባራዊ ሆነው የሚያውቅ ባለመሆናቸው፣ ፅኑ ግዞት የሚፈፀምበት ቦታና ሁኔታ በኢትዮጵያ ተመቻችቶ ስለማያውቅና በቅርብ ጊዜም ይህን ለማመቻቸት ይቻላል ተብሎ ስላልተገመተ እና በስዊዘርላንድና በስዊድን

አገሮች ከሚሠራበት በቀር በሌሎች አገሮች የማይታወቅ የጥንቃቄ እርምጃ ዓይነት በመሆኑ ምክንያት ስለመሆኑ ተጠቅሷል።[17]

3. ደጋጋሚነት፣ ተደራራቢ ወንጀሎች እና የቅጣት አወሳሰን

ደጋጋሚነት (recidivism) እና የቅጣት አወሳሰን

3.1.1. ደጋጋሚነት በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ

አንድ ሰው ቀደም ሲል ወንጀል መፈፀሙ ወይም ከዚሁ የተነሳ መቀጣቱ ብቻ ደጋጋሚ ወንጀለኛ አያሰኘውም። አንድ ሰው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ነው ማለትና በተደጋጋሚ ወንጀል የፈፀመ ነው ማለት የሚያስከትለው ውጤት የተለያዬ ነው። ደጋጋሚ ወንጀለኛት ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን በተደጋጋሚ የተቀጣ መሆን ወይም የወንጀል ሪኮርድ ያለው መሆን ግን ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ተደርጎ የሚወሰድ ነው። በዚህም መሰረት አንድ ሰው በተደጋጋሚ ወንጀል የፈፀመ በመሆኑ ምክንያት ቅጣቱ የሚከብድበት ቢሆንም በመጨረሻ ለፈፀመው ወንጀል በሕጉ ልዩ ክፍል ከተመለከተው ቅጣት ጣራ በማለፍ ቅጣት ሊጣልበት አይችልም። ሆኖም ደጋጋሚ ወንጀለኛ ሆኖ ከተገኘ ግን በሕጉ ልዩ ክፍል ጥፋተኛ ለተባለበት ወንጀል ከተደነገገው ጣራ በላይ ቅጣት ሊወሰንበት ይችላል። አንድን ሰው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ነው ለማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉም ሆነ በአዲሱ የወንጀል የተቀመጡ መሟላት ያለባቸው መመዘኛዎች አሉ።

ከወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር 82(1)(ለ) ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት እንደሚቻለው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ለማለት የመጀመሪያው መመዘኛ በወንጀለኛው ላይ ከዚህ ቀደም የወንጀል ክስ ቀርቦበት ቅጣት የተወሰነበት መሆን አለበት። አዲሱን ወንጀል በፈፀመበት ወቅት ቀደም ሲል ፈፅሞት በነበረው የወንጀል ድርጊት ምክንያት የወንጀል ክስ ያልቀረበበት ወይም ክስ ቢቀርብበትም ገና በጉዳዩ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔና ቅጣት ያልተጣለበት ከሆነ የደጋጋሚ ወንጀለኛነት መስፈርት አልተሟላም ማለት ነው። አዲሱ

[17] የወንጀል ሕግ ሐተታ ዘምክንያት፣ መስከረም 1998፣ ገጽ 74(ያልታተመ)

የወንጀል ሕግ በዚህ የመጀመሪያ መስፈርት ላይ ያደረገው ለውጥ ወንጀለኛው ከዚህ ቀደም ጥፋተኛ በተባለት ወንጀል የተቀጣው በእስራት መሆን አለበት የሚል ነው። በዚህም መሠረት አንድ ሰው በመጀመሪያው ወንጀል የተፈረደበት የገንዘብ መቀጮ፣ የግዴታ ሥራ ወይም ወቀሳና ማስጠንቀቂያ ከሆነ ለደጋጋሚነት ማሟያ ነጥብ አይሆንም ማለት ነው።

አንድን ሰው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ለማለት ሁለተኛው መመዘኛ ወንጀለኛው ከዚህ ቀደም የተወሰነበትን ቅጣት በሙሉ ወይም በከፊል ከፈፀመበት፤ ወይም በምህረት ወይም በአዋጅ ምህረት ቅጣቱ ከቀረለት ጊዜ ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሌላ ወንጀል የፈፀመ መሆን አለበት። አዲሱ የወንጀል ሕግ በዚህ መመዘኛ ላይም አንዳንድ ለውጦችን አድርጓል። ይኸውም በመጀመሪያው መስፈርት ላይ እንደተገለፀው ከዚህ ቀደም የተቀጣበት ወንጀል በእስራት የሚያስቀጣ መሆን ያለበት በመሆኑ ማንኛውንም ቅጣት ሳይሆን ይህን የእስራት ቅጣት በሙሉ ወይም በከፊል ከፈፀመበት፣ ወይም ቅጣቱ በይቅርታ ከቀረለት ጊዜ ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሌላ ወንጀል የፈፀመ መሆን አለበት (አንቀጽ 67)። እዚህ ላይ ከእንግሊዝኛው አገላለፅ ጋር እንዲስማማ ተብሎ በአዲሱ የወንጀል ሕግ በቀድሞው ሕግ "ምህረት" በሚል ተመልክቶ የነበረው "ይቅርታ" በሚል የተተካ ሲሆን "የአዋጅ ምህረት" የሚለው ደግሞ "ምህረት" ተብሎ መመልከቱ ልብ ሊባል ይገባል። ስለሆነም በቀድሞው ሕግ መሠረት አንድ ሰው የአዋጅ ምህረት (ምህረት ለማለት ነው) በተሰጠው በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ አዲስ ወንጀል ቢፈፅም ለደጋጋሚነት ማሟያ ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን በአዲሱ ሕግ መሠረት ግን ምህረት የተደረገለት ሰው አዲስ ወንጀል ቢፈፅም ምህረት ያገኘበት ከዚህ ቀደም የፈፀመው ወንጀል ለደጋጋሚነት ማሟያ ነጥብ አይሆንም ማለት ነው።

ሦስተኛው የደጋጋሚ ወንጀለኛነት መመዘኛ ወንጀለኛው አዲሱን ወንጀል የፈፀመው አስቦ/intentionally/ መሆን አለበት የሚል ነው። በዚህ መሰረት በቸልተኝነት የተፈፀመ ወንጀል ደጋጋሚ ወንጀለኛ አያሰኝም። በዚህ የደጋጋሚ ወንጀለኛነት መስፈርት ዙሪያ የቀድሞውም ሆነ አዲሱ የወንጀል ሕግ ተመሳሳይ ናቸው። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነጥብ ደጋጋሚ ለመባል ወንጀለኛውን ከዚህ ቀደም ያስቀጣውና አዲስ የተፈፀመው ወንጀል የግድ ተመሳሳይ መሆን የማይኖርባቸው መሆኑ ነው፤ ማለትም

መስፈርቶቹ እስከተሟሉ ድረስ የወንጀሎቹ ዓይነት ቢለያይም የሚያከስትለው ለውጥ የለም፡፡

አንድን ሰው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ለማለት አራተኛውና የመጨረሻው መመዘኛ ወንጀለኛው የፈፀመው አዲስ ወንጀል “እጅን አሳልፎ ለመስጠት የሚያበቃ” ዓይነት ወንጀል መሆን አለበት የሚል ነው፡፡ ይህ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር 82(1)(ለ) ድንጋጌ ላይ ሰፍሮ የነበረው መስፈርት ሲሆን በአዲሱ የወንጀል ሕግ መሰረት ግን ወንጀለኛው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ነው የሚባለው አዲስ የፈፀመው ወንጀል ቢያንስ እስከ ስድስት ወር ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል የሆነ እንደሆነ ነው በማለት በቀድሞው ሕግ የነበረውን መመዘኛ ለውጦታል፡፡

3.1.2. <u>በደጋጋሚ ወንጀለኞች ላይ የሚኖረው የቅጣት አወሳሰን</u>

ደጋጋሚ ወንጀለኛ የሆነ ሰው ከቀድሞ ቅጣቱ ትምህርት ያላገኘ ነው ተብሎ ስለሚገመት ይህ ሁኔታ በወንጀለኛው ላይ የሚጣለው ቅጣት ከፍ እንዲል ያደርገዋል፡፡ በወንጀለኛው የተፈፀመው አዲስ ወንጀል ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት በህጉ ላይ በተደነገጉት የደጋጋሚነት መስፈርቶች መሰረት ደጋጋሚ ወንጀለኛ ነው የሚያሰኘው ከሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር 193(1) መሰረት ፍርድ ቤቱ ለአዲሱ ወንጀል በሕጉ ልዩ ክፍል ወንጀለኛው ጥፋተኛ በተባለበት ድንጋጌ የቅጣት ጣራ ሳይገታ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ጠቅላላ ክፍል ለቅጣቱ ዓይነት እስካሰፈረው ከፍተኛ ቅጣት ድረስ ሊወስን ይችላል፡፡

በዚህም መሠረት ወንጀለኛው አዲስ የፈፀመው ወንጀል በገንዘብ መቀጮ የሚያስቀጣ ከሆነ ጥፋተኛ በተባለበት የወንጀል ድንጋጌ ላይ ባይመለከትም በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ቁጥር 88 ላይ እስከተደነገገው ጣራ ብር አምስት ሺህ ብር ድረስ፣ አዲስ የፈፀመው ወንጀል በቀላል እስራት የሚያስቀጣ ከሆነ በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ቁጥር 105 ላይ እስከተደነገገው ጣራ ሦስት ዓመት ቀላል እስራት ድረስ፣ አዲስ የፈፀመው ወንጀል በፅኑ እስራት የሚያስቀጣ ከሆነ በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ቁጥር 107 ላይ እስከተደነገገው ጣራ ሀያ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት ድረስ ፍርድ ቤቱ በጥፋተኛው ላይ ቅጣቱን አክብዶ መወሰን ይችላል ማለት ነው፡፡

እንዲሁም ወንጀለኛው ደጋጋሚና ቅጣት የማይመልሰው ሲሆን ጥፋተኛውን ወደ ፅኑ ግዞት እንዲላክ ፍርድ ቤቱ በቁጥር 128 ድንጋጌ መሠረት እንዲወስን የቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 193(2) ላይ ይደነግግ ነበር፡፡ በእርግጥ ስለ ጥንቃቄ እርምጃዎች በሚገልፀው የዚህ ጽሑፍ ክፍል እንደተመለከተው ፅኑ ግዞት የሚፈፀምበት ቦታና ሁኔታ በኢትዮጵያ ተመቻችቶ የማያውቅ ከመሆኑም ባሻገር የፅኑ ግዞት ውሣኔ በፍርድ ቤቶች ተግባራዊ ሆኖ የሚያውቅ አይደለም፡፡

በአዲሱ የወንጀል ሕግ መሠረት በደጋጋሚ ወንጀለኛ ላይ የሚጣለው ቅጣት አወሳሰን የተወሰኑ ለውጦች ተደርገውበታል፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 188(1) ላይ እንደተደነገገው አዲስ የፈፀመው ወንጀል ወንጀለኛውን ስለ ደጋጋሚነት በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት ደጋጋሚ ወንጀለኛ ነው የሚያሰኘው ከሆነ በመርህ ደረጃ ፍርድ ቤቱ ለአዲሱ ወንጀል በሕጉ ልዩ ክፍል ወንጀለኛው ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ የቅጣት ጣራ እጥፍ እስኪሆን ድረስ ቅጣቱን አክብዶ መወሰን ይችላል፡፡ በመሆኑም እንደ ወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ሁሉ ወንጀለኛው ጥፋተኛ የተባለበትን የሕጉ ልዩ ክፍል ድንጋጌ የቅጣት ጣራ አልፎ ፍርድ ቤቱ መወሰን ይችላል፡፡ ነገር ግን ቅጣቱን ሊያከብድ የሚችለው ጥፋተኛ ለተባለበት ወንጀል ከተመለከተው የቅጣት ጣራ እጥፍ እስኪሆን ድረስ እንጅ በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ለቅጣቱ ዓይነት እስከሰፈረው ከፍተኛ ቅጣት ድረስ ሊወስን አይችልም፡፡ ከዚህ አኳያ ወንጀለኛው አዲስ የፈፀመው ወንጀል እስከ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት ሚያስቀጣ ቢሆንና ወንጀለኛው ደጋጋሚ ቢሆን በአዲሱ የወንጀል ሕግ መሠረት በመርህ ደረጃ ቅጣቱ ሊከብድበት የሚችለው ጥፋተኛ ለተባለበት አዲስ ወንጀል እስከተመለከተው የቅጣት ጣራ አጠፌታ ማለትም እስከ አስር ዓመት ድረስ ነው፡፡ በቀድመው ሕግ መሠረት ግን ለእስራቱ ዓይነት ማለትም ለፅኑ እስራት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል እስከተመለከተው ከፍተኛ ቅጣት (ሀያ አምስት ዓመት) ድረስ ሊወስን ይችል ነበር፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው በአዲሱ የወንጀል ሕግ የተካተተው ለደጋጋሚ ወንጀለኛ በመርህ ደረጃ የሚኖረው የቅጣት አወሳሰን ዘዴ ነው፡፡ የተደጋገሙት ወንጀሎች ቁጥር ብዛት ያላቸው ከሆነ እንዲሁም የወንጀለኛው የአጥፊነት ደረጃና የድርጊቱ አደገኛነት

ከባድ ከሆነ ከወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ለአዲሱ ወንጀል በሕጉ ልዩ ክፍል ወንጀለኛው ጥፋተኛ በተባለበት ድንጋጌ ላይ የተጠቀሰውን የቅጣት ጣራ በማለፍ በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል ለቅጣቱ ዓይነት እስከሰፈረው ከፍተኛ ቅጣት ድረስ ሊወስን ይችላል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 188(2))። እንዲሁም ወንጀለኛው ልማደኛ ደጋጋሚ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ለመጨረሻው አዲስ ወንጀል የሚጥለው ቅጣት በሕጉ ልዩ ክፍል ወንጀለኛው ጥፋተኛ በተባለበት ድንጋጌ ላይ ከተጠቀሰውን ቅጣት ጣራ የግድ በማለፍ መሆን ያለበት ስለመሆኑ በፍርድ ቤቱ ላይ አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ በዚሁ ንዑስ አንቀጽ ላይ ተደንግጓል።

እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነጥብ በየትኛውም ዘዴ ቢሆን ሕጉ በሚያዘው መሰረት በደጋጋሚ ወንጀለኛው ላይ ቅጣቱ እንዲከብድበት ሲደረግ በምንም ዓይነት ጥፋተኛው አዲስ ለፈፀመው ወንጀል በሕጉ ልዩ ክፍል ከተመለከተው ቅጣት አንጻር በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ለቅጣት ዓይነቱ ከተደነገገው ጣራ ቅጣት በማለፍ ፍርድ ቤቱ ቅጣት ሊጥል የማይችል መሆኑ ነው። ይህም ማለት ጥፋተኛ ለተባለበት አዲስ ወንጀል እስከተመለከተው የቅጣት ጣራ አጠፊታ ድረስ ፍርድ ቤቱ በጥፋተኛው ላይ ቅጣቱን ሊያከብድበት የሚችል ቢሆንም በሕጉ ልዩ ክፍል ለወንጀሉ የተቀመጠውን ቅጣት አጠፊታ ሲያደርግ በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ለቅጣቱ ዓይነት የተመለከተውን ገደብ የሚያልፍ ከሆነ ቅጣቱን በመቀነስ የጠቅላላ ክፍሉን ጣራ ቅጣት በወንጀለኛው ላይ ተፈጻሚ ያደርጋል ማለት ነው።

3.2. ተደራራቢ ወንጀሎች እና ቅጣት አወሳሰን

3.2.1. የተደራራቢ ወንጀሎች ምንነት

ተደራራቢ ወንጀሎች (Concurrence offences) በአጠቃላይ በአንድ ሰው ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ወንጀሎች ተፈፅመው ሲገኙ ያለውን ሁኔታ የሚመለከት ሲሆን ሁለት ወይም ቁጥራቸው ከዚያ በላይ የሆኑ ወንጀሎች ተደራራቢ ናቸው ሊባሉ የሚችሉት ሁለተኛው ወንጀል ከመፈፀሙ በፊት መጀመሪያ በተፈፀመው ወንጀል ላይ

ፍርድ አልተሰጠ እንደሆነ ነው፡፡ የወንጀሎች መደራረብ በሁለት ተከፍሎ ሊታይ ይችላል፡፡

<u>ግዙፍ የሆነ (ቁሳዊ) መደራረብ</u> /Material concurrence/-አንድ ሰው ተመሳሳይ ድርጊቶችን በተለያዩ ጊዜያት በመፈጸም እንደ አንድ ወንጀል የማይቆጠሩ ወንጀሎችን ሲፈፅም ወይም ተመሳሳይ ያልሆኑ ማለትም የተለያዩ ድርጊቶችን በተለያዩ ጊዜያት በመፈጸም በተለያዩ የወንጀል ድንጋጌዎች ሥር የሚወድቁ ወንጀሎችን የፈፀመ እንደሆነ ግዙፍ የሆነ (ቁሳዊ) መደራረብ አለ ይባላል፡፡ የእንዲህ ዓይነት ተደራራቢ ወንጀሎች ዓይነተኛ መለያ የድርጊቶች መደጋገም ነው፡፡ የድርጊት መደጋገም እስካለ ድረስ የተፈፀሙት ወንጀሎች ዓይነታቸው አንድ ቢሆንም ወይም ባይሆንም የተደራረቡ ወንጀሎች ናቸው፡፡ ማለትም እንደ አንድ ወንጀል የማይቆጠሩ ነገር ግን በአንድ አንቀጽ ስር የሚወድቁ በተለያዩ ጊዜያት የተፈፀሙ ተመሳሳይ ድርጊቶችም ቢሆኑ ግዙፍ የሆኑ ተደራራቢ ወንጀሎች ናቸው፡፡

ለምሳሌ፡- አንድ ሰው በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ ተደብቆ እየገባ የተለያዩ ንብረቶች ቢሰርቅ ወይም ደግሞ ዛሬ ጠዋት አንድ ሰው ቢገድል እና ማታ ላይ ደግሞ አንዲት ሴት አስገድዶ ቢደፍር የወንጀል ድርጊቶቹ ተመሳሳይ ቢሆኑም ባይሆኑም እንደ አንድ ወንጀል ተቆጥረው በአንድ አንቀጽ ብቻ አንድ የወንጀል ክስ የማይቀርብበት እስከሆነ የተደራረቡ ወንጀሎችን ፈጽሟል፡፡ እንዲህ ዓይነት መደራረብ የድርጊትን መደጋገም የሚያመለክት በመሆኑ ግዙፍ የሆነ ወይም ቁሳዊ መደራረብ በመባል ይጠራል፡፡

<u>ሐሳባዊ (ጣምራዊ) መደራረብ</u> /Notional concurrence/ - አንድ ሰው በአንድ ድርጊት ግዙፍነት ያላቸው ወይም የሌላቸው ውጤቶችን በማስከተል ከአንድ በላይ የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎችን የጣሰ እንደሆነ ሐሳባዊ መደራረብ አለ ይባላል፡፡ የሐሳባዊ መደራረብ መለያ ባህሪ በአንድ ነጠላ ድርጊት ከአንድ በላይ የሆኑ ወንጀሎች መፈፀማቸው ነው፡፡ በድርጊት ደረጃ የተፈፀመው ተግባር አንድ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም የተፈፀመው አንድ ድርጊት ከአንድ በላይ የሆኑ ግዙፍ የሆኑ ውጤቶችን ካስከተለ ወይም ደግሞ ድርጊቱ ከአንድ በላይ

የሆኑ ግዙፍ ውጤቶችን ባያስከትልም ከሕግ አንጻር በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ የሆኑ የህግ ድንጋጌዎችን የሚጥስ ተግባር ሆኖ ከተገኘ የተደራረቡ ወንጀሎችን ፈጽሟል፡፡

ለምሳሌ፡- አንድ ሰው በአንድ ጥይት አስቦ አንድ ሰው ቢገድል እና በዚያው ጥይት ደግሞ ሌላ ሰው ቢያቆስል በድርጊቱ ላደረሰው ሞት በግድያ ወንጀል እና በዚያው ድርጊት ላደረሰው ማቁሰል በመግደል ሙከራ ወንጀሎች ሊጠየቅ የሚችል ሲሆን በዚህም መሰረት የተፈፀመው ድርጊት አንድ ብቻ ቢሆንም ያስከተላቸው ውጤቶች ግን ሁለት የሚታዩ ግዙፍነት ያላቸው ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ባለትዳር የሆነ ሰው አንዲት ሴት አስገድዶ ቢደፍር በአንድ ድርጊት የአመንዝራነት /የሴሰኝነት/ እና የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎችን ፈፅሟል፡፡ እዚህ ላይ ለማንኛውም ሰው ግልፅ ሆኖ የሚታየው የድርጊቱ ውጤት በሴትዮዋ ላይ በማስገደድ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የተፈፀመባት መሆኑ ነው፡፡ ሌላ የሚታይ ግዙፍ ውጤት የለም፡፡ ሆኖም ከሕግ አንጻር ሲታይ ግለሰቡ በፈፀመው አንድ ድርጊት ከአንድ በላይ የወንጀል ድንጋጌዎችን በመጣስ የተደራረቡ ወንጀሎችን ፈፅሟል፡፡ በዚህም መሠረት በሁለቱም ምሳሌዎች ላይ ከአንድ ድርጊት የተነሳ ከአንድ በላይ ወንጀሎች በመፈፀማቸው የተደጋገመው ድርጊቱ ሳይሆን ወንጀሎቹ ናቸው፡፡

3.2.2. <u>ወንጀሎች በተደራራቡ ጊዜ ስለሚኖረው የቅጣት አወሳሰን</u>

3.2.2.1. <u>ለተደራራቢ ወንጀሎች የቅጣት አወሳሰን ዘዴዎች</u>

ከዚህ በላይ ባለው የጽሑፉ ክፍል ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ወንጀሎች ተደራረቡ የሚባለው አንድ ሰው የተለያዩ የወንጀል ድርጊቶችን አከታትሎ በመፈፀም ግዙፍነት ያላቸውን የተለያዩ ወንጀሎችን ሲፈፅም ወይም በአንድ ድርጊት ከአንድ በላይ የሆኑ የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎችን በመጣስ ጣምራ ወንጀሎችን ፈፅሞ ሲገኝ ነው፡፡ የወንጀሎች መደራረብ በሚኖርበት ጊዜ ቅጣትን ለመወሰን የሚያገለግሉ መሠረታዊ ዘዴዎች ሦስት ናቸው፡፡

የመጀመሪያው የቅጣት አወሳሰን ዘዴ የማዳመር (cumulation) ዘዴ ሲሆን ይህ ዘዴ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተደራራቢ ወንጀሎችን አንድ ሰው ፈጽሞ

በሚገኝበት ጊዜ በመጀመሪያ ለእያንዳንዱ ወንጀል በተናጠል ተገቢ ነው ተብሎ የሚታመነውን ቅጣት በመወሰን በመጨረሻ ሁሉም ቅጣቶች አንድ ላይ እንዲደመሩ የሚደረግበት አሰራር ነው። ይህን ዘዴ የሚከተሉ አንዳንድ አገሮች የቅጣቶች አጠቃላይ ድምር በሕጉ ላይ ለቅጣቱ ዓይነት የተቀመጠውን ጣራ እንዳያልፍ ገደብ የሚያደርጉ ሲሆን ሌሎች አገሮች ደግሞ ቅጣቶቹ ያለገደብ እንዲደመሩ ያደርጋሉ። ስለሆነም በእነዚህ ገደብ በማያስቀምጡ የማዳመር የቅጣት አወሳሰን ዘዴን በሚከተሉ አገሮች አንድ ሰው ለፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች ሁለት መቶ ዓመት ወይም ሦስት መቶ ዓመት እስራት ሊፈረድበት ይችላል።

ሁለተኛው የቅጣት አወሳሰን ዘዴ የማጠቃለል (absorption) ዘዴ ሲሆን ይህ ዘዴ በ1923 ዓ.ም ወጥቶ በነበረው የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ ተካትቶ የነበረ አሰራር ነው። በዚህ ዘዴ መሠረት ወንጀለኛው ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘባቸው ተደራራቢ ወንጀሎች ውስጥ ከባድ (ከፍተኛ) ለሆነው ወንጀል የሚጣለው ቅጣት ለሌሎች ወንጀሎች ይወሰን የነበረውን ቅጣት አጠቃልሎ እንዲሸፍን ይደረጋል።

ሦስተኛው ለተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣት የሚወሰንበት ዘዴ የማክበድ (aggravation) ዘዴ የሚባለው ሲሆን ይህ ዘዴ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የማዳመር እና የማጠቃለል ዘዴዎችን በማጣመር የሚሰራበት ዘዴ ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚችል ነው። በዚህ የቅጣት አወሳሰን መርሕ መሰረት በወንጀለኛው ከተፈፀሙት ተደራራቢ ወንጀሎች ውስጥ ከባድ ለሆነው ወንጀል ቅጣት ከተወሰነ በኋላ ለቀሪዎቹ ወንጀሎች በሕግ በተወሰነው መጠንና ገደብ መሰረት የመጀመሪያው ቅጣት እንዲከብድ ይደረጋል።

3.2.2.2. <u>ለተደራራቢ ወንጀሎች የቅጣት አወሳሰን ዘዴ በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ</u>

ተደራራቢ ወንጀሎች ስለሚያስከትሉት ቅጣት አወሳሰን ከሚደነግጉት ድንጋጌዎች አንዱ የሆነው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 189(1)(ሀ) ድንጋጌ ላይ ወንጀለኛው ከፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች ውስጥ "በአንደኛው ምክንያት የሞት ቅጣት የሚወሰን ከሆነ ይህ የቅጣት ውሳኔ ስለሌሎቹ ተደራራቢ ጥፋቶች የሚወሰነውን ቅጣት ሁሉ

አጠቃሎ(ደርቦ) ይይዛል" ተብሎ ተደንግጓል። በዚህም መሠረት ለከባዱ ወንጀል የሚወሰነው ቅጣት የሞት ፍርድ ከሆነ ሌሎች ቅጣቶችን ስለሚያጠቃልል ወንጀለኛው ጥፋተኛ የተባለባቸውን ሌሎች ወንጀሎች ግምት ውስጥ በማስገባት የእስራት ቅጣት መወሰን አይቻልም ማለት ነው። በዚህ ጊዜ ሕጉ ለተደራራቢ ወንጀሎች የማጠቃለል (absorption) የቅጣት አወሳሰን ዘዴን ተከትሏል ማለት ነው።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር 189(1)(ለ) እንደተደነገገው ደግሞ ሌሎች ነጻነትን የሚያሳጡ ወንጀሎችን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ ቅጣትን የሚወስነው በመጀመሪያ ከሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች ውስጥ ከባድ ለሆነው ወንጀል የሚገባውን ቅጣት በወንጀለኛው ላይ ይወስንና በመቀጠል ሌሎችን ጥፋተኛው የፈፀማቸውን ተደራራቢ ወንጀሎች ግምት ውስጥ በማስገባት ቅጣቱን ያከብዳል። ፍርድ ቤቱ ይህን የማክበድ የቅጣት አወሳሰን ዘዴ ተከትሎ ተደራራቢ ወንጀሎችን በፈፀመው ወንጀለኛ ላይ ቅጣት ሲጥል ለከባዱ ወንጀል በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ልዩ ክፍል የተመለከተውን የቅጣት ጣራ ማለፍ የሚችል ሲሆን የከባዱን ወንጀል ቅጣት ጣራ አጋማሽ ያህል እስኪሆን ድረስ ቅጣቱን ማክበድ እንደሚችል ተመልክቷል። ነገር ግን የከባዱን ወንጀል ቅጣት ጣራ በማለፍ የቅጣቱን አጋማሽ ያህል በማሳደግ ፍርድ ቤቱ መቅጣት የሚችል ቢሆንም በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ለቅጣቱ ዓይነት የተመለከተውን ከፍተኛ ጣራ በማለፍ መወሰን አይችልም። በዚህም መሠረት ወንጀለኛው የፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ከሆነ በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ቁጥር 105 ላይ ለቀላል እስራት ከተደነገገው ጣራ ማለትም ከሦስት ዓመት ቀላል እስራት በላይ አሳልፎ ቅጣት ፍርድ ቤቱ ለመወሰን አይችልም፤ ወንጀለኛው የፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች በፅኑ እስራት የሚያስቀጡ ከሆነ ደግሞ በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ቁጥር 107 ላይ ለፅኑ እስራት ከተደነገገው ጣራ ማለትም ከሀያ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት በላይ አሳልፎ ፍርድ ቤቱ ቅጣት ለመወሰን አይችልም ማለት ነው።

በገንዘብ መቀጮ የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲያጋጥሙ ፍርድ ቤቱ ለእያንዳንዱ ወንጀል የሚገባውን ቅጣት ለየብቻው ቢወስን ኑሮ ከሚጣለው ቅጣት ሳያልፍ ከወሰነ በኋላ አንድ ላይ እንዲደመር በማድረግ አንድ ጠቅላላ መቀጮ በወንጀለኛው ላይ ይጥላል። በዚህ ጊዜ ሕጉ ለተደራራቢ ወንጀሎች የማዳመር

(cumulation)) የቅጣት አወሳሰን ዘዴን ተከትሏል ማለት ነው። ሆኖም የቅጣቶች አጠቃላይ ድምር በሕጉ ላይ ለቅጣቱ ዓይነት የተቀመጠውን ጣራ እንዳያልፍ ገደብ አድርጓል። በዚህም መሠረት ወንጀለኛው ለፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ቁጥር 88 ላይ ከተደነገገው ጣራ ማለትም ከብር አምስት ሺህ ብር በላይ አሳልፎ ቅጣት ፍርድ ቤቱ ሊወስን አይችልም ማለት ነው። የገንዘብ መቀጮው የአምስት ሺህ ብር ከፍተኛ ጣራውን በማለፍ እስከ ብር አስር ሺህ ብር ድረስ ሊጣል የሚችለው ወንጀሎቹ የተፈፀሙት በአፍቅሮ ንዋይ ከሆነ ነው።[18]

እዚህ ላይ የእስራት ቅጣቶችን ለማክበድ "በተወሰነው" ቅጣት ላይ እስከ ግማሽ ድረስ መጨመር ነው የሚለው የሕጉ አቀራረብ ላይ ይነሱ ከነበሩት ክርክሮች አንደኛው "በተወሰነው" ሲባል ዳኛው የወሰነውን ቅጣት ለማመልከት ነው ወይስ ለወንጀሉ በሕጉ ልዩ ክፍል የተደነገገውን ከፍተኛ ቅጣት ለማመልከት ነው የሚለው ጉዳይ ሲሆን ነገር ግን በብዙ የህግ ባለሙያዎች ዘንድ በሕጉ ልዩ ክፍል የተመለከተውን ለማለት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰድ ነበር /ይወሰዳል።

አንድ ሰው የፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች ከፊሎቹ የሚያስቀጡት በቀላል እስራት ከፊሎቹ ደግሞ በፅኑ እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች በሚሆኑበት ጊዜ የቅጣት አወሳሰኑ በምን ዓይነት መንገድ እንደሚሰላ የ1949 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በግልፅ የደነገገው ነገር አልነበረም።

በሌላ በኩል ግን ነጻነትን በመቀነስ (በቀላል ወይም በፅኑ እስራት) የሚያስቀጣ ወንጀል እና የገንዘብ መቀጮ የሚያስፈርድ ወንጀል ተደራራቢ በሚሆኑበት ጊዜ ቅጣቱ እንዴት እንደሚወሰን የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር 189(1)(ሐ) ድንጋጌ ያስቀምጣል። በንዑስ አንቀጹ ላይ እንደተደነገገው ወንጀለኛው ከፈፀማቸው ወንጀሎች ውስጥ አንዱ በእስራት ሁለተኛው ደግሞ በመቀጮ የሚያስቀጣ የሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ሁለቱንም ዓይነት ቅጣት በማጣመር ውሳኔ ለመስጠት ይችላል።

[18] የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 90፣

ከዚህ በላይ ለማንሳት የተሞከረው አንድ ሰው ከአንድ በላይ የወንጀል ድርጊቶችን በመፈፀም ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎችን በሚፈፅምበት ጊዜ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የተመለከተውን የቅጣት አወሳሰን ዘዴን ሲሆን በአንድ የወንጀል ተግባር ከአንድ በላይ የወንጀል ድንጋጌዎችን በመጣስ ተደራራቢ ወንጀሎችን በሚፈፅምበት ጊዜ የሚኖረው የቅጣት አወሳሰንን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ የሚወስነው በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር 192 ላይ የተቀመጠውን መስፈርት በመመልከት ነው።

በዚህም መሠረት አንድ ሰው በአንድ ድርጊት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ድንጋጌዎችን ከጣሰ (ጣምራ ወንጀሎችን ከፈፀመ) በመርህ ደረጃ ከጣሳቸው የወንጀል ድንጋጌዎች ውስጥ ከባድ ለሆነው ወንጀል ተገቢ የሆነውን ቅጣት ፍርድ ቤቱ ከጣለ በኋላ ወንጀለኛው የጣሳቸውን ሌሎች የወንጀል ድንጋጌዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ቅጣቱን የሚያከብድ ሲሆን በመጨረሻ የሚወሰነው ቅጣት ግን ለከባዱ ወንጀል ከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ጣራ ማለፍ አይችልም። ማለትም ፍርድ ቤቱ የሚወስነው ቅጣት ከሁሉም ይልቅ ከባድ ለሆነው ወንጀል በማስቀጫው አንቀጽ ላይ እስከተወሰነው ከፍተኛ ቅጣት ድረስ ብቻ ነው። ለከባዱ ወንጀል በማስቀጫው አንቀጽ ከተወሰነው ከፍተኛ ቅጣት በማለፍ ሊወስን የሚችለው "... የነገሩ አካባቢ ሁኔታና ይልቁንም በተለይ የተገለፀው አድራጎትና ሆነ ብሎ በአሳብ የተሰራው ወንጀል ወይም ግልጽ የሆነው የወንጀለኛው መጥፎነት ጉዳይ በቂ ምክንያት የሚያስገኝ መሆኑን ፍርድ ቤቱ በገመተው ጊዜ..." ስለመሆኑ በተጠቀሰው ድንጋጌ ላይ ተመልክቷል። ይህ ሁኔታ በሚኖርበት ጊዜ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎችን በሚመለከት በተቀመጠው(በቁጥር 189) ዓይነት በወንጀለኛው ላይ ቅጣቱ እንዲከብድበት ተደርጎ ይወሰናል።

ከዚህ በላይ ከተገለፀው ለመረዳት የሚቻለው ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች ተፈፅመው ሲገኙ ፍርድ ቤቶች በቁጥር 189 መሠረት በወንጀለኛው ላይ ቅጣት አክብደው የመወሰን ግዴታ ያለባቸው ሲሆን በአንድ የወንጀል ድርጊት ከአንድ በላይ የሕግ ድንጋጌዎች በመጣሳቸው ምክንያት ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈፅመው ሲገኙ ግን ፍርድ ቤቶች በወንጀለኛው ላይ ቅጣቱን አክብደው የሚወስኑት እንደሁኔታው መሆኑን ነው። ከሀሳባዊ መደራረብ የተነሳ ወንጀል የሚፈፅም የፈፀመው ድርጊት አንድ ብቻ በመሆኑና ከሁኔታዎች አጋጣሚ የተነሳ ከአንድ በላይ የሆኑ የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎችን

በመጣሱ በተደጋጋሚ በፈፀማቸው ድርጊቶች ከአንድ በላይ ወንጀሎችን ከፈፀመ ሰው ጋር እኩል አደገኛ ነው ተብሎ አይገመትም፡፡ ስለዚህም ከሀሳባዊ መደራረብ የተነሳ ቅጣት ሊከብድ የሚችለው የወንጀሎቹ አፈጻጸም የወንጀል አድራጊውን አደገኛነት የሚያመለክት ከሆነ ብቻ ነው፡፡

3.2.2.3. <u>ለተደራራቢ ወንጀሎች የቅጣት አወሳሰን ዘዴ በአዲሱ የወንጀል ሕግ</u>

በተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣት አወሳሰን ዙሪያ አዲሱ የወንጀል ሕግ ከቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የሚለይባቸው የተለያዩ ጉዳዮች ቢኖሩም መሠረታዊ ተብሎ ሊጠቀስ የሚችለው ልዩነት ግን የተደራረቡ ወንጀሎች በተፈፀሙ ጊዜ ቀደም ሲል ይሰራበት የነበረው መሠረታዊ መርህ መለወጡ ነው፡፡ በዚህም መሠረት በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ አካሄድ ለከባዱ ወንጀል ቅጣት ከተወሰነ በኋላ ለሌላው ወንጀል እስከ መጀመሪያው (የከባዱ) ወንጀል ማስቀጫ አንቀጽ የቅጣት ጣራ አጋማሽ ድረስ ቅጣት ይጨመር የነበረበት የማክበድ (aggravation) መርህ ቀርቶ ለየቅጣቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገውን የቅጣት ጣራ እስካላለፈ ድረስ ለሁሉም ወንጀሎች የሚወሰኑ ቅጣቶች እንዲደመሩ ሆኗል፡፡ በተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣት አወሳሰን ዙሪያ በአዲሱ የወንጀል ሕግ የተካተቱትን ነጥቦች ቀጥለን በአጭሩ እንመለከታቸዋለን፡፡

ሀ. <u>ከተደራራቡት ግዙፍ ወንጀሎች ውስጥ ለአንደኛው የሚጣለው ቅጣት የቀሪዎችን ወንጀሎች ቅጣት የሚያጠቃልል በሆነ ጊዜ፣</u>

ከተደራራቢ ወንጀሎች ውስጥ በአንደኛው ምክንያት የሞት ወይም የዕድሜ ልክ እስራት ወይም ወንጀሎቹ ተመሳሳይ ዓይነት የእስራት ቅጣት የሚያስቀጡ ሆኖ በአንደኛው ምክንያት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ከተወሠነ ይህ ውሳኔ ለሌሎች ተደራራቢ ወንጀሎች የሚወሠነውን ቅጣት ሁሉ አጠቃሎ ይይዛል (አንቀጽ 184(1)(ሀ))፡፡ ይህም ማለት ከተደራራቢ ወንጀሎች ውስጥ በአንዱ ምክንያት የሞት ቅጣት ወይም የዕድሜ ልክ ዕኑ እስራት፣ የ25 ዓመት ዕኑ እስራት ወይም

የአምስት ዓመት ቀላል እስራት ከተወሠነ በሌሎች ተመሣሣይ ዓይነት ቅጣት በሚያስፈርዱ ወንጀሎች ምክንያት ከተገለፀው ቅጣት በላይ መወሠን አይቻልም። (በአንቀጽ 184/1//ሀ/ የተደነገገው ሁኔታ ቅጣቱ ቢከብድም ከተደራረቡት ወንጀሎች በአንደኛው ውስጥ በሕጉ ልዩ ክፍል ቅጣቱ ተካትቶ /ተሸፍኖ/ የምናገኝበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው)።

ነገር ግን ፍርድ ቤቱ ከባድ ለሆነው ለአንደኛው ወንጀል የሞት ቅጣት፤ የዕድሜ ልክ እስራት ወይም ለእስራቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገውን ከፍተኛ ቅጣት መወሰኑን ትቶ ዝቅ ያለ ቅጣት ከወሠነ፤ በሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ምክንያት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል እስከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ድረስ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን አክብዶ መወሠን ይችላል። ለምሳሌ አንድ ጥፋተኛ ከሚፈረድበት ወንጀሎች ውስጥ በአንደኛው ምክንያት የሀያ አምስት ዓመት ዕኑ እስራት ቅጣት የሚወሰንበት ከሆነ በሌሎች አነስተኛ ወንጀሎች ምክንያት የእስራት ቅጣት ሊወሰንበት አይችልም። ምክንያቱም ለዕኑ እስራት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተቀመጠው ከፍተኛ የቅጣት ጣራ ሀያ አምስት በመሆኑ ከዚያ አልፎ ሰላሳ ዓመት ወይም ደግሞ የዕድሜ ልክ ዕኑ እስራት ፍርድ ቤቱ ሊወስን ዓይችልም። የዕድሜ ልክ ዕኑ እስራት ሊወሰን የሚችለው ወንጀለኛው ከፈፀማቸው ወንጀሎች ውስጥ ቢያንስ አንዱ በዕድሜ ልክ ዕኑ እስራት የሚያስቀጣ ሆኖ ከተገኘ ብቻ ነው። ምንም እንኳን ወንጀለኛው የፈፀመው ከባዱ ወንጀል በሀያ አምስት ዓመት ዕኑ እስራት ቅጣት ሊያስቀጣ የሚችል ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የተለያዩ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ከቅጣት ጣራው ዝቅ በማድረግ ለከባዱ ወንጀል ቅጣት የሚጥል ከሆነ ሌሎች ጥፋተኛው የፈፀማቸው ወንጀሎች ግምት ውስጥ ገብተው ቅጣቱ እንዲከብድ ይደረጋል። በዚህ ሁኔታ ለተደራራቢዎቹ ወንጀሎች የሚወሰነው ቅጣትም ለሁሉም ወንጀሎች ለየራሳቸው ቅጣቶችን በመጣል እንዲደመሩ በማድረግ ይሆናል።

ለ. <u>በእስራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች ሲያጋጥሙ፤</u>

ጥፋተኛው ከፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች ውስጥ የየትኛውም ወንጀል ቅጣት የቀሪዎችን ወንጀሎች ቅጣት የሚያጠቃልል ካልሆነና ወንጀሎቹ በእስራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች ከሆኑ ለእያንዳንዱ በተደራራቢነት ለተፈፀመው ወንጀል

ተገቢ የሆነው ቅጣት ተወስኖ ሁሉም እንዲደመር ይደረጋል፡፡ ሆኖም ምንጊዜም ቢሆን ለእስራቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተደነገገው ጣራ ቅጣት ማለፍ አይቻልም/አንቀጽ 184/1//ለ/፡፡

አንድ ሰው የፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች ከፊሎቹ የሚያስቀጡት በቀላል እስራት ከፊሎቹ ደግሞ በፅኑ እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች በሚሆኑበት ጊዜ የቅጣት አወሳሰኑ በምን ዓይነት መንገድ እንደሚሰላ በአዲሱ የወንጀል ሕግ ላይ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ይኸውም እንዲህ ዓይነት ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ ቅጣቶችን ለመደመር እንዲያመች ሁለት ዓመት ቀላል እስራት እንደ አንድ ዓመት ፅኑ እስራት ይቆጠራል፡፡ ይህ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ላይ በፅኑ እስራትና በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ተደራርበው /ተቀላቅለው/ ከተገኙ የእስራት ቅጣቶችን ለመደመር እንዴት እንደሚቻል የሚያመለክተው ድንጋጌ በ1949 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ላይ ያልነበረ አዲስ የተጨመረ ሲሆን የቀድሞው ሕግ በግልፅ የደነገገው ነገር ባለመኖሩ ምክንያት የነበረውን የተዘበራረቀ አሰራር ወጥ በሆነ አሰራር እንዲተካ የሚያደርግ ነው፡፡

ሐ. <u>ሁለት ወይም ከዚያ የሚበልጡ በገንዘብ የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲያጋጥሙ፣</u> /አንቀጽ 184/1//መ/

አንድ ሰው የፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች በገንዘብ ቅጣት (በመቀጮ) የሚያስቀጡ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች የሆኑ እንደሆነ ወይም ከሌሎች ቅጣት ጋር ተጣምረው ለተደራራቢ ወንጀሎቹ የገንዘብ ቅጣቶች በጥፋተኛው ላይ የሚጣሉ በሚሆንበት ጊዜ ለእያንዳንዱ በተደራራቢነት ለተፈፀመው ወንጀል ተገቢ የሆነው የገንዘብ ቅጣት ተወስኖ ሁሉም ይደመራል፡፡ ሆኖም ወንጀሉ በአፍቅሮ ንዋይ የተፈፀመ ካልሆነ በቀር ምንጊዜም ቢሆን በወንጀለኛው ላይ የሚጣለው የመቀጮ ቅጣት አጠቃላይ ድምር በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተመለከተው ከፍተኛ የገንዘብ ቅጣት ወሠን ማለፍ አይችልም፡፡

የመውረስና የገንዘብ መቀጮ በሚያጋጥምበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ሊከተለው የሚገባው የቅጣት አወሳሰን ዘዴ ምን ሊሆን ይገባል የሚለውን በተመለከተ በቀድሞውም ሆነ በአዲሱ የወንጀል ሕግ የተካተተው ሀሳብ ተመሳሳይ ነው፡፡ ከተደራራቢዎቹ ወንጀሎች

በአንዱ ምክንያት የተቀጪው ንብረት እንዲወረስ ከተወሰነ በሌላው ወንጀል ምክንያት መቀጮ በተጨማሪ ሊወሠን አይችልም /ቁጥር 189(ሠ)፣ አንቀጽ 184(1)(ሠ)/

በዚህም መሠረት ጥፋተኛው ከፈፀማቸው ተደራራቢዎቹ ወንጀሎች ውስጥ በአንደኛው ወንጀል ምክንያት ከሚፈረድበት ከዋናው ቅጣት በተጨማሪ የወንጀለኛው ንብረት እንዲወረስ ከተፈረደበት በሌሎች ተደራቢ ወንጀሎች ምክንያት የገንዘብ መቀጮ መፍረድ አይቻልም ማለት ነው፡፡

መ. <u>ጣምራ ተደራራቢ ወንጀሎች በሚፈፀሙበት ጊዜ</u>

በአዲሱ የወንጀል ሕግ መሠረት አንድ ሰው በአንድ ድርጊት የሚጥሰው አንድን የሕግ ድንጋጌ ብቻ ቢሆንም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ካደረሰ ተደራራቢ ወንጀሎችን እንደፈፀመ እንደሚቆጠር በአንቀጽ 60(ሐ) ላይ ተደንግጓል፡፡ ቅጣቱ የሚወሰነውም በሌላ አካኋን ካልተደነገገ በቀር ከዚህ በላይ በተጠቀሠው ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች በሚፈፀሙበት ጊዜ ቅጣት በሚወሰንበት መንገድ ነው (አንቀጽ 184(2))፡፡

- በአንድ ድርጊት የተደራረቡ ጣምራ ወንጀሎች የፈፀመ ቢሆንም የጉዳዩን አካባቢ ሁኔታዎች በመመርመር ፡-
  - ጣምራ ወንጀሎቹን የፈፀመው ከዚህ በታች ከተጠቀሰው ሁኔታ ውጭ ከሆነ በሕጉ ልዩ ክፍል ለከባዱ ወንጀል የተደነገገውን ከፍተኛ ቅጣት ወሰን ባለማለፍ ፍርድ ቤቱ ቅጣትን አክብዶ ይወስናል (አንቀጽ 187(1))፡፡
  - ወንጀለኛው አስቦና አቅዶ ሕጉን ጥሶ ከሆነ ወይም ግልፅ የሆነ መጥፎ ፀባይ አሳይቶ እንደሆነ ግን በአንቀጽ 184 መሰረት ማለትም ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች በሚፈፀሙበት ጊዜ ቅጣት በሚወሰንበት መንገድ ቅጣቱ ከብዶ ይወሰንበታል፣

- ግዙፍ ውጤት የሚያስከትሉ ጣምራ ወንጀሎች ተፈፅመው በተገኙ ጊዜ ግን፡-

- ጥፋተኛው ከተደራራቢ ጣምራ ወንጀሎች ውስጥ ቢያንስ አንደኛውን አስቦ ያደረገ እንደሆነ በአንቀጽ 184 መሰረት ማለትም ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች በሚፈፀሙበት ጊዜ ቅጣት በሚወሰንበት መንገድ ቅጣቱ ከብዶ ይወሰንበታል (አንቀጽ 187/2/ሀ)፣
- ጥፋተኛው ጣምራ ወንጀሎቹን የፈፀመው በቸልተኛነት ከሆነ በሕጉ ልዩ ክፍል ለከባዱ ወንጀል ከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ወሰን ባለማለፍ ይወሰንበታል (አንቀጽ 187/2/ለ)፣

ሠ. <u>የተዛመዱ ወንጀሎች በተፈፀሙ ጊዜ</u>

የተዛመዱ ወይም የተቀራረቡ ወንጀሎች ተፈፀሙ የሚባለው አንዱ የተደረገው ሌላው ወንጀል እንዲፈፀም ለማድረግ፤ ወይም ለማመቻቸት ወይም ለሌላው ከለላ እንዲሆን ለማድረግ ታስቦ ሲሆን ነው (አንቀጽ 63)። በመርህ ደረጃ የተዛመዱ ወንጀሎች በተፈፀሙ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ቅጣትን የሚወስነው በአንቀጽ 184 መሰረት ማለትም ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች በሚፈፀሙበት ጊዜ ቅጣት በሚወሰንበት መንገድ ነው /አንቀጽ 185/1//።

ሆኖም አንዳንድ ጊዜ የተዛመዱ ወንጀሎች እንደ አንድ ነጠላ ወንጀል የሚቆጠሩበት ሁኔታ አለ። ይህም የሚሆነው ወንጀል ፈጻሚው ዋናውን ወንጀል እግብ ለማድረስ ሲል ሌላ ወንጀል የፈፀመ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ሕግ አውጭው አጥፊው ለዋናው ወንጀል ብቻ ተጠያቂ እንዲሆን በሚደነግግበት ጊዜ ወይም ተዛማጅ ወንጀሎችን እንደ አንድ ነጠላ ወንጀል በመውሰድ የሚደነግግ በወንጀል ሕጉ ውስጥ አንድ ድንጋጌ በሚኖርበት ጊዜ ነው። እንዲህ በሚሆንበት ለምሳሌ እንደ ከባድ ግድያ ወይም ከባድ ውንብድና የመሳሰሉ /የተዛመዱ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች/ ቅጣት የሚያከብዱ አንድ ወንጀልን የሚያቋቁሙ መሆናቸው በሕጉ ልዩ ክፍል በተደነገገ ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆነው ለእነዚሁ ወንጀሎች የተመለከቱት ድንጋጌዎች ናቸው።

ረ. <u>ተነጣጥለው ተሠጥተው የነበሩ ውሳኔዎችን ስለማጣመር</u>

ጥፋተኛው ተፈርዶበት ቅጣቱን በመፈፀም ላይ ሳለ ወይም ከፈፀመ በኋላ ከፍርዱ በፊት የፈፀመው ተደራቢ ወንጀል መኖሩ ሲደረስበት ተደራቢው ወንጀል አስቀድሞ ቢታወቅ ሊወሰንበት ይችል ከነበረው ቅጣት ሳያልፍ ይወሰናል (አንቀጽ 186(1))። ከአንድ ፍርድ በፊት የተፈፀመ ሌላ ወንጀል ተደራራቢ ወንጀል በሚለው የሚሸፈን ሲሆን ከፍርድ በኋላ የሚፈፀም ሌላ ወንጀል ግን እንደ ሁኔታው ደጋጋሚ ወንጀለኛ በሚለው ነው ሊሸፈን የሚችለው።

ተጣምረው መታየት የነበረባቸው ወንጀሎች በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ወይም በተለያዩ ችሎቶች ታይተው ውሳኔ አግኝተው ከሆነ የጠቅላላ ቅጣቱ አወሳሰን ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል /አንቀጽ 186//3//። በተመሳሳይ ወቅት ማለትም ሁለተኛው ወንጀል የተፈፀመው በአንደኛው ወንጀል ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ከሆነ ወንጀሎችቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ናቸው። ስለዚህ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ወይም በተለያዩ ችሎቶች ታይተው ቢሆን አንኳን በተናጠል ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ እንደገና በአንድነት ታይቶ ተደራራቢ ወንጀሎች በሚወሰኑበት መንገድ ቅጣቱ ሊወሰን ይገባል።

4. ቅጣትን ስለማክበድና ስለማቅለል

አንድ ፍርድ ቤት ቅጣትን በሚወስንበት ጊዜ ግምት ውስጥ ማስገባት የሚኖርበት ሕጉ የደነገጋቸው የማቅለያ ወይም የማክበጃ ምክንያቶች አሉ።

4.1. የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች እና የቅጣት አወሳሰን

እነዚህ ምክንያቶች በጠቅላላና በልዩ ሁኔታ ቅጣት የሚያከብዱ ምክንያቶች ተብለው የተከፋፈሉ ናቸው።

4.1.1. ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች እና የቅጣት አወሳሰን

በልዩ ሁኔታ ቅጣትን ለማክበድ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ተብለው በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግም ሆነ በአዲሱ የወንጀል ሕግ የተጠቀሱት ምክንያቶች ተደራራቢ ወንጀሎች እና ደጋጋሚነት /ደጋጋሚ ወንጀለኛነት/ ናቸው።

የወንጀሎች መደራረብ አለ የሚባለው ምን ዓይነት ሁኔታዎች በሚኖሩበት ጊዜ እንደሆነ አንዲሁም አንድ ሰው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ነው በወንጀል ሕጋችን መሠረት የሚባለው ምን ምን ሁኔታዎች ሲሟሉ እንደሆነ እና የቅጣት አወሳሰኑ በቀድሞው ሕግም ሆነ በአዲሱ የወንጀል ሕግ ምን እንደሚመስል "ደጋጋሚነት፣ ተደራራቢ ወንጀሎች እና የቅጣት አወሳሰን" በሚለው የዚህ ጽሑፍ ክፍል ውስጥ የቀረበ በመሆኑ እዚህ ላይ በድጋሚ መግለፁ አላስፈላጊ ነው። ከልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች አንጻር ሊሰመር የሚገባው ነጥብ ቢኖር እነዚህ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ አንድ ሰው ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘበት በሕጉ ልዩ ክፍል ውስጥ በተደነገገው የቅጣት ጣራ ሳይገደብ ቅጣት በአጥፊው ላይ ሊወስን የሚችል መሆኑ ነው። እንደሚታወቀው በመርህ ደረጃ አንድ ሰው ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘበት የሕጉ ልዩ ክፍል ድንጋጌ ላይ ከተጠቀሰው ቅጣት ወለል በታች ወይም ደግም ከተደነገገው ቅጣት ጣራ በላይ ሊቀጣ አይችልም። ይሁን እንጅ ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ይህ ለመደበኛ ሁኔታ አግባብነት ያለው መርህ ተፈጻሚነት የለውም።

4.1.2. ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች እና የቅጣት አወሳሰን

ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን አስመለክቶ በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 81 ድንጋጌ ላይ ተመልክተው የነበሩት ጉዳዮች የተወሰነ ማሻሻያ ተደርጎባቸው የአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 84 ድንጋጌ ሆነው ተካተዋል። ጠቅላላ የቅጣት የማክበጃ ምክንያቶች የሚባሉት ተከሳሹ ወንጀሉን የፈፀመው በጨካኝነት፣ በከሀዲነት፣ በወስላታነት፣ በወራዳነት፣ መጥፎ አመልን በሚያሳይ ምቀኝነት፣ በጥላቻ፣ በክፋት የሆነ እንደሆነ፣ ወንጀለኛው ወንጀል ማድረግን ሙያ ወይም ልማድ አድርጎ ይዞ እንደሆነ፣ የወንጀሉ አፈጻጸም ዘዴ፣ወንጀሉ የተፈፀመበት ጊዜ፣ ቦታና የአፈጻጸሙ

አካኋን የወንጀለኛውን አደገኛነት የሚያሳይ የሆነ እንደሆነ፣ ወንጀሉ የተፈፀመው ወንጀል ለመፈፀም ስምምነት ባደረጉ ሰዎች ወይም ቡድኖች ሲሆን፣ ወንጀሉ የተፈፀመው በተለያዩ ምክንያት ጥበቃ ወይም እንክብካቤ በሚሹ ሰዎች ላይ ሲሆን፣ ወ.ዘ.ተ. ነው።

በአዲሱ የወንጀል ሕግ የተደረጉትን መሻሻሎች ስንመለከት በወንጀል ሕጉ ሐተታ ዘምክንያት ላይ በትክክል እንደተገለፀው መሠረታዊ የሚባሉ አይደሉም። የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል "ስግብግብነት" የሚል ቀደም ሲል ያልነበረ ተጨምሯል፣ "ከወንበዴዎች ጋር ማህበርተኛ በመሆን" ወንጀሉ ተፈፅሞ ከሆነ ይል የነበረው "ወንጀል ለመስራት ከተቋቋመ ቡድን ጋር በመስማማት" በሚል ተተክቷል፣ ወንጀሉ የተፈፀመው "ወደታች የሚቆጠር ተወላጅ ወይም ወደ ላይ የሚቆጠር ወላጅ ከሆነ ሰው ላይ ከሆነ" ይል የነበረው "በቅርብ ዘመዱ" ላይ የሆነ እንደሆነ በሚል ተተክቷል። "በሕገ መንግስት በተቋቋመ ባለሥልጣን" ላይ እንደሆነ ይል የነበረው "በሕግ በተቋቋመ ባለሥልጣን" ላይ እንደሆነ በሚል ተተክቷል። ወንጀሉ "በሀይማኖት ባለሥልጣን" ላይ የተፈጸመ እንደሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ መሠረት ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ተደርጎ ይቆጠር የነበረ ሲሆን ከአዲሱ የወንጀል ሕግ ላይ ግን ተሰርዟል።

ከጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች አንጻር ልብ ሊባሉ የሚገባቸው ሦስት የሚሆኑ ነጥቦች አሉ። እነርሱም፡-

1. ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ተብለው በሕጉ የተጠቀሱት ሁኔታዎች በሕጉ ልዩ ክፍል ለአንድ ለሆነ ወንጀል ማቋቋሚያ ወይም ለቅጣት ማክበጃ ምክንያት ተደርገው በተመለከቱ ጊዜ የወንጀሉን ቅጣት ዳግመኛ ለማክበድ ተፈፃሚ አይሆኑም (አንቀጽ 84(2))። ማለትም አንድ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ከአንድ ጊዜ በላይ ወይም ዳግመኛ ቅጣቱን ሊያከብድ አይችልም። ለምሳሌ "ጨካኝነት" ጠቅላላ ቅጣትን ከሚያከብዱ ምክንያቶች አንዱ ነው። ይህ ቃል በሕጉ ልዩ ክፍል ወንጀሉን ከሚያቋቋሙት ሁኔታዎች አንዱ ሆኖ ወንጀለኛው በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ቅጣት በሚወሰንበት ጊዜ በሕጉ

ጠቅላላ ክፍል የተመለከተው “ጨካኝነት” ዳግመኛ ግምት ውስጥ ገብቶ ቅጣቱ ሊከብድበት አይችልም።

2. ወንጀልን ሙያ ወይም ልማድ አድርጐ መያዝ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ላያሰኝ ይችላል። በዚህ ጊዜ ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት አይሆንም። ነገር ግን ቅጣትን ከሚያከብዱ ጠቅላላ ምክንያቶች እንደ አንዱ ተደርጐ ተወስዷል (አንቀጽ 84(1)(ሐ))።

3. በሕጉ በግልፅ ከተመለከቱት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ውጭ ፍርድ ቤቶች ሌሎች ሁኔታዎችንም የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች አድርገው ሊቆጥሩ ይችላሉ (አንቀጽ 86)። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ግን፦

    1. ለምን በቂ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት አድርጐ ፍርድ ቤቱ እንደተቀበለው በውሳኔው ላይ መግለፅ አለበት፣
    2. ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት እንጂ ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ፍርድ ቤቱ ሊፈጥር አይችልም።

ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት በሚኖርበት ጊዜ ያለውን የቅጣት አወሳሰን በተመለከተ የቅጣት ማክበጃ ጠቅላላ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ የምክንያቶችን ዓይነትና ብዛት፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነት /የቀድሞው ሕግ ትልቅነት ይል ነበር/ ግምት ውስጥ በማስገባት ለወንጀሉ በሕጉ ልዩ ክፍል የተደነገገውን ከፍተኛ የቅጣት ጣራ ሳያልፍ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ማክበድ ይችላል (አንቀጽ 183)። በዚህም መሠረት አንድ ሰው በፈፀመው አንድ ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ሆኖ ተገኝቶ ቅጣቱ በሚወሰንበት ወቅት የቱንም ያህል ብዛት ያላቸው ወይም ክብደታቸው ከፍተኛ የሆነ ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ቢኖሩም በአጥፊው ላይ የሚወሰነው ቅጣት ተከሳሹ ጥፋተኛ በተባለበት አንቀጽ ከተደነገገው ከፍተኛ የቅጣት ጣራ ሊያልፍ አይችልም።

4.2. <u>የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች እና የቅጣት አወሳሰን</u>

የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችንም እንዲሁ በሁለት ከፍሎ ማየት ይችላል፡፡

1. ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች፣እና
2. ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች

4.2.1.<u>ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች እና የቅጣት አወሳሰን</u>

/አንቀጽ 83፣ ቁጥር 80/

በልዩ ሁኔታ ቅጣትን ለማቅለል የሚያስችሉ ሁኔታዎች ተብለው በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 80 እንዲሁም በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 83 ላይ በግልፅ የተጠቀሱት ምክንያቶች ዝምድናና የጠበቀ ወዳጅነት ቢሆኑም በሕጉ ልዩ ክፍል ውስጥ ፍርድ ቤቱ በመሠለው ቅጣት ማቅለል ይችላል የተባለባቸው ምክንያቶች ሁሉ ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ናቸው (አንቀጽ 83(1))፡፡

የወንጀል ሕጉ ዝምድና ለአንዳንድ ዓይነት ወንጀሎች እንደ ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ተደርጎ እንደሚወሰድ የደነገገ ቢሆንም የዝምድናውን ደረጃ በግልፅ አላመለከተም፡፡ ነገር ግን ዝምድና አለ የሚባለው መቼ ነው የሚለውን በተመለከተ ሕግ አውጭው ያለውን አቋም ለመረዳት በቤተሰብ ሕጉ ላይ የተደነገገው የዝምድና ግንኙነት መመዘኛ ለዚህ ጉዳይ ሊያገለግል ይችላል፡፡

“የጠበቀ ወዳጅነት” የሚለውም እንደዚሁ በሕጉ ትርጉም ያልተሰጠው ጉዳይ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ የተለያዩ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ግንኙነቱ በቂ ምክንያት ተደርጐ ሊቆጠር የሚችል መሆን አለመሆኑን እንደሚወስን መረዳት ይቻላል፡፡

ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ያለውን የቅጣት አወሳሰን በተመለከተ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 83(2) እና 122 ላይ እንደተመለከተው የወንጀለኛው ጥፋት በጣም ከባድ ካልሆነና የዝምድና ወይም የወዳጅነት ትስስሩ /ግንኙነቱ/ እጅግ ጥብቅ ከሆነ ወንጀለኛውን በማስጠንቀቅ ወይም በወቀሳ ብቻ ፍርድ ቤቱ ሊያልፈው ይችላል ፡፡ ከዚህ ውጭ ባሉ ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ግን ፍርድ ቤቱ

በመሠለው ቅጣትን ማቅለል የሚችል ቢሆንም የሚወሰነው ቅጣት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ለየቅጣቱ ዓይነት ከተደነገገው መነሻ ቅጣት ዝቅ ሊል አይችልም /የቀድሞው ቁጥር 185፣አዲሱ አንቀጽ 180/። ይህም ማለት፡-

- የገንዘብ ቅጣት በአንቀጽ 90 መሠረት ከብር አስር ሊያንስ አይችልም።
- የቀላል እስራት ቅጣት በአንቀጽ 106 መሠረት ከአስር ቀን ሊያንስ አይችልም፣
- የፅኑ እስራት ቅጣት በአንቀጽ 108 መሠረት ከአንድ ዓመት ሊያንስ አይችልም።

4.2.2. <u>ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች እና የቅጣት አወሳሰን</u> /የድሮው 79፣አዲሱ 82

ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን አስመለክቶ በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 79 ድንጋጌ ላይ ተመልክተው የነበሩት ጉዳዮች የተወሰነ ማሻሻያ ተደርጎባቸው የአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 82 ድንጋጌ ሆነው ተካተዋል። ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች የሚባሉት የወንጀለኛው የዘወትር ጠባይ መልካም ሆኖ ያጠፋው በዕውቀት ማነስ፣ ባለማወቅ፣ በየዋህነት፣ ወይም ባለታሰበ ድንገተኛ አጋጣሚ፣ ወንጀለኛው ወንጀሉን የፈፀመው በተከበረና በግል ጥቅም ላይ ባልተመሰረተ ምክንያት መሆን፣ ወይም ከፍተኛ ቁሳዊ እጦት ወይም የሕሊና ስቃይ ስለደረሰበት መሆን፣ወ.ዘ.ተ. ነው።

በአዲሱ የወንጀል ሕግ የተደረጉትን መሻሻሎች ስንመለከት መሠረታዊ የሚባሉ አይደሉም ማለትም በቀድሞው ሕግ ላይ የተመለከቱት የተወሰነ ማሻሻያ ብቻ ነው የተደረገባቸው። የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል "እጅን ለፍርድ ባለሥልጣን ከሰጠ በቅጣት ማቅለያነት እንደሚያዝለት የቀድሞው የወንጀል ሕግ ተገልፆ የነበረው ሰፋ ተደርጎ "እራሱን ለፍትሕ አካላት ካቀረበ" በሚል የተተካ ሲሆን ወንጀለኛው ተከስሶ ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ በክስ ማመልከቻው ላይ የተመለከተውን የወንጀል ዝርዝር በሙሉ ያመነ እንደሆነ በቅጣት ማቅለያነት ይያዝለታል የሚል አዲስ ሀረግ ተጨምሮበታል።

ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ተብለው በሕጉ የተጠቀሱት ሁኔታዎች በሕጉ ልዩ ክፍል በማቅለያነት በተመለከቱ ጊዜ ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያዎች የወንጀሉን ቅጣት ለማቅለል ዳግመኛ ተፈፃሚ አይሆኑም፡፡ በዚህም መሠረት አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ከአንድ ጊዜ በላይ ወይም ዳግመኛ ቅጣትን ሊያቀል አይችልም ማለት ነው፡፡

እንዲሁም በሕጉ በግልፅ ከተመለከቱት ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ውጭ ፍርድ ቤቶች ሌሎች ሁኔታዎችንም የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች አድርገው ሊቆጥሩ ይችላሉ /አንቀጽ 86/፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ግን፡-

1. ለምን በቂ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አድርጐ እንደተቀበለው ፍርድ ቤቱ በውሳኔው ላይ መግለፅ አለበት፣
2. ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን እንጂ ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን ፍርድ ቤቱ ሊፈጥር አይችልም፡፡

ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ያለውን የቅጣት አወሳሰን በተመለከተ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 184 እንዲሁም በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 179 ላይ እንደተመለከተው ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ እንደ ነገሩ ሁኔታ የቅጣቱ ዓይነት ወይም የቅጣቱ መጠን ይቀየራል፡፡ ለምሳሌ፡-

- በሞት ቅጣት ምትክ- ከ20 ዓመት እስከ ዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት/179/ሀ//- እዚህ ላይ የተቀየረው የቅጣቱ ዓይነት ነው
- በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ምትክ ከ10 ዓመት እስከ 20 ዓመት ፅኑ እስራት-እዚህ ላይ የቅጣቱ ዓይነት አልተቀየረም ማለትም የተቀየረው የቅጣቱ መጠን ነው፡፡
- መነሻው አንድ ዓመት በሆነ ፅኑ እስራት ምትክ ከ6 ወር እስክ 5 ዓመት የሚደርስ ቀላል እስራት፣
- ከአስር ቀን በማያንስ የቀላል እስራት ቅጣት ምትክ የግዳጅ ሥራ ወይም መቀጮ፣

ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ይወስናል፡፡

4.3. <u>የልዩ ልዩ ቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶች መደራረብ</u>

ቅጣትን የሚያቃልሉና የሚያከብዱ ልዩ ልዩ ሁኔታዎች በአንድነት ሲገኙ ቅጣት የሚወሰነው እንዴት ነው የሚለውን በተመለከተ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 189 ስር በምን መልኩ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን እንደሚወስን ተመልክተው እናገኛቸዋለን፡፡ ይኸውም፡-

1. የተደራረቡት ቅጣትን የሚያከብዱና የሚያቃልሉ ጠቅላላ ምክንያቶች ከሆኑ ፍርድ ቤቱ፣
    - አስቀድሞ የሚያከብዱ ጠቅላላ ምክንያቶችን ግምት ውስጥ አስገብቶ ቅጣቱን ያከብዳል፣
    - በመቀጠል የሚያቃልሉትን ጠቅላላ ምክንያቶች መሠረት አድርጎ ቅጣቱን ይቀንሳል/አንቀጽ 189/1/፣ቁጥር 84/

2. የተደራረቡት ደጋጋሚ ወንጀለኛነት እና ተደራራቢ ወንጀሎች ከሆኑ /ማለትም ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በአንድነት ከተገኙ/ ፍርድ ቤቱ፡-
    - አስቀድሞ ለተደራረቡት ወንጀሎች ቅጣትን ይወስናል፣
    - በመቀጠል ደግሞ ደጋጋሚ ወንጀለኛ መሆኑን ግምት ውስጥ አስገብቶ ቅጣቱን ያከብዳል/አንቀጽ 189(2)፣ ቁጥር 82(2)/

2. የተደራረቡት ሁሉም ዓይነት የማክበጃና የማቅለያ ምክንያቶች የሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ፡-
    - በመጀመሪያ የማክበጃ ምክንያቶችን መሠረት በማድረግ ቅጣቱን ያከብዳል፣
    - ቀጥሎ ደግሞ የማቅለያ ምክንያቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት ቅጣቱን ይቀንሳል /አንቀጽ 189/3//- በድሮው ሕግ ላይ ያልነበረ ድንጋጌ ነው፡፡

5. የወንጀል ጉዳዮች የይርጋ ጊዜ ገደብ

በወንጀል ጉዳይ የግል አቤቱታ ወይም ክስ የማቅረብ እና ጉዳዩን በዳኝነት የማየት እንዲሁም ቅጣትን ተፈጻሚ እንዲሆን የማድረግ እንቅስቃሴዎች በጊዜ የተገደቡ ናቸው። ይህ የጊዜ ገደብ እንደ ወንጀሉ ከባድነት የሚለያይ ሲሆን "ይርጋ" ተብሎ ይጠራል። የክስ ይርጋ የወንጀል ድርጊት ፈጽሚል ተብሎ የተጠረጠረ ሰው የወንጀል ክስ ቀርቦበት ጉዳዩ በዳኝነት ሳይታይ የተወሰነ ጊዜ ካለፈ ሊከሰስ የማይችል ስለመሆኑ የሚደነግግ ሲሆን የቅጣት ይርጋ ደግሞ ቅጣት የተፈረደበት ሰው ቅጣቱ ተፈፃሚ ሳይሆንበት የተወሠነ ጊዜ ካለፈ ሊቀጣ እንደማይችል የሚደነግግ ነው።

ይርጋ የወንጀል ክስም ሆነ ቅጣት ቀሪ እንዲሆኑ የማድረግ ውጤት ቢኖረውም በአንዳንድ የወንጀል ጉዳዮች ዙሪያ እንዲህ ዓይነት አሰራሮችን በመከተል ወንጀል አድራጊዎች ከቅጣት እንዲያመልጡ ማድረግ በሕብረተሰቡ መብትና ጥቅም ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል ተብሎ ይታመናል። በዚህም ምክንያት አንዳንድ የወንጀል ዓይነቶች ይርጋ አይኖራቸውም። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 28 ላይ እንደተደነገገው በስብዕና ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች በይርጋ አይታገዱም። ይህን ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ግምት ውስጥ በማስገባትም በስብዕና ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች በይርጋ ቀሪ ሊሆኑ እንደማይችሉ ለማመልከት "በሕግ በሌላ አካኋን በግልፅ ካልተደነገገ በስተቀር" የሚል ሀረግ በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 216 እና 223 ስር እንዲገባ ተደርጓል።

5.1. የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ጊዜ

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው የክስ ይርጋ የወንጀል ድርጊት ፈጽሚል ተብሎ የተጠረጠረ ሰው የወንጀል ክስ ቀርቦበት ጉዳዩ በዳኝነት ሳይታይ የተወሰነ ጊዜ ካለፈ ሊከሰስ የማይችል ስለመሆኑ የሚደነግግ ሲሆን የይርጋ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው የወንጀል ድርጊቱ ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ ነው። ሆኖም ወንጀሉ በተለያዩ ጊዜያት የተፈፀመ ከሆነ የይርጋ ዘመኑ መቆጠር የሚጀምረው የመጨረሻው ድርጊት

ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ ሲሆን ወንጀሉ ለረጅም ጊዜ ሲፈፀም የቆዬ ከሆነ ደግሞ መቆጠር የሚጀምረው የወንጀል ድርጊቱ መፈፀም ካቆመበት ቀን ጀምሮ ነው።

የይርጋ ዘመን የሚቆጠረው የቅጣት ማቅለያ እና ማክበጃ ምክንያቶች ግምት ውስጥ ሳይገቡ ለተፈፀመው ወንጀል በሕጉ ልዩ ክፍል የተደነገገውን ከፍተኛ ቅጣት መሰረት በማድረግ ነው። ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈፅመው በሚገኙበት ጊዜ የክስ ማቅረቢያው ጊዜ የሚወሰነው የተደራራቢዎች ወንጀሎች የቅጣት ጣራ ተመሳሳይ ከሆነ የአንደኛው ወንጀል የክስ ማቅረቢያ ዘመን ለሌሎቹ ወንጀሎች ተፈፃሚ የሚደረግ ሲሆን የተደራራቢዎቹ ወንጀሎች ቅጣት ጣራ የተለያዬ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ የከባዱ ወንጀል የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን በሌሎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል። በዚህም መሠረት የአንዱ ተመሳሳይ ወንጀል ወይም ከተደራራቢ ወንጀሎች ከባድ የሆነው ወንጀል የክስ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ምክንያት የይርጋ ጊዜው እንዲራዘም አይደረግም ማለት ነው። የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ተከሣሹ ተደራራቢ ወንጀሎችን ፈፅሞ ከሆነ የይርጋ ጊዜው የሚወሰነው እንዴት እንደሆነ አይደነግግም ነበር።

የይርጋ ዘመን መቆጠር ከጀመረ በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ሊታገድ ወይም ሊቋረጥ ይችላል። ከወንጀለኛው ድርጊት ሌላ ክስ እንዳይቀርብ ወይም እንዳይቀጥል የሚያደርጉ መሰናክሎች ሲከሰቱ የይርጋ ዘመን መቆጠር ይታገዳል። እነዚህ መሰናክሎች የህግ ወይም የፍሬ ነገር (የሁኔታ) መሰናክሎች ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ ተከሳሹ ያለ መከሰስ መብት ያለው ቢሆን (ሕጋዊ መሰናክል) ወይም ደግሞ ተከሳሹ በፅኑ ቢታመም (የፍሬ ነገር መሰናክል) ይህ መሰናክል እስኪወገድ ድረስ የይርጋ ዘመን መቆጠሩ ታግዶ የሚቆይ ሲሆን መሰናክሉ እንደተወገደ መቆጠር ይጀምራል። ይህም በሚሆንበት ጊዜ መሰናክሉ ከመከሰቱ በፊት የተቆጠረው ጊዜ ከቀሪው ዘመን ጋር እንዲታሰብ ይደረጋል።

በሌላ በኩል ወንጀለኛውን ለመያዝ፣ ለወንጀለኛው መጥሪያ ለመስጠት ወይም የተፈፀመውን ወንጀል ለመመርመር የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ይርጋን የሚያቋርጡ ሲሆን እነዚህ ተከሳሹ ለፈፀመው የወንጀል ድርጊት ተገቢውን ፍርድ እንዲያገኝ ለማስቻል የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ሲቆሙ የይርጋ ዘመኑ እንደገና መቆጠር

ይጀምራል። ሆኖም በተቋረጠ ቁጥር መቆጠር የሚጀምረው እንደገና እንደ አዲስ ነው። ስለዚህም የይርጋ ጊዜው እንዲቋረጥ ያደረገው ምክንያት ከተከሰተበት ቀን በፊት ተቆጥሮ የነበረው የይርጋ ዘመን እንዳልነበረ ይቆጠራል።

5.2. <u>የቅጣት የይርጋ ጊዜ</u>

ከላይ እንደተገለፀው የቅጣት ይርጋ ቅጣት የተፈረደበት ሰው ቅጣቱ ተፈፃሚ ሳይሆንበት የተወሠነ ጊዜ ካለፈ ሊቀጣ እንደማይችል የሚደነግግ ነው። የቅጣት ይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው በወንጀለኛው ላይ የተወሰነው ፍርድ ተፈጻሚ መሆን ይችል ከነበረበት፣ ፍርዱ መፈፀም ጀምሮ የነበረ እንደሆነ ተቀጪው ፍርዱ እንዳይፈፀምበት ካመለጠበት ወይም ወንጀለኛው ፍርዱ ታግዶለት የነበረ ከሆነና የማገድ ትእዛዙ ተሽሮ ከሆነ የቅጣቱ አፈጻጸም እንዲቀጥል ከተወሰነበት ጊዜ ጀምሮ ነው። ከአንድ በላይ ቅጣት በወንጀለኛው ላይ ተወስኖበት ከሆነ የይርጋ ጊዜው የሚሰላው ከሁሉም ቅጣቶች ከባድ የሆነው ቅጣት የሚኖረውን የይርጋ ጊዜ በመውሰድ ነው።

የቅጣት ይርጋ ዘመን መቆጠር ከጀመረ በኋላም እንዲሁ በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ሊታገድ ወይም ሊቋረጥ ይችላል። በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 227 ላይ እንደተመለከተው በወንጀለኛው ላይ የተጣለውን ቅጣት የማስፈፀም ኃላፊነት ባለው አካል ቅጣቱን ለማስፈፀም የሚደረግ ማናቸውም ተግባር የቅጣት ይርጋ ዘመኑ መቆጠር እንዲቋረጥ የማድረግ ውጤት አለው።

በሌላ በኩል የቅጣት ይርጋ መቆጠር ታግዶ የሚቆይባቸው ሁኔታዎች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 226 ላይ ተመልክተዋል። እነርሱም፡-

- በወንጀለኛው ላይ የተጣለው ቅጣት እንዳይፈፀም ወይም አፈፃፀሙ ተጀምሮ ከሆነ እንዳይቀጥል የሚያደርግ ምክንያት ተከስቶ ከሆነ ይህ መሰናክሉ እስኪወገድ ድረስ፣
- በተቀጪው ላይ የተጣለው ቅጣት ታግዶ፣ በአመክሮ ተፈትቶ ፣ የዕዳ መክፈያ ጊዜ ተሰጥቶት ከሆነ ይህ የተሰጠው ጊዜ እስኪያልቅ፣
- ተቀጪው ታስሮ ከሆነ እስሩ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ

የቅጣት የይርጋ ዘመን መቆጠሩ ታግዶ ይቆያል።

የጥንቃቄ እርምጃዎች ያለ ዋነኛ ቅጣት በሚወሰኑበት ጊዜ በይርጋ ቀሪ ሊሆኑ የሚችሉበት ዘመን በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ አልተመለከተም ነበር። አሁን ግን በአዱሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 224(1) ስር እንዲገባ ተደርጓል። በዚህም መሰረት የጥንቃቄ እርምጃዎች መደበኛ የቅጣት ይርጋ ዘመን አምስት ዓመት ሆኗል።

5.3. <u>የመደበኛ እና ፍፁም የይርጋ ጊዜ ልዩነት</u>

ለወንጀል ጉዳዮች ተፈጻሚ የሚሆነው የይርጋ ጊዜ ሁለት ዓይነት ነው። አንደኛው መደበኛ የይርጋ ዘመን የሚባለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ፍፁም የሆነ የይርጋ ዘመን የሚባለው ነው።

ከዚህ በላይ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የይርጋ መቆጠርን የሚያግዱ ወይም የሚያቋርጡ ሁኔታዎች ስለመኖራቸው ተመልክተናል። እነዚህ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ የይርጋ መቆጠር ታግዶ ወይም ተቋርጦ የሚቆይ ሲሆን ሁኔታዎቹ ሲወገዱ ወይም ሳይኖሩ ሲቀር ደግሞ የይርጋ ጊዜው መቆጠር እንደገና ይጀምራል። ነገር ግን እነዚህ ሁኔታዎች እንዲህ ዓይነት የማገድ ወይም የማቋረጥ ውጤት (effect) የሚኖራቸው በመደበኛው የይርጋ ጊዜ ላይ ነው። ፍፁም የሆነ ይርጋ መቆጠር ከጀመረ በኋላ በምንም ዓይነት ምክንያት ሊታገድ ወይም ሊቋረጥ አይችልም። በዚህም መሠረት ፍፁም የሆነ የይርጋ ጊዜ በሚቆጠርበት ጊዜ የይርጋ ዘመን መቆጠርን የሚያግዱ ወይም የሚያቋርጡ ሁኔታዎች በፍፁም ግምት ውስጥ አይገቡም።

ስለዚህም ክስ ወይም ቅጣት የታገደበት ወይም የተቋረጠበት ምክንያት ምንም ይሁን ምን ፍፁም የሆነው የይርጋ ዘመን ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ወንጀል በፈፀመ

ሰው ክስ መመስረትም ሆነ ቅጣት በተወሰነበት ሰው ላይ ፍርዱን እንዲፈፀም ማድረግ አይቻልም።[19]

የክስ ማቅረቢያ ፍፁም የሆነ የይርጋ ዘመን የመደበኛው የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን አጠፊታ ወይም በግል አቤቱታ የሚቀርብ የወንጀል ጉዳይ ዓይነት ሲሆን የግል አቤቱታ ልዩ የይርጋ ዘመን ከአጋማሽ የሚበልጥ ጊዜ ሲያልፍ ነው። ከዚህ አንጻር ለምሳሌ ከአንድ ዓመት በላይ ቀላል እስራት የማያስቀጣ ወንጀል መደበኛ የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን አምስት ዓመት ነው። ፍፁም የሆነ የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመኑ ግን የመደበኛው አጠፊታ ማለትም የአምስት ዓመት አጠፊታ ስለሚሆን አስር ዓመት ነው ማለት ነው። እንዲሁም ልዩ የግል አቤቱታ ማቅረቢያ መደበኛ የይርጋ ዘመን ሁለት ዓመት ነው። ልዩ የግል አቤቱታ ማቅረቢያ ፍፁም የሆነ የይርጋ ዘመኑ ግን የመደበኛው የይርጋ ዘመን ከአጋማሽ የሚበልጥ ጊዜ ሲያልፍ ማለትም የሁለት ዓመት አጋማሽ ሲያልፍ ስለሚሆን ሦስት ዓመት ነው ማለት ነው።

የቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃዎች ፍፁም የሆነ የይርጋ ዘመን አለፈ የሚባለው ከመደበኛው የቅጣት የይርጋ ዘመን በግማሽ የሚበልጥ ጊዜ ካለፈ ነው። በዚህም መሰረት ለምሳሌ ከአንድ ዓመት በላይ ከአስር ዓመት በታች ለሆነ ነጻነትን የሚያሳጣ ቅጣት የተደነገገው መደበኛ የቅጣት የይርጋ ዘመን አስር ዓመት ነው። በመሆኑም ለእንደዚህ ዓይነት ቅጣቶች የሚኖረው ፍፁም የሆነ የቅጣት የይርጋ ዘመን ከመደበኛው በግማሽ የሚበልጥ በመሆኑ ከአስር ዓመት በግማሽ የሚበልጥ ማለትም አስራ አምስት ዓመት ይሆናል ማለት ነው።

[19] ሆኖም ጥፋተኛው በፅኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል አስቦ በመፈፀም አደገኛ መሆኑን ካሳዬ ፍፁም የሆነው የቅጣት የይርጋ ዘመን ቢያልፍም ቅጣቱ ቀሪ ላይሆን እንደሚችል የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 228 ያመለክታል።

6. ቅጣትን መገደብ

6.1. ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠትና የጥፋተኝነት ውሳኔን መሰረዝ

በአንድ ተከሳሽ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ፍርድ ቤቱ በሕግ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ ጥፋተኛውን ሲመዝን በወንጀለኛው ላይ ጥፋተኛ በተባለበት የወንጀል ድንጋጌ ላይ የተቀመጠውን ቅጣት መወሰኑ ከትርፉ ይልቅ ኪሳራው ያመዝናል ብሎ በሚያምንበት ወቅት የቅጣት ውሳኔውን ከመወሰን ተቆጥቦ ለወንጀለኛው የፈተና ጊዜ ሊሰጠውና የፈተና ጊዜውን በተገቢው ሁኔታ ከተወጣ የጥፋተኝነት ውሳኔውን ሊሰርዝለት ይችላል። በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 191 ላይ እንደተመለከተው ፍርድ ቤቱ እንዲህ ዓይነት የፈተና ጊዜ በመስጠት ወንጀለኛው ጥፋተኛ ለተባለበት ወንጀል ቅጣት ሳይጥል የሚተወው ወንጀለኛው ለወደፊት ጠባዩን ለማረም እንዲችል እምነት ሊጣልበት የሚገባው መሆኑንና "ጥፋተኛ ነህ" መባሉ ብቻ ማስጠንቀቂያ ሆኖት እስከመጨረሻው ጠባዩን ለማሻሻል የሚያስችለው መሆኑን የገመተ እንደሆነ ነው።

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ድንጋጌ ላይ ወንጀለኛው ሊታረም ይችላል ተብሎ የሚገመትባቸው ሁኔታዎች የተዘረዘሩ ሲሆን በዚህም መሰረት ወንጀለኛው ቀድሞ ያልተቀጣ ወይም ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጀል የፈፀመ፣ ጠባዩም አደገኛነት የሌለው ስለመሆኑ የሚታመንበት ዓይነት እንደሆነና አሁን ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘበት ወንጀል በመቀጮ፣ በግዴታ ሥራ ወይም ከሦስት ዓመት ባልበለጠ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛነቱን ካረጋገጠ በኋላ የፈተና ጊዜ በመስጠት የቅጣት ውሳኔውን ከመወሰን ገድቦ ማቆየት ይችላል።

ፍርድ ቤቱ ለጥፋተኛው የሚሰጠው የፈተና ጊዜ ከሁለት ዓመት ሊያንስና ከአምስት ዓመት ሊበልጥ የማይችል ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤቱ በወሰነው የፈተና ጊዜ ወቅት ጥፋተኛው ሊከተለው የሚገባውን የጠባይ አመራር፣ የአጠባበቅና የመቆጣጠር ደንቦችን በተመለከተ በውሳኔው ላይ የሚያሰፍር ሲሆን እነዚህ ደንቦች በአንድ የጥበብ መስክ ሙያ መማርን፣ በተወሰነ ሥፍራ መቀመጥን፣ ከአንዳንድ ሰዎች ጋር አለመገናኘትን፣ አልኮል ከመጠጣት መቆጠብን፣ ወ.ዘ.ተ ሊያካትቱ ይችላሉ። በተጨማሪም ፍርድ ቤቱ

እንዚህን የጠባይ አመራር፣ የአጠባበቅና የመቆጣጠር ደንቦችን ጥፋተኛው ተከትሎ እየፈፀመ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር አድርጎ ቢያንስ በየሦስት ወሩ ወይም አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ ለሚመለከተው የጠባይ መሻሻል ጥበቃ ኮሚሽን ሪፖርት የሚያቀርብ አሳዳሪ፣ ሞግዚት፣ የጠባይ መሻሻል ጥበቃ ኃላፊን ወይም የጠባቂነት ሥልጣን የተሰጠው አካል የጥበቃ ባልደረባን ያዝዛል፡፡

በዚህ ፍርድ ቤቱ በሰጠው የፈተና ጊዜ ወቅት ጥፋተኛው መጥፎ ጠባይ ካሳዬ ወይም በቸልተኝነት ወንጀል ከፈፀመ በቸልተኛነት ላደረገው ወንጀል መከሰሱ እንደጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቱ ማስጠንቀቂያ የሚሰጠው ሲሆን ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው በኋላ በመጥፎ የጠባይ አመራር ከቀጠለ ወይም አስቦ አዲስ ወንጀል ሰርቶ የተፈረደበት እንደሆነ ፍርድ ቤቱ አግዶት የነበረውን የቅጣት መወሰን ሰርዞ ወንጀለኛው ጥፋተኛ ሆኖ ለተገኘበት ወንጀል ተገቢውን ቅጣት በመጣል ቅጣቱ እንዲፈፀምበት ያደርጋል፡፡ ቅጣቱ የሚወሰነውም ስለደጋጋሚነት የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ለተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጻሚ በሚሆነው የቅጣት አወሳሰን መርህ መሰረት ለተፈረደበት ወንጀል ከሚወሰነው ቅጣት ጋር አዲስ ለፈፀመው ወንጀል የሚጣለውን ቅጣት በመደመር ነው፡፡

በሌላ በኩል ግን ፍርድ ቤቱ ለጥፋተኛው በወሰነው የፈተና ጊዜ ውስጥ ምንም ዓይነት ጥፋት ካልፈፀመ ማለትም ጥፋተኛው የፈተና ጊዜውን በጥሩ ሁኔታ ካሳለፈና ፈተናው መልካም ፍሬ ካስገኘ የጥፋተኝነት ውሳኔው እንዳልተሰጠ ተቆጥሮ የተወሰነበት ፍርድ ከፍርድ መመዝገቢያ መዝገብ ላይ እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡

6.2. <u>ቅጣት እንዳይፈጸም ማገድ</u>

ፍርድ ቤት አንድ ተከሳሽ ጥፋተኛ መሆኑን ካረጋገጠና የሚገባውን ቅጣት ከወሰነ በኋላ ወንጀለኛው ለወደፊቱ ጠባዩን ለማረም እንደሚችል እምነት ሊጣልበት የሚገባውና ይህ ፅኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ እስከመጨረሻው ጠባዩን እንዲያሻሽል እንደሚያደርገው የገመተ እንደሆነ የቅጣቱን አፈጻጸም አግዶ የፈተና ጊዜ ለወንጀለኛው ሊሰጠው ይችላል (አንቀጽ 192)፡፡ ፍርድ ቤቱ ቅጣት እንዳይፈጸም የሚሰጠው ትእዛዝ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሊመለከት የማይችል ሲሆን ከዋና ቅጣቶች በተጓደኝ የሚጣሉ ተጨማሪ

ቅጣቶችን በተመለከተ ግን እንደአግባብነቱ አብረው ታግደው እንዲቆዩ ወይም ተፈጻሚ መሆናቸው እንዲቀጥል ፍርድ ቤቱ ሊወስን ይችላል፡፡

በአንድ ወንጀለኛ ላይ የተወሰነ ቅጣት ሊገድብ የማይችልባቸው ሁኔታዎች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 (1) ላይ የተመለከቱ ሲሆን እነርሱም፡-

(1) ከዚህ በፊት የፅኑ እስራት ቅጣት ወይም ከሦስት ዓመት የሚበልጥ ቀላል እስራት ቅጣት ተወስኖበት የነበረ ከሆነና አሁን እንደገና በፈፀመው አዲስ ወንጀል ምክንያት ከእነዚህ ቅጣቶች አንዱ የሚወሰንበት የሆነ እንደሆነ የተወሰነበት ቅጣት ሊገደብለት አይችልም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር 198 ላይ ቅጣት እንዳይታገድ ይከለክል የነበረው ወንጀለኛው ከዚህ ቀደም በፈፀመው ወንጀል ከሦስት ዓመት ፅኑ እስራት በላይ ወይም ፅኑ ግዞት ተፈርዶበት ከነበረና አዲስ በፈፀመው ወንጀል ምክንያትም ከእነዚህ ቅጣቶች አንዱ የሚወሰንብት ከሆነ ነበር፡፡ በመሆኑም አዲሱ የወንጀል ሕግ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ የተቀመጠው መስፈርት እንዲሻሻል አድርጓል፡፡

(2) ምንም እንኳ ወንጀለኛው ከአሁን በፊት ወንጀል ፈጽሞ ያልተቀጣ ቢሆንም አሁን በተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት ዓመት የበለጠ ፅኑ እስራት ቅጣት የሚፈረድበት ከሆነ ቅጣቱ ሊታገድለት አይችልም፡፡ ይህ መስፈርት በወንጀል ሕጉ እንዲካተት የተደገ አዲስ መስፈርት ነው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥፋተኛ የሆነ ሰው ከምን በላይ ቢፈረድበት ቅጣቱ ሊገደብለት እንደማይችል በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ የተደነገገ ነገር አልነበረም፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ሳይደነገግ በመቅረቱ ፍርድ ቤቶች ከፈለጉ እስከ ዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ሊገድቡ ቢችሉ የሚያግዳቸው ነገር አልነበረም፡፡[20]

ፍርድ ቤቱ ለወንጀለኛው የሚሰጠውን የፈተና ጊዜ፣ በፈተና ጊዜው ወቅት ወንጀለኛው ሊከተለው የሚገባውን የመልካም ጠባይ አመራር፣ የአጠባበቅና የመቆጣጠር ደንቦችን በተመለከተ እንዲሁም የተሰጠው ገደብ ስለሚሻርበት ሁኔታ ከዚህ በላይ በወንጀል ጥፋተኝነት ከተወሰነ በኋላ ቅጣት ሳይጣል ስለሚሰጥ ገደብ በቀረበው ላይ

[20] የወንጀል ሕግ ሐተታ ዘምክንያት፣ መስከረም 1998፣ ገጽ 106(ያልታተመ)

የተገለፁት ጉዳዮች ቅጣት እንዳይፈጸም ፍርድ ቤቱ በሚያግድበት ጊዜም ተፈጻሚነት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው።

ፍርድ ቤቱ ለጥፋተኛው በሰጠው የፈተና ጊዜ ውስጥ ምንም ዓይነት ጥፋት ካልፈፀመ ማለትም ጥፋተኛው የፈተና ጊዜውን በጥሩ ሁኔታ ካሳለፈና ፈተናው መልካም ፍሬ ካስገኘ በጥፋተኛው ላይ ተወስኖበት የነበረው ቅጣት እስከ መጨረሻው ቀሪ ይሆንለታል። ነገር ግን ፍርዱ በወንጀለኞች መመዝገቢያ መዝገብ ላይ እንደተመዘገበ ይቆያል። ከመዝገብ የሚወጣው ለመሰየም የሚያበቁ ሁኔታዎች ተሟልተው ለፍርድ ቤት ጥያቄ ቀርቦ ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ ነው።

በአመክሮ ከእስር ስለመፍታት

አመክሮ (parole) በአስራት የተቀጣ ወንጀለኛ የእስር ጊዜውን ሳይጨርስ ከእስር የሚፈታበት ሥርዓት ነው። ይህ ሥርዓት እስረኛው በእስር ቤት ባለበት ወቅት ጥሩ ከሰራና ለወደፊቱም ጥሩ አመል ይኖረዋል ተብሎ ከተገመተ የተፈረደበትን የእስር ጊዜ ሙሉ በሙሉ ሳይጨርስ ከእስር ቤት የሚለቀቅበት ከእስር ቤት ከወጣ በኋላ የድሮ መጥፎ አመሉን ካላሻሻለ እንደገና እስር ቤት ተመልሶ የቀረውን እስራት የሚጨርስበት አካሄድ ነው።[21] በዚህም መሰረት አመክሮ ማለት አንድን እስረኛ በተወሰኑ ሁኔታዎች ላይ በመመርኮዝ ከእስር ቤት እንዲለቀቅ ማድረግና የቀረውን የእስራት ጊዜ ለጊዜው በእንጥልጥል ማቆየት ማለት ነው።

የአመክሮን መሠረተ ሀሳብ የሚያብራራው የወንጀል ሕጉ አንቀጽ እንደሚከተለው ይነበባል፡-

> " በዚህ የወንጀል ሕግ ውስጥ የተደነገገው ነጻነትን የሚያሳጣ ቅጣት ወይም የጥንቃቄ እርምጃ በተወሰነ ጊዜ ሁሉ በሕጉ የተወሰነው የቅጣት አፈጻጸም ጊዜ ሲደርስና ጠቅላላውም ሁኔታ ተሟልቶ ሲገኝ ተቀጪውን ለአመክሮ አስቀድሞ መልቀቅ ይቻላል።

[21] ለጠቅላይ ፍ/ቤት ጉባኤ 3ኛ መደበኛ ስብሳባ የቀረበ ጽሑፍ፣ 1982፣ ገጽ 10 (ያልታተመ)

ለአመክሮ በተወሰነ ገደብ መፈታት የተቀጪውን ጠባይ ማሻሻያና ወደ ደንበኛው ማህበራዊ ኑሮ መመለሻ ሆኖ መቆጠር ይገባዋል። ተቀጪው ለዚሁ ተገቢ ካልሆነና በተወሰነ ገደብ መፈታቱ ተገቢውን ውጤት የሚያስገኝ መሆኑ ካልታመነበት በቀር ሊፈቀድ አይችልም።"[22]

ከዚህ በላይ ከቀረበው የወንጀል ሕጉ ድንጋጌ የአመክሮን ዋና ዋና ባህሪያት ማየት ይቻላል። እነርሱም፦

1. አመክሮ እስረኛው ላሳየው የጠባይ መሻሻል የሚሰጥ የእስራት ቅናሽ መሆኑን፣
2. የእስራት ቅናሹ የሚሰጠው የእስረኛውን ጠባይ ለማሻሻልና ወደ ሕበረተሰቡ እንዲቀላቀል ለማበረታታት መሆኑን፣
3. አመክሮ የሚሰጠው በይገባኛል እንደመብት ሆኖ ሳይሆን አንድ እስረኛ የዚህ አሰራር ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያበቁትን አሟልቶ ስለመገኘቱ ሲረጋገጥ መሆኑን፣እንዲሁም
4. አመክሮ ውጤት የሚያስገኝ መሆኑ ካልታመነበት በቀር ማለትም አመክሮው እንደተፈለገው አጥፊውን አርሞ መልካም የሕበረተሰቡ አባል የማያደርገው ከሆነ ሊሰጥ የማይገባ መሆኑ፣

ናቸው።

አመክሮ "በይገባኛል" የሚጠየቅ መብት አይደለም። ማለትም አመክሮ ባህሪውን ላሻሻለ ወይም ለማሻሻል የሚጠበቅበትን ጥረት ሁሉ ስለማድረጉ ምልክት ላሳዬ እስረኛ ሕብረተሰቡ የሚሰጠው ማበረታቻ እንጅ እስረኛው ሊሰጠኝ ይገባል ብሎ እንደ መብት የሚጠይቀው አይደለም። በዚህም መሰረት አንድ እስረኛ በአመክሮ ከመለቀቁ በፊት ለአመክሮ ብቁ የሚያደርጉ በሕግ ተዘርዝረው የተመለከቱ ሁኔታዎች ተሟልተው መገኘታቸው መረጋገጥ ይኖርበታል።

[22] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 201

እስረኛው በአመክሮ እንዲፈታ ሊያሟላ የሚገባቸው ሁኔታዎች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 202 ላይ የተዘረዘሩ ሲሆን እነርሱም፡-

- ተቀጪው ከተፈረደበት የእስራት ጊዜ ውሰጥ ሁለት ሦስተኛውን ወይም ፍርዱ የዕድሜ ልክ ዕኑ እስራት ከሆነ ሀያ ዓመት ያህሉን ፈጽሞ ከሆነ፣
- እስረኛው ፍርዱን በሚፈፅምበት ወቅት በሥራውና በጠባዩ የተረጋገጠ መሻሻል አሳይቶ ከሆነ፣
- እስረኛው በፈፀመው ጥፋት ያደረሰውን ጉዳት ለማስተካከል ከሳ ስለመክፈሉ ወይም ለመካስ በተቻለው መጠን ጥረት ስለማድረጉ የሚያሳይ ማረጋገጫ ካቀረበ፣
- የእስረኛው ዐመልና ጠባይ ከሕብረተሰቡ ጋር በመልካም ሁኔታ ተቀላቅሎ ለመኖር የሚያስችለው ሲሆን፣

ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ ከተመለከቱት በአመክሮ ለመለቀቅ መሟላት ካለባቸው መመዘኛዎች በተጨማሪ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ ጥፋተኛው በአመክሮ ሲፈታ የሚተዳደርበት ሥራ ወይም የገቢ ምንጭ ያለው መሆን አለመሆኑ እንደ አንድ ቅድመ-ሁኔታ ተደንግጎ የነበረ ሲሆን[23] ይህ መመዘኛ ከግምት መግባቱ ድህውን የሚጐዳ ነው በሚል ከአዲሱ የወንጀል ሕግ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

ሌላው በአዲሱ የወንጀል ሕግ ላይ የተደረገው ለውጥ ከቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በተለዬ በአመክሮ መፈታት ለልማደኛ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ተፈፃሚ እንዳይሆን የሚከለክል አዲስ ድንጋጌ እንዲጨመር መደረጉ ነው፡፡[24] ይህ አዲስ ድንጋጌ ልማደኛ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ በተቀጣው ባለመታረሙ አደገኛ ስለሆነና ለእንዲህ ዓይነት ወንጀለኛ በአመክሮ የመፈታት ዕድል መስጠቱ የወንጀለኛነት ድርጊቱን እንዲገፋበት የሚያበረታታ በመሆኑ በአመክሮ መለቀቅ የለበትም የሚል አስተሳሰብ የያዘ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ደጋጋሚ ወንጀለኛ የአመክሮ ዕድል ተጠቃሚ አይደለም፡፡

[23] የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 207
[24] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 202(2)

አንድ እስረኛ በአመክሮ የሚፈታው ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ጥያቄውን ተቀብሎ አመክሮውን ሲፈቅድ ሲሆን አመክሮ እንዲሠጥ የሚቀርበው ጥያቄም አግባብ ባለው አካል ወይም በጥፋተኛው አሳሳቢነት ሊሆን እንደሚችል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 202 ላይ ተመልክቷል፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ መሠረት ግን የአመክሮ ጥያቄ ሊቀርብ የሚችለው በዋናነት በእስር ቤቱ ሥራ አስኪያጅ አሳሳቢነት ሲሆን ሆኖም እስረኛው ልለቀቅ ብሎ ሀሳብ ሊያቀርብና ማመልከቻውን የእስር ቤቱ ሹም ተቀብሎ ድጋፍ ያለው ወይም የሌለው መሆኑን ጨምሮ ለፍርድ ቤቱ ሊያስተላልፍ የሚችልበት ሁኔታም ነበር፡፡[25]

በመሆኑም በቀድሞው ሕግ አመክሮ በእስር ቤቱ ሥራ አስኪያጅ አሳሳቢነት ለፍርድ ቤት እንደሚቀርብ ተመልክቶ የነበረው በአዲሱ የወንጀል ሕግ ላይ አግባብ ባለው ማንኛውም አካል ሊቀርብ እንደሚችል ለማመልከት የአመክሮ ጥያቄ "አግባብ ባለው አካል ወይም በጥፋተኛው አሳሳቢነት" ሊቀርብ ይችላል ተብሎ እንዲተካ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ከእስር ቤቱ የበላይ ኃላፊ በተጨማሪ ሌሎች ሕግ በሚደነግገው መሰረት የአመክሮ ጥያቄዎችን ሊያቀርቡ የሚችሉ አካላት አመክሮ ለእስረኛው እንዲሰጥ ፍርድ ቤቱን ማሳሳብ እንዲችሉ አዲሱ የወንጀል ሕግ ይፈቅዳል፡፡

አንድ እስረኛ በአመክሮ እንዲፈታ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ተፈቺው በአመክሮ የሚቆይበትን ጊዜ መጠን የሚወስን ሲሆን ይህ ጊዜ የተፈቺው ጠባይ ክትትል የሚደረግበት የፈተና ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ፍርድ ቤቱ በወሰነው የፈተና ጊዜ ወቅት ጥፋት ከፈፀመ በአመክሮ የመፈታት ትዕዛዙ የሚሻርና ወንጀለኛው ወደ እስር ቤት ተመልሶ በአመክሮው ምክንያት ተቋርጦ የነበረውን ቀሪ የእስራት ቅጣት የሚፈፅም ሲሆን በአመክሮ ተፈትቶ ከእስር ቤት ውጭ ያሳለፈው ጊዜ ሊፈፅም ከሚገባው ቀሪ እስራት ላይ አይታሰብለትም፡፡ ፍርድ ቤቱ ለእስረኛው በወሰነው የፈተና ጊዜ ውስጥ ምንም ዓይነት ጥፋት ካልፈፀመ ወይም የአመክሮ ጊዜው ያለ ምንም ጥፋት ከተጠናቀቀ ግን ያልፈፀመው የእስራት ጊዜ እስከ መጨረሻው ቀሪ ይሆንለታል፡፡

[25] የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 207 እና 208

በፈተና ጊዜው ወቅት ምን ዓይነት ጥፋቶች ናቸው የአመክሮ ትዕዛዙ እንዲሰረዝ የማድረግ ውጤት የሚኖራቸው የሚለውን በተመለከተ የቀድሞውም ሆነ አዲሱ የወንጀል ሕግ የሚያስቀምጡት መስፈርት ተመሳሳይ ነው፡፡ ይኸውም ጥፋተኛው ለፈተና በተሰጠው ጊዜ ውስጥ አስቦ አዲስ ወንጀል ሰርቶ የተፈረደበት እንደሆነ የአመክሮ ውሳኔው ተሰርዞ ቀሪው እስራት እንዲፈፀምበት ይደረጋል፡፡[26]

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው አንድ እስረኛ በአመክሮ እንዲፈታ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ተፈቺው በአመክሮ የሚቆይበትን ጊዜ መጠን የሚወስን ሲሆን ይህ ጊዜ በሌላ ሁኔታ ካልታዘዘ በስተቀር እስረኛው ከቀረው የእስራት ጊዜ በላይ ሊሆን አይችልም፡፡ እንዲሁም በማናቸውም ሁኔታ ከሁለት ዓመት ሊያንስ እና ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር ከአምስት ዓመት ሊበልጥ አይችልም፡፡ አመክሮ የተሰጠው የፅድሜ ልክ ፅኑ እስራት የተወሰነበት ወንጀለኛ ሲሆን የአመክሮው ጊዜ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ "ከአምስት ዓመት አይወርድም" ይል የነበረ ሲሆን በአዲሱ የወንጀል ሕግ ላይ ግን "ከአምስት ዓመት ሊያንስ ከሰባት ዓመት ሊበልጥ አይችልም" በሚል ተተክቷል፡፡ ይህም የተደረገው ፍርድ ቤቶች /ዳኞች/ ፅድሜ ልክ ፅኑ እስራት በተፈረደበት ጥፋተኛ ላይ ተገቢ ያልሆነ ረጅም የፈተና ጊዜ እንዳይሰጡ ለመገደብ ታስቦ ስለመሆኑ ስለድንጋጌው በተጻፈው በወንጀል ሕጉ ሐተታ ዘምክንያት ላይ ተመልክቷል፡፡[27]

7. ይቅርታና ምህረት

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ "Pardon" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል "ምህረት"፣ "amnesty" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል "የአዋጅ ምህረት" በሚል ተመልክተው የነበሩ ሲሆን በአዲሱ የወንጀል ሕግ ግን "Pardon" የሚለው "ይቅርታ"፣ "amnesty" የሚለው ደግሞ "ምህረት" በሚል ተተክቷል፡፡

[26] የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 211 እና 204(2)፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 206 እና 200(2)
[27] የወንጀል ሕግ ሐተታ ዘምክንያት፣መስከረም 1998፣ገጽ 112(ያልታተመ)

7.1. የይቅርታ ምንነትና ሕጋዊ ውጤቱ

ይቅርታ ወንጀል መፈፀማቸው በፍርድ ቤት ተረጋግጦ የቅጣት ውሳኔ የተሰጠባቸውን ወንጀለኞች የሚመለከት ነው። ይቅርታ ቅጣትን ሊያስቀር፣ ሊያስቀንስ ወይም ሊያስቀይር የሚችል ውሳኔ ነው። የከባድንታቸው ደረጃ ማናቸውም ቢሆን በዋነኛነትም ሆነ ወይም በተጨማሪ ተፈጻሚ ለሚሆኑ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ይቅርታ ሊሰጥ ይችላል። ሆኖም ይቅርታ ሊሠጥ የማይችልባቸው ሁኔታዎች አሉ። "በስብዕና ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች"ን አስመልክቶ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 28 ስር እንደተደነገገው ማንኛውም የመንግስት አካል በስብዕና ላይ ወንጀል ለፈፀሙ ሰዎች ይቅርታ ማድረግ አይችልም። ይህን የሕገ መንግስቱን የክልከላ ድንጋጌ ለማመልከትም አዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 229 "በሕግ በሌላ አካኋን ካልተደነገገ በቀር" በፍርድ የተወሰነ ቅጣት በሙሉ ወይም በከፊል በይቅርታ ቀሪ እንዲሆን ሊወሰን ወይም የቅጣቱ ዓይነት አነስተኛ ወደ ሆነ ቅጣት ሊለወጥ እንደሚችል ደንግጓል። "በሕግ በሌላ አካኋን ካልተደነገገ በቀር" በሚል ድንጋጌው ላይ የተቀመጠው ሀረግ የሚያመለክተው ለማናቸውም ወንጀሎች ይቅርታ እንደማይሰጥ ማለትም በሕገ መንግሥቱ የተደረገው ክልከላ ግምት ውስጥ መግባት ያለበት መሆኑን ነው።

ይቅርታ ገደብ ተደርጎበት ወይም ፍፁም በሆነ ሁኔታ ሊሰጥ ይችላል። በገደብ ወይም በሁኔታ ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ ይቅርታ ጥፋተኛው በተሰጠው ገደብ መሰረት እንቅስቃሴውን አስተካክሎ ካልተራመደ የይቅርታ ውሳኔው ቀሪ ሆኖ ቅጣቱ እንዲፈፀምበት የሚደረግ ሲሆን ፍፁም የሆነ ይቅርታ ግን በገደብ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተንጠለጠለ በመሆኑ ከይቅርታው በኋላ ያለው የጥፋተኛው እንቅስቃሴ በተሠጠው የይቅርታ ውሳኔ ላይ የሚያስከትለው ምንም ውጤት አይኖርም። ይቅርታ በሚሰጥበት ወቅት ገደቡ (ካለ) በይቅርታ ውሳኔው ላይ ይገለጻል።

ይቅርታ የቅጣት ውሳኔን ከመፈፀም ቀሪ ሊያድርግ ቢችልም የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔን ወይም ፍርድን ግን ሊያሰርዝ አይችልም። ስለዚህ ይቅርታ የተደረገለት ሰው የተወሰነበት ፍርድ በፍርድ መመዝገቢያ መዝገብ ላይ መመዝገቡ አይቀርም።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት በአንቀጽ 71(7) ይቅርታ የማድረግ ሥልጣንን (በፊደራል መንግስት ደረጃ) ለአገሪቱ ፕሬዝዳንት ሰጥቷል፡፡

ይቅርታ የፍትሐብሔር ተጠያቂነትን አያስቀርም ማለትም ጥፋተኛው በፈፀመው የወንጀል ድርጊት ምክንያት በተበዳዩ ላይ ያደረሰውን ጉዳት የመካስ ግዴታውን ቀሪ አያደርግም፡፡ ለመንግስት መከፈል የነበረበት ኪሣራ ካለ ግን ለጥፋተኛው በተሰጠው ይቅርታ ቀሪ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ ሆኖም በተለየ ሁኔታ በይቅርታ ውሳኔው ወይም ትዕዛዙ ላይ ለመንግሥት ሊከፈል የሚገባው ክፍያ በይቅርታ ውሳኔው ቀሪ እንደማይሆን ከተመለከተ ለመንግሥት የሚከፈለው የፍትሐብሔር ካሣ ቀሪ አይሆንም (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 231(2))፡፡

7.2. <u>የምህረት ምንነትና ሕጋዊ ውጤቱ</u>

ምህረት ለተወሰኑ የወንጀል ዓይነቶች ወይም ወንጀለኞች የሚሠጥ ውሳኔ ነው፡፡ ሁኔታዎች ተገምግመው የእርምጃው አስፈላጊነት ሲታመንበት የምህረት ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ሆኖም ምህረት ሊሠጥ የማይችልባቸው ሁኔታዎች አሉ፡፡ ይቅርታን አስመልክቶ ከዚህ በላይ በቀረበው ጽሑፍ ላይ እንደተገለፀው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 28 ድንጋጌ መሠረት ማንኛውም የመንግስት አካል በስብዕና ወንጀል ለፈፀሙ ሰዎች ምህረት ማድረግ አይችልም፡፡ ይህን ሕገ መንግሥታዊ ክልከላ ለማመልከትም ስለ ምህረት የሚደነግገው የአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 230 ድንጋጌ “በሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በቀር” የሚል ሀረግ ተጠቅሟል፡፡ ይህም የሚያመለክተው ለማናቸውም ወንጀሎች ምህረት እንደማይሰጥ ማለትም በሕገ መነግሥቱ የተደረገው ክልከላ ግምት ውስጥ መግባት ያለበት መሆኑን ነው፡፡

ምህረት ከተሰጠ ጊዜ ጀምሮ ወንጀል ፈፃሚዎቹ ያልተያዙ ወይም ክሱ ያልቀረበባቸው ከሆነ ወደፊት ሊያዙም ሆነ ክስ ሊቀርብባቸው አይችልም፣ ክስ ቀርቦባቸው ከሆነ ክሱ ይሰረዛል፣ በቅጣት ላይ ካሉ ቅጣቱ ይቆማል፡፡ ምህረት የተደረገበትን ወንጀል የፈፀመ ሰው ተፈርዶበት ከሆነ ፍርዱ እንዳልነበረ ተቆጥሮ

ከፍርድ መመዝገቢያ መዝገብ ላይ ይሠረዛል፤ ማለትም ምንም ዓይነት ሪኮርድ አይያዝበትም፡፡

ምንም እንኳን ምህረት በዋነኛነትም ሆነ ወይም በተጨማሪ ተፈጻሚ የሚሆኑ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሁሉ ቀሪ የማድረግ ውጤት ቢኖረውም አንድ የውጭ አገር ዜጋ ለቅጣቱ ምህረት ቢደረግለትም ከአገር የማስወጣቱ የጥንቃቄ እርምጃ ግን ቀሪ ላይሆን ማለትም ከአገር የማስወጣቱ ውሳኔ ተፈጻሚ ሊሆንበት ይችላል (አንቀጽ 151(2))፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት ይቅርታ የማድረግ ሥልጣንን (በፌደራል መንግስት ደረጃ) ለአገሪቱ ፕሬዝዳንት የሰጠ ሲሆንም ምህረትን በተመለከተ ግን ምንም የሚለው ነገር የለም፡፡

እንደ ይቅርታ ሁሉ ምህረትም የፍትሐብሔር ተጠያቂነትን አያስቀርም ማለትም ጥፋተኛው በፈፀመው የወንጀል ድርጊት ምክንያት በተበዳዩ ላይ ያደረሰውን ጉዳት የመካስ ግዴታውን ቀሪ አያደርግም፡፡ ለመንግስት መከፈል የነበረበት ኪሣራ ካለ ግን ለጥፋተኛው በተሰጠው የምህረት ውሳኔ ቀሪ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ ሆኖም በተለየ ሁኔታ በምህረት ውሳኔው ወይም ትዕዛዙ ላይ ለመንግሥት ሊከፈል የሚገባው ክፍያ በምህረት ውሳኔው ቀሪ እንደማይሆን ከተመለከተ ለመንግሥት የሚከፈለው የፍትሐብሔር ካሣ ቀሪ አይሆንም (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 231(2))፡፡

8. <u>የመሰየም ምንነትና ሕጋዊ ውጤቱ</u>

ቀድሞ ወንጀለኛ የነበረ ሰው ወደ ንፁህነት የሚመለስበት ወይም ስሙ እንደገና የሚታደስበት ሁኔታ መሰየም ተብሎ ይጠራል፡፡ አንድ ወንጀለኛ ቅጣቱን ከፈፀመና ወደ ሕበረተሰቡ ተመልሶ በሕጉ የተመለከተውን የፈተና ጊዜ በብቃት ካለፈ የወንጀል ሪኮርዱ ሊፋቅለት ይገባል እንጅ ወንጀሉ በሄደበት ቦታ ሁሉ እንደ ጥላ ሊከተለው አይገባም፡፡ ሕብረተሰቡ ውስጥ ገብቶ መልካም ኗሪነቱን በተግባር ያረጋገጠው የቀድሞ ወንጀለኛ እንደ ማንኛውም የሕብረተሰብ አባል መታየት የሚጀምርበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡

የፈፀመው ወንጀል አሉታዊ ውጤት እስከ ሕይወት ፍጻሜው እንዲከተለው መደረጉ ለሕብረተሰቡም ምንም ዓይነት ገንቢ አገልግሎት የለውም።

ለመሰየም በጥፋተኛው ላይ የተጣለው ቅጣት በተለያዩ ምክንያቶች ቀሪ ከሆኑ በኋላ የተወሰነ ጊዜ ማለፍ አለበት። ቅጣቱ ቀሪ ከሆነ በኋላ ምን ያህል ጊዜ ቆይቶ ነው የቀድሞው ወንጀለኛ ለመሰየም ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው የሚለውን በተመለከተ ተወስኖበት በነበረው የቅጣት ዓይነት ይወሰናል። በወንጀለኛው ላይ ተወስኖበት የነበረው ቅጣት ፅኑ እስራት፣ ከአገር እንዲወጣ ወይም ንብረቱ እንዲወረስ ከሆነ ቅጣቱ ቀሪ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ አምስት ዓመት (የቀድሞው ሕግ አስር ዓመት ይል ነበር) ማለፍ ያለበት ሲሆን አጥፊው ተወስኖበት የነበረው ቅጣት ከነዚህ ዝርዝሮች ውጭ ከሆነ ግን ሁለት ዓመት (የቀድሞው ሕግ አምስት ዓመት ይል ነበር) ማለፍ አለበት። ይህ አጠቃላይ የጊዜ ወሰን በመርህ ደረጃ የተደነገገ ቢሆንም የመሰየም ጥያቄ የሚያቀርበው ተቀጪ በሕዝባዊ፣ በወታደራዊ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት መስክ ተሰማርቶ በግልፅ የሚታይ የሚያስመሰግን ሥራ ለሕብረተሰቡ አበርክቶ ከተገኘ በሕግ የተወሰነው አነስተኛ የጊዜ ገደብ ከመድረሱ በፊት መሰየሙ ሊፈቀድለት ይችላል(አንቀጽ 234(2))። እንዲሁም ለመሠየም የሚያበቃው አነስተኛ ጊዜ ተፈፃሚነት የሚኖረው ስለደጋጋሚነት የተደነገገውን የጊዜ ገደብ እስካልነካ ድረስ ነው። ይህም ማለት አንድ ሰው ቅጣቱ ቀሪ ከሆነለት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ካለፈ በፍርድ ቤት ውሳኔ ሊሰየም የሚችል ቢሆንም ስለ ደጋጋሚነት በተቀመጠው መስፈረት መሰረት ደግሞ ቅጣቱ ቀሪ ከሆነለት ጊዜ ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ወንጀል ከፈፀመ በደጋጋሚ ወንጀለኛት ሊፈረጅ የሚችል በመሆኑ መሰየሙ እንደ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ከመቆጠር አያድነውም ማለት ነው። ይህ ልዩ ሁኔታ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ ያልነበረ በወንጀል ሕጉ ውስጥ እንዲካተት የተደረገ አዲስ መመዘኛ ነው።

ቅጣቱ ቀሪ ከሆነ በኋላ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው አነስተኛ የጊዜ ገደብ ማለፉ ብቻ ወድያውኑ መሰየምን አያስከትልም። እንዲሁም በወንጀል ሕጉ ላይ በግልፅ እንደሰፈረው "መሰየም የሚገኘው በመልካም ሥራ ነው እንጂ በይገባኛል አይደለም" (አንቀጽ 232(1))። ለመሰየም ቅጣቱ ቀሪ ከሆነ በኋላ በሕግ የተወሰነው ጊዜ ማለፍ ያለበት

መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች ለመሰየም የሚያበቁ ቅድመ ሁኔታዎችም ተሟልተው መገኘት አለባቸው። እነርሱም፡-

1. ለመሰየም ብቁ እንዲሆን በሕግ በተወሰነው ከላይ በተጠቀሰው አነስተኛ የጊዜ ገደብ ወስጥ በመልካም ጠባይ ተመርቶ እንደሆነና በእስራት ቅጣት የሚያስቀጣ ወንጀል ፈጽሞ ጥፋተኛ ሳይሆን ቆይቶ ከሆነ፤ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ይህ ቅድመ ሁኔታ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በማናቸውም ጥፋት ሳይከሰስ እንዲሁም አቤቱታ ሳይቀርብበት ቆይቶ እንደሆነ በሚል ነበር ተመልክቶ የነበረው (ቁጥር 243(ለ))።

2. ከዋናው ቅጣት ጋር ተጨማሪ ቅጣት በአጥፊው ላይ ተወስኖ የነበረ ከሆነ ይኸው ቅጣት ተፈጽሞ እንደሆነ፤ በዚህም መሰረት አጥፊው ለምሳሌ የወንጀሉን ተጎጂ ይቅርታ እንዲጠይቅ ተጨማሪ ቅጣት ተወስኖበት የነበረ ከሆነ ይህንኑ መፈፀሙ ካልተረጋገጠ በቀር ለፍርድ ቤት ያቀረበው የመሰየም ጥያቄ ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም።
3. የተለቀቀው ተቀጪ አቅሙ በፈቀደ መጠንና ራሱም ሊፈፅመው ይገባዋል ብሎ በሚገመትበት ሁኔታ በፍርድ የተወሰነበትን ካሳ፣ የዳኝነትና ማናቸውንም ሌላ ኪሣራ በሚገባ አጠናቅቆ ከፍሎ እንደሆነ፣

የሚሉት ናቸው።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር 247 መሠረት አንድ ጥፋተኛ በተሰየመ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ማናቸውም ዓይነት ነፃነትን የሚያሳጣ ወይም የሞት ቅጣት የሚያስቀጣ አዲስ ወንጀል የፈፀመ እንደሆነ የመሰየም ውሳኔው ይሻራል። በዚህም መሰረት ተቀጪው የፈፀመው አዲስ ወንጀል ቀላል እስራትም ሆነ ፅኑ እስራት የሚያስቀጣው ቢሆን የመሰየም ውሳኔውን የማሻር ውጤት ይኖረዋል። በአዲሱ የወንጀል ሕግ ላይ ግን በዚህ መመዘኛ ማሻሻያ ተደርጎበታል። ይኸውም ተቀጪው የፈፀመው አዲስ ወንጀል በፅኑ እስራት ወይም በሞት ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር የመሰየም ውሳኔውን የማሻር ውጤት አይኖረውም። ስለሆነም በአዲሱ ሕግ መሰረት ተቀጪው እንዲሰየም ከረፈቀደለት በኋላ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ አዲስ ወንጀል ፈፅሞ በሞት

ወይም በፅኑ እስራት ከተቀጣ (ፅኑ እስራት ከተወሰነበት) የተፈቀደለት መሰየም ይሰረዛል፣እንዲሁም ዳግመኛ እንዲሰየም ሊፈቀድለት አይችልም (አንቀጽ 237)፡፡

በቀድሞው ሕግ ላይ ጥፋተኛው በገደብ የተለቀቀ በሚሆንበት ጊዜ ስለሚሰየምበት ሁኔታ አልተመለከተም ነበር፡፡ ከዚህ በፊት ለመግለፅ እንደተሞከረው አንድ ወንጀል አድራጊ በፍርድ ቤት ተከስሶ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ በኋላ የሚጣልበት ቅጣት የተወሰነ ፈተና ጊዜ ተሰጥቶት ሳይፈፀምበት ሊቀር የሚችልበት ያለ ሲሆን በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ አጥፊው በገደብ በሚለቀቅበት ጊዜ ለመሠየም የሚያበቃው አነስተኛ ጊዜ የሚሰላው ቅጣቱ ከታገደበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 233(ሀ) ላይ በግልፅ ሰፍሯል፡፡

የመሰየም ውሳኔ ቀደም ሲል በተቀጪው ላይ ተወስኖ የነበረውን ፍርድ ሙሉ በሙሉ የሚሰርዘው በመሆኑ የመሰየም ውሳኔውን የሚያሸር ወንጀል ካልተፈፀመ በስተቀር ተቀጥቶ የነበረው ሰው ከቅጣቱ የተነሳ እንዳይጠቀምባቸው ተከልክሎ የነበሩትን መብቶች ሁሉ እንደገና ይዞ የመስራት ችሎታ ይኖረዋል፡፡ ፍርዱ የሚሰረዝለት በመሆኑ ከወንጀለኞች መዝገብ ላይ ተፍቆለት ወደፊት እንዳልተፈረበት ይቆጠራል፡፡

የሕጉ ዓላማ የወንጀለኛው ወደ መልካም ሰውነት መመለስ ይቃና ዘንድ ለዚህ ብቁ የሆነን የቀድሞ ወንጀለኛ ምንም ዓይነት የወንጀለኛንነት ምልክት እንዳይኖር ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ጥፋተኛነቱና ቅጣቱ እንዳልነበሩ ሆነው ሊቆጠሩ ይገባል፡፡ በተግባር ቀደም ሲል መፈፀሙ በፍርድ ቤት ጭምር በማስረጃ ተረጋግጦ የነበረውን እውነታ (የወንጀል ድርጊት) ሕጉ ለግለሰቡና ለሕብረተሰቡ ጥቅም ሲል እንዳልነበረ (እንዳልተፈጠረ) የሚቆጥረው በመሆኑ ከመሰየሙ በፊት የነበረውን ጥፋት እያነሳ የተሰየመውን ሰው መውቀስ በስም ማጥፋት ወንጀል የሚያስጠይቅ አድርጎታል፡፡ ስለ ጥፋቱ የተነሳው ለመልካም ዓላማ እንደሆነ አድርጎ በማቅረብ ከተጠያቂነት መዳንም አይቻልም፡፡ በዚህ መሰረትም የመሰየም ውሳኔው ተሰያሚውን ከቀድሞ የወንጀለኛነት ሪከርዱ ፍፁም ንፁህ ያደርገዋል ማለት ነው፡፡

9. የወጣት ጥፋተኞችና ዳኝነት

ዕድሜያቸው ከዘጠኝ ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናት በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ መሠረት በወንጀል ሊጠየቁ አይችሉም፡፡ በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሕጻናት በወንጀል ኃላፊ ሊያደርግ የሚችል የእውቀትም ሆነ ድርጊትን የመቆጣጠር ችሎታ የሌላቸው በመሆኑ ለፈፀሙት ወንጀል እንደ ኃላፊ ሆነው አይቆጠሩም፡፡ በመሆኑም ለፈፀሙት ወንጀል ሊቀጡ አይችሉም፡፡ በዚህም መሠረት ሕጻናት ወንጀል ፈፅመው በሚገኙበት ጊዜ ለሕጻናቱ መልካም አስተዳደግ ኃላፊነት ያለባቸው ወገኖች ተገቢ የሆኑትን ጥንቃቄዎች እንዲያደርጉላቸው ይደረጋል (አንቀጽ 52)፡፡ ሕጻናት ከወንጀል ኃላፊነት ነጻ ከሚሆኑባቸው ምክንያቶች መካከል ጥቂቶቹ ሕጻኑን ወላጆቹ እንዲያርሙትና እንዲያስተምሩት ዕድል መስጠትና በለጋ ዕድሜ ውስጥ ለሚገኝ ሁሉ ተስማሚ ቦታ በሆነው በቤተሰቡ መኖሪያ ቤት እንዲጠበቅ ማድርግ ናቸው፡፡[28]

ስለሆነም “ወጣት ጥፋተኞች” ስንል ስያሜው ዕድሜያቸው ከዘጠኝ ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናትን የማያካትት ስለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ወጣት ጥፋተኞች በማለት የሚፈርጃቸው ከዘጠኝ እስከ አስራ አምስት ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙትን በወንጀል የሚያስቀጣ ድርጊትን የፈፀሙ ሰዎችን ሲሆን ከአስራ አምስት ዓመት እስከ አስራ ስምንት ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙትን ደግሞ አካለ መጠን ከማድረስ አስቀድሞ የሚገኘው “መካከለኛ ጊዜ” በማለት በወንጀል ሕጉ የዕድሜ አከላለል መሠረት ከወጣትነት ወደ ዐዋቂነት የመሸጋገሪያ ዕድሜ እንደሆነ አድርጎ ይወስደዋል፡፡

በሌላ በኩል የወንጀል ሕግ ወጣት ወንጀል አድራጊዎች በማለት የሚጠራቸው ከዘጠኝ ዓመት እስከ አስራ ስምንት ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙትን የወንጀል ድርጊት የፈፀሙ ሰዎችን ነው፡፡

[28] ስታንሊ ዜድ ፊሸር “በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት በወጣት ጥፋተኞች ላይ” የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት7፡1 ገጽ 41

ሁለቱ የወንጀል ሕጎች ወጣት ወንጀል አድራጊዎች እነማን ናቸው በሚለው ላይ የተለያዩ ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙትን ወንጀል የፈፀሙ ሰዎችን የሚጠቅሱ ቢሆንም ሁለቱም ሕጎች ከዘጠኝ እስከ አስራ አምስት ባለው ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወንጀል አድራጊዎች መደበኛ የሆኑት ወይም ለአዋቂዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት ቅጣቶች ተፈጻሚ ሊሆኑባቸው እንደማይችሉ ሆኖም ዕድሜያቸው ከአስራ አምስት እስከ አስራ ስምንት ዓመት የሆኑት ወንጀል አድራጊዎች በመርህ ደረጃ በመደበኛዎቹ ማለትም ለአዋቂዎች ተፈጻሚ በሚሆኑት ድንጋጌዎች መሰረት ጉዳያቸው እንደሚታይ፤ ነገር ግን እንደ አስፈላጊነቱ ማለትም አጥፊው ሊታረም የሚችል መሆኑንና አደገኛነቱን ግምት ውስጥ በማስገባት ፍርድ ቤቱ ከዘጠኝ እስከ አስራ አምስት ዓመት ዕድሜ ክልል ውስጥ ላሉት ተፈጻሚ እንዲሆኑ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ማድረግ እንደሚችል አስቀምጠዋል።

ስለዚህ በሁለቱም የወንጀል ሕጎቻችን በየትኛውም ሁኔታ ከአዋቂዎች በተለዩ ጉዳያቸው እንዲታይና ለአዋቂዎች ተፈጻሚ የሚሆኑ ቅጣቶችዎች ተፈጻሚ እንዳይሆኑባቸው በግልፅ በመከልከል ለራሳቸው የሚሆኑ የተለዩ የጥንቃቄ እርምጃዎችና ቅጣቶች የተቀመጡላቸው ዕድሜያቸው ከዘጠኝ ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ላሉት ወንጀል አድራጊዎች በመሆኑ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ጽሑፍ ወጣት ወንጀል አድራጊዎች፣ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ወንጀል አድራጊዎች ወይም ወጣት ጥፋተኞች (juvenile delinquency ወይም juvenile offenders) በማለት የምንመለከታቸው በዚህ ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉትን የወንጀል ድርጊት የፈፀሙ ሰዎችን ነው።

በአዋቂዎችና በወጣት ወንጀል አድራጊዎች መካከል ተጠያቂ ሊሆኑባቸው በሚችሉት ወንጀሎች ዓይነትና በወንጀሎቹ ጥፋተኛ ሆኖ ለመገኘት በሚያስፈልጉት ጉዳዮች ረገድ ልዩነት የለም። ልዩነቱ የሚስተዋለው ጥፋቱ ከተረጋገጠ በኋላ ባለው ሁኔታ ነው። በዚህም መሰረት በወጣት አጥፊዎች ላይ የሚፈሙ የተለዩ የጥንቃቄ እርምጃዎችና ቅጣቶች አሉ። በዚህም መሰረት ወንጀል ነክ ሕግ በወጣትና በአዋቂ ሰዎች ላይ እኩል ተፈጻሚ ሲሆን ወንጀሉ መሠራቱ ከተረጋገጠ በኋላ ግን በወጣት ጥፋተኞች ላይ ፍርድ ቤቱ ቅጣት የሚወስነው ነገሩን ለማየት የሚረዱትን ልዩ የሕግ ድንጋጌዎች ብቻ በመከተል ይሆናል ማለት ነው።

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው ለአካለ መጠን ባልደረሱ ወንጀል አድራጊዎች ላይ የወንጀል ሕጉ መደበኛ (ተራ) ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ተፈጻሚ አይሆኑም። ለዚህም ጥፋት መፈፀማቸው ሲረጋገጥ ሊወሰኑባቸው የሚችሉ የተለዩ የጥንቃቄ እርምጃዎችን እና ቅጣቶችን የወንጀል ሕጉ አስቀምጧል።

9.1. ለአካለ መጠን ባልደረሱ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ስለሚወሰኑ የጥንቃቄ እርምጃዎች

ለአካለ መጠን ባልደረሱ ወጣቶች ላይ የሚፈፀሙ የቅጣት ዓይነቶች አሉ። ሆኖም እነዚህ ቅጣቶች ሊወሰኑ የሚችሉት አስቀድሞ በአጥፊው ላይ የተወሰዱት የጥንቃቄ እርምጃዎች ፍሬ ሳያስገኙ የቀሩ እንደሆነ ነው (አንቀጽ 166)። በመሆኑም ለአካለ መጠን ባልደረሱ ሰዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው አስቀድሞ የተወሰዱት የጥንቃቄ እርምጃዎች በወጣቱ ላይ ፍሬ አለማስገኘታቸው ሲረጋገጥ ነው። ለምሳሌ ወጣቱ ለሁለተኛ ጊዜ ወንጀል ፈጽሞ ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ ለመጀመሪያው ጥፋት የተወሰዱት የጥንቃቄ እርምጃዎች ፍሬ አለማስገኘታቸውን ራሱ ለሁለተኛ ጊዜ ለአካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ጥፋት መፈፀሙ የሚያስረዳ በመሆኑ ቅጣቶችን ለመወሰን ያስችላል።[29]

በአጠቃላይ ለአካለ መጠን ባልደረሱ ሰዎች ላይ ሊታዘዙ የሚችሉት የጥንቃቄ እርምጃዎች ሕክምና ወደሚደረግበት ተቋም መላክን፣ ቁጥጥር በሚደረግበት ሁኔታ ትምህርት እንዲማር ማድረግን፣ የድርጊቱን ውጤት እንዲረዳውና ለወደፊቱ መልካም ጠባይ እንዲኖረው መገሰፅና መውቀስን፣ በትምህርት ቤት ወይም በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ተወስኖ ሳይወጣ በእረፍት ሰዓቱ ወይም በእረፍት ቀኖቹ ለእድሜው የሚስማማ ስራ እንዲሰራ ማድረግን፣ እንዲሁም ለወጣት ወንጀል አድራጊዎች ማረሚያና ማስተማሪያ ወደ ተቋቋመ ልዩ ተቋም እንዲገባ ማድረግን ሁሉ ያጠቃልላል።

[29] ስታንሊ ዜድ ፊሸር "በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት በወጣት ጥፋተኞች ላይ" የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት7፡1 ገጽ 44

የሕክምናና የቁጥጥር ትምህርት የሚቆይበት ጊዜ የሚወሰነው ተገቢው የሕክምና ባለሥልጣን ወይም የጥበቃ ባልደረባ ያስፈልጋል በማለት ወስኖ ባቀረበው ጊዜ ልክ መሠረት ሲሆን ወንጀል አድራጊው ለአካለ መጠን እስከሚደርስበት ጊዜ ሊቀጥል ይቻላል። ሆኖም በፍርድ ቤቱ የታዘዘው የጥንቃቄ እርምጃ ጥሩ ፍሬ ያስገኘ ስለመሆኑ በተገቢው ባለሥልጣን አስተያየት ከቀረበና ፍርድ ቤቱ ካመነበት የትእዛዙ ተፈጻሚነት ቀሪ ሊሆን ይችላል (አንቀጽ 163)።

ለወጣት ወንጀል አድራጊዎች ማረሚያና ማስተማሪያ ወደ ተቋቋመ ልዩ ተቋም እንዲገባ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ የሚሰጥ ከሆነ በጠባይ ማረሚያ ተቋሙ ውስጥ ወጣት ወንጀል አድራጊው የሚቆይበት ጊዜ ምን ያህል እንደሆነ በፍርድ ቤቱ ውሳኔ ላይ መገለጽ ያለበት ሲሆን ይህ ጊዜ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችል ቢሆንም በማናቸውም ሁኔታ ወጣት ወንጀል አድራጊው አስራ ስምንት ዓመት ከሞላው (ለአካለ መጠን ከደረሰ) በኋላ የጥንቃቄ እርምጃው አፈጻጸም ሊቀጥል አይችልም።

ለፈተና በአመክሮ መለቀቅን በሚመለከት አመክሮ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸውን መደበኛ ሁኔታዎች ለአካለ መጠን ያልደረሰው ወንጀል አድራጊ አሟልቶ ከተገኘ አንድ ዓመት የተወሰነበትን በጠባይ ማረሚያ ተቋም ውስጥ የመቆየት የጥንቃቄ እርምጃ ከፈፀመ በኋላ አመክሮ ሊሰጠው ይችላል (አንቀጽ 163(2))።

ለአካለ መጠን ባልደረሱ ሰዎች ላይ ሊታዘዝ የሚለውን የጥንቃቄ እርምጃ ዓይነት ፍርድ ቤቱ የሚወስነው በአጥፊው ላይ ሊያመጣ የሚችለውን መልካም ለውጥ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ይህን የወንጀል ሕጉን ግብ እንዲሳከ ለማድረግም ፍርድ ቤቱ በአጥፊው ላይ ሊወሰዱ የሚገባቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚመርጠው "ዕድሜውን፣ ጠባዩን፣ የአዕምሮና የሞራል ዕድገቱን ሁኔታ" ግምት ውስጥ በማስገባት የተሻለ ውጤት ሊያስገኝ የሚችለውን መሆን አለበት።[30] የሚወሰደው እርምጃ ለአጥፊው ተስማሚ እንዲሆን የሚደረገው ጥረት የተቃና ይሆን ዘንድ ወጣቱ ምን ዓይነት ትምህርት፣ ጠባይን ማረሚያ እንደሚያስፈልገው ልዩ ዕውቀት ያለውን ሰው ፍርድ ቤቱ መጠየቅ የሚችል ሲሆን አንድ ጊዜ ውሳኔ ከሰጠ በኋላም ከተገቢው አካል በሚቀርብለት

[30] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 55

አስተያየት መነሻ አስቀድሞ ሰጥቶት የነበረውን የጥንቃቄ እርምጃ ትእዛዝ መለወጥ ይችላል(አንቀጽ 164)።

ሌላው እዚህ ላይ ሳይነሳ መታለፍ የሌለበት ነጥብ ቢኖር ለአካለ መጠን ያልደረሱ ወንጀል አድራጊዎች ላይ በወንጀል ጥፋተኛ ሆነው ተገኝተው በፍርድ ቤቱ የጥንቃቄ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ቢወሰንም "በወንጀል" እንደተቀጡ ተደርገው እንደማይቆጠሩ በወንጀል ሕጉ ላይ በግልፅ ተደንግጎ የሚገኝ መሆኑ ነው(ቁ. 169)።

9.2. <u>ለአካለ መጠን ባልደረሱ ወጣቶች ላይ ስለሚወሰኑ ቅጣቶች</u>:- ከዚህ በላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ለአካለ መጠን ባልደረሰ ወጣት ላይ ፍርድ ቤቱ የቅጣት ውሳኔ መወሰን የሚችለው ከዚህ ቀደም የተወሰዱበት የጥንቃቄ እርምጃዎች ፍሬ አለመስጠታቸውን ፍርድ ቤቱ የተገነዘበ እንደሆነ ነው። በዚህም መሰረት አንድ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ለምሳሌ ለሁለተኛ ጊዜ ወንጀል ፈጽሞ መቅረቡ ብቻውን ለሁለተኛው ወንጀል ቅጣት እንዲጣልበት አያደርግም። ሁለተኛ በፈፀመው ወንጀል ምክንያት ቅጣት ሊጣልበት የሚችለው መጀመሪያ ለፈፀመው ወንጀል የተወሰደበት የጥንቃቄ እርምጃ ፍሬ አለማስገኘቱ ሲረጋገጥ ነው። "አንድ የጥንቃቄ እርምጃ ከተፈፀመ በኋላ የተሰጠ የጥፋተኝነት ውሳኔ ቢኖርም እንኳ ፍርድ ቤቱ ቀድሞ የተሰጡት ውሳኔዎች ፍሬ ሰጥተው የሚያገኝበት ጊዜ አይጠፋም። ይህም የሚሆነው ለምሳሌ ልጁ ጠባዩንና ዝንባሌውን በጠቅላላው በጣም አሻሽሎ ሲገኝና አዲሱ ጥፋትም ከቀድሞ ኑሮው ሁኔታ ጋር የማይገናኝ ቀላል ጥፋት ሲሆን ነው።"[31]

ፍርድ ቤቱ በወንጀል ሕጉ የተመለከቱተን መመዘኛዎች በመከተል በአጥፊው ላይ ቅጣት መጣል አስፈላጊ ሆኖ በሚያገኝበት ጊዜ አካለ መጠን ባልደረሱ ሰዎች ሊወሰኑ ከሚችሉ ቅጣቶች ውስጥ አንዱን ሊወስንበት ይችላል። እነዚህም ቅጣቶች የገንዘብ መቀጮና እስራት ናቸው። በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ከእነዚህ ቅጣቶች በተጨማሪ አጥፊው እንቢተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነና ፍርድ ቤቱም ወደ በጎ መንፈስ

[31] ስታንሊ ዜድ ፊሸር "በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት በወጣት ጥፋተኞች ላይ" የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት7፡1 ገጽ 46

የሚመልሰውና ጠባዩን የሚያሻሽለው መሆኑን የገመተ እንደሆነ ከአስራ ሁለት ላልበለጠ ጊዜ ወጣት ወንጀል አድራጊው በአለንጋ እንዲገረፍ ለማዘዝ ፍርድ ቤቱ እንዲችል ይፈቅድ የነበረ ሲሆን (ቁጥር 172) በአዲሱ የወንጀል ሕግ ይህ በአለንጋ የመግረፍ የቅጣት ዓይነት ከሕጉ እንዲሰረዝና እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

ለአካለ መጠን ባልደረሱ ሰዎች ላይ የእስራት ቅጣት ሊወሰንባቸው የሚችለው የፈፀሙት ወንጀል አስር ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የፅኑ እስራት ቅጣት የሚያስቀጣ ወይም የሞት ቅጣት የሚያስከትል ከባድ ወንጀል ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ለአካለ መጠን ባልደረሱ ጥፋተኞች ላይ እስራት የሚወሰንበትን ሁኔታ ስንመለከት ልብ ሊባል የሚገባው መሠረታዊ ነገር አለ፡፡ ይኸውም አጥፊው ምንም ዓይነት ከባድ ወንጀል ይፈፅም የእስራት ቅጣት በአጥፊው ላይ ፍርድ ቤቱ ላይወስን ይችላል፡፡ በዚህም መሠረት ወጣት ጥፋተኛው የፈፀመው ወንጀል ከባድነት በሕጉ ላይ የተመለከተውን መመዘኛ የሚያሟላ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የእስራት ቅጣት በአጥፊው ላይ መጣሉን አስፈላጊነቱን ካላመነበት የጥንቃቄ እርምጃ እንዲወሰድበት መወሰን ይችላል (አንቀጽ 168(1/ሀ1))፡፡

ለአካለ መጠን ባልደረሰ ወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት የሚቆይበት አነስተኛ ጊዜ በቀድሞው ሕግ ላይ ከሦስት ዓመት እንደማያንስ ተመልክቶ የነበረ ሲሆን (ቁጥር 173(2)) በአዲሱ የወንጀል ሕግ ላይ ግን የእስራቱ መነሻ ከአነድ ዓመት አያንስም ተብሎ ተሻሽሏል (አንቀጽ 168(2))፡፡ በሁለቱም የወንጀል ሕጎች የእስራቱ ጊዜ ሊቆይ የሚችለው ደግሞ እስከ አስር ዓመት ድረስ ነው፡፡ ከዚህም በቀር በወጣት ጥፋተኞች ላይ የሚወሰነው የእስራት ቅጣት የሚፈፀመው በቀላል እስራት አፈጻጸም ደንብ መሠረት ነው፡፡[32]

ከላይ እንደተገለፀው ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ላይ የተወሰደበት እርምጃ የጥንቃቄ ብቻ ከሆነ በወንጀል እንዳልተቀጣ ተደርጎ የሚቆጠር ሲሆን የጥንቃቄ እርምጃ እና ሌላ ቅጣት ከሆነ ግን ከእስራት ቅጣት በስተቀር የጥንቃቄ እርምጃዎቹና ቅጣቱ በተፈፀመ በሁለት ዓመት በኋላ ጊዜ ውስጥ ለመሰየም

[32] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 169(3)

የሚያስፈልጉት ሁኔታዎች ተሟልተው ከተገኙ ለፍርድ ቤት የመሰየም ጥያቄ ማቅረብ ይችላል (አንቀጽ 175)። የተወሰነበት ቅጣት እስራት በሚሆንነት ጊዜ ግን የመሰየም ጥያቄውን ማቅረብ የሚችለው ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ማቅረብ በሚችሉበት ተመሳሳይ ጊዜ ነው።

በወጣት ጥፋተኞች ላይ የሚሰጥ ፍርድ በማናቸውም መንገድ ሕዝብ እንዲያውቀው ፍርድ ቤቱ ማድረግ የሌለበት ሲሆን በተጨማሪም ለአካለ መጠን ያልደረሰ ወንጀል አድራጊን በሚመለከት የተሰጠ የቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃ ውሳኔ በወንጀለኞች መዝገብ ላይ የሚመዘገብ ቢሆንም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት በስተቀር በማናቸውም ምክንያት የመዝገቡ ቅጂ ለሌላ ሰው መግለጽ የተከለከለ ስለመሆኑ የወንጀል ሕጉ ይደነግጋል (አንቀጽ 174)።

9.3. <u>የወጣት ጥፋተኞች የዳኝነት አመራር</u>፡- የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ወጣት የሚባለው ዕድሜው ከዘጠኝ ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት የሆነ ሰው ስለመሆኑ የሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 3 በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ በተደነገገው ዓይነት ያስቀምጣል። ለአካለ መጠን ባልደረሱ ወጣቶች ላይ የሚቀርብ የወንጀል ክስ የሚመራው በሥነ ሥርዓት ሕጉ ከቁጥር 171 እስከ ቁጥር 180 ባሉት ድንጋጌዎች ማለትም ወጣት ጥፋተኞችን በሚመለከተው በልዩው ሥነ ሥርዓት መሠረት ነው።

ለአካለ መጠን ያልደረሰ ወጣት የወንጀል ተግባር ፈጽሟል ተብሎ ሲጠረጠር ወድያውኑ መቅረብ ያለበት በቅርቡ ወደሚገኘው የወረዳ ፍርድ ቤት (ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች አወቃቀር አንጻር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል) ነው። ለአካለ መጠን ያልደረሰውን ወንጀል አድራጊ ለፍርድ ቤቱ ሊያቀርቡ የሚችሉትን በሚመለከት ፖሊስ፣ ዐቃቤ ሕግ፣ ወላጆቹ ወይም ሞግዚቱ ሊሆን እንደሚችል የተመለከተ ሲሆን ጉዳዩ የቀረበለት የወረዳ ፍርድ ቤትም መፈፀም ያለባቸውን እንደ ክሱን የመመዝገብና የፖሊስ ምርምራ ሂደቱን እንደ መቆጣጠር ዓይነት ሥራዎችን ካከናወነ በኋላ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ያለው ከሆነ እዚያው ጉዳዩን ማየት

ይቀጥላል፤ የወንጀል ክሱን የመስማት ሥልጣን ከሌለው ግን ሥልጣኑ ወዳለው ፍርድ ቤት ያስተላልፈዋል፡፡

ወጣቱ ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ ቤተሰብ ካልቀረበ እንዲጠራ ፍርድ ቤቱ ማድረግ ያለበት ሲሆን ተጠርቶ ቤተሰብ ባልቀረበ ጊዜ እንዲሁም ወጣቱ የተከሰሰበት ጉዳይ በሞት ወይም ከአስር ዓመት በላይ በሆነ የፅኑ እስራት ቅጣት በሚያስከትል ወንጀል የሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጠበቃ ለአካለ መጠን ላልደረሰው ወጣት ተከሳሽ እንዲቆምለት ማድረግ ይኖርበታል (ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.174)፡፡

ለአካለ መጠን ያልደረሰው ወጣት ተይዞ ከቀረበለት በኋላ በወጣቱ ላይ የቀረበውን ክስ ወይም የክስ አቤቱታ የሚመዘግበውና ተገቢ መስሎ የታየውንም ማናቸውንም ምርመራ ፖሊስ እንዲያደርግ የሚመራው ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ካልፈቀደ በስተቀር የተከሳሹን ተይዞ መቆየት የሚመለከቱ እንደ አስገዳጅ የሕክምና ምርመራና ቃልን መቀበል ያሉ የምርመራ እርምጃዎችን በራሳቸው ሥልጣን ፖሊሶች ሊወስዱ አይችሉም፡፡ ምክንያቱም ከወረዳው ፍርድ ቤት አስቀድሞ ፈቃድ ሳያገኙ ይህን መሰል እርምጃ መውሰድ የሚችሉ ከሆነ ለአካለ መጠን ባልደረሱ ወጣቶች ላይ የሚፈፀም የፖሊሶችን የመያዝ ተግባር ለማስወገድ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 172ትን ጠቃሚ ዓላማ ዋጋ እንዳይኖረው የሚያደርግ ስለሚሆን ነው፡፡[33] ስለሆነም ፖሊስ አካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ ከያዘ ወድያውኑ ፍርድ ቤት ማቅረብ ያለበት ሲሆን ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሕጉ በፖሊስ ምርመራው ላይ ሙሉ ሥልጣን ለፍርድ ቤቱ ይሰጠዋል፡፡ ወጣቱ ተመልሶ ለፖሊስ ተላልፎ አይሰጥም፡፡ ከዚያ ይልቅ ጉዳዩ ቀጠሮ መስጠትን የሚጠይቅ ወይም ወደ የበላይ ፍርድ ቤት መቅረብ የሚገባው ሆኖ ፍርድ ቤቱ ሲያገኘው ጉዳዩ በሚሰማበት ጊዜ ለሚያቀርቡ ለወጣቱ ወላጆች፣ ለዘመድ ወይም ለሞግዚቱ ወ.ዘ.ተ. ለአከላ መጠን ያልደረሰው ወጣት ተላልፎ እንዲሰጥ ሕጉ ያዛል፡፡[34] ይህም የሚሆንበት ምክንያት ለአካለ መጠን ያልደረሱ ወጣቶች ጉዳያቸው ታይቶ ውሳኔ

[33] ስታንሊ ዜድ ፊሸር "በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት በወጣት ጥፋተኞች ላይ" የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት7፡1 ገጽ 64-5

[34] የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ቁጥር 172(4)፣

ከመሰጠቱ በፊት ታስረው እንዳይቆዩ በማድረግ ሕጉ ወጣት ጥፋተኞችን ወደ መልካም ሰውነት ለመመለስ ያለውን ዓላማ የሚጻረር ሁኔታ እንዳይፈጠር ለማስቻል ነው፡፡

መደበኛ በሆኑ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ለመክሰስ ወይም ላለመክሰስ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ዐቃቤ ሕግ ነው፡፡ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ሰዎችን አስመልክቶ በሚቀርቡ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ግን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 173 ላይ እንደተመለከተው ጉዳዩ ከአስር ዓመት በላይ በሆነ ፅኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ በሚሆንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ዐቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻውን አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ ያዛል በማለት የሚደነግግ ሲሆን ይህ አቀራረብ በሌሎች ጉዳዮች ላይ ግን አስቀድሞ ለፍርድ ቤቱ የሚቀርበው ክስ ወይም አቤቱታ እንደ ክስ ማመልከቻ ሆኖ እንደሚያገለግልና መደበኛ በሆነው ዓይነት መልኩ የክስ ማመልከቻ በዐቃቤ ሕግ በኩል ተዘጋጅቶ መቅረብ የሚያስፈልግ አለመሆኑን የሚያመላክት ከመሆኑም ባሻገር በሥነ ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 108 ላይ ለአካለ መጠን ባልደረሱ ወጣቶች ላይ የሚቀርበው ክስ በመደበኛው የክስ ማመልከቻ አቀራረብ ሥርዓት እንደማይሸፍን ከተመለከተው አንጻርም በወጣቱ ላይ ክስ ሊቀርብ ይገባ ወይም አይገባ እንደሆነ መወሰን የሚችለው ፍርድ ቤት ስለመሆኑ መገመት የሚያስችል ነው፡፡

ፍርድ ቤት ነገሩን ሁሉ የሚሰማው በዝግ ችሎት ስለመሆኑ በሥነ ሥርዓት ሕጉ ተመልክቷል፡፡[35] ነገሩ በሚሰማት ጊዜ እንዲገኙ የሚፈቀድላቸው ሰዎች ወላጆች፣ ምስክሮች፣ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ሞግዚት ወይም የበጎ አድራጎት አባል (ምናልባት ልጁ የሕጻናት ማሳደጊያ ድርጅቶች ውስጥ ይኖር ከነበረ) ብቻ ናቸው፡፡ ለአካለ መጠን ባልደረሱ ወጣቶች ላይ የሚቀርበው ክስ በዝግ ችሎት እንዲሰማ ሕጉ የሚያዝበት ምክንያት የጉዳዩ መሰማት ምስጢር ሆኖ እንዲጠበቅ ለማድረግ ይመስላል፡፡ ለአካለ መጠን ያልደረሰው ወጣት በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝም ባይገኝም የነገሩ መሰማት በተቻለ መጠን በምስጢር የሆነ እንደሆነ ተከሳሹ ወደ ህብረተሰቡ ሲመለስ በቀላሉ ሊዋሀድ ይችላል፡፡

[35] የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ቁጥር 176(1)፣

በምስክሮች አመሰካከር ዙሪያ በመጀመሪያ በጥያቄ የሚመረምረው ፍርድ ቤቱ ራሱ ሲሆን የተከሳሹ ወገን የመስቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ መብት የሚኖረው ፍርድ ቤቱ ጥቄዎችን ካቀረበ በኋላ ነው (ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.176(6))፡፡ በወጣቱ ላይ የቀረበውን ክስ ለመደገፍ ወይም ለመቃወም የተጠሩ ምስክሮች ሁሉ ለአካለ መጠን ባልደረሱ ወንጀል አድራጊዎች ላይ በሚቀርቡ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ቀርበው የሚመሰክሩ ምስክሮች የፍርድ ቤቱ ምስክሮች ተደርገው የሚቆጠሩ ይመስላል፡፡ በዚህም ምክንያት በተከሳሹ ወገን ተጠርተው የቀረቡትን ምስክሮች ጭምር ፍርድ ቤቱ በጥያቄ የሚመረምር ሲሆን ራሱ እንዲጠሩ ያደረጋቸውን ምስክሮች የተከሳሹ ወገን ራሱ መስቀለኛ ጥያቄ ለመጠየቅ የሚችልበትን ሁኔታ ይመለከታል፡፡[36] በዚህም መሰረት ሁሉንም ምስክሮች ፍርድ ቤቱ ከመረመራቸው በኋላ የተከሳሹ ወገን መስቀለኛ ጥያቄ ካለው ይጠይቃል እንጂ መደበኛ እንደሆነው የአዋቂ አጥፊዎች የክስ መስማት ሥነ ሥርዓት ሂደት ዋና ጥያቄ፣ መስቀለኛ ጥያቄ፣ ድጋሚ ጥያቄ እና የፍርድ ቤት የማጣሪያ ጥያቄ የሚባሉ ምስክሮች የሚጠየቁበት ደረጃ የለም፡፡

ለአካለ መጠን ባልደረሱ ወጣቶች ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው መሰረታዊው የወንጀል ሕግ እንደሚያስቀምጠው ፍርድ ቤት ከፍርድ በኋላ በማናቸውም ጊዜ የወጣቱን ጥቅም ግምት ውስጥ በማስገባት አስቀድሞ በአጥፊው ላይ የተሰጠውን የጥንቃቄ እርምጃ ወይም የቅጣት ውሳኔ አፈጻጸም መለዋወጥ ይችላል(አንቀጽ 55 እና 164)፡፡ይህን ሥልጣኑን መሰረት በማድረግም ፍርድ ቤቱ የእስራት ጊዜን ማሳጠር ወይም ማስረዘም፣ ወጣቱን ከአንድ ጠባይ ማረሚያ ተቋም ወደ በእስራት እንዲቀጣ ወደ ማረሚያ ቤት መላክ የመሳሰሉትን ማድረግ ይችላል፡፡

[36] ስታንሊ ዜድ ፊሸር “በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት በወጣት ጥፋተኞች ላይ” የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት7፡1 ገጽ 84

10. ትኩረት የሚሹ አንዳንድ የወንጀል ጉዳዮች

10.1. ስለ ሙስና ወንጀሎች አንዳንድ ነጥቦች

የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 "የሙስና ወንጀል " ማለት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ የተመለከቱት የሙስና ወንጀሎች ናቸው በማለት በአዋጁ ውስጥ ትርጓሜዎችን ባስቀመጠው አንቀጽ ስር የደነገገ ሲሆን በወንጀል ሕጉ ውስጥ የሙስና ወንጀል ምን ማለት እንደሆነ በመተርጎም ደረጃ የተቀመጠበት ቦታ የለም፡፡

በሕግ ሙያ ዙሪያ የምንጠቀምባቸውን ቃላት እና ሀረጎች ወይም ፅንሰ ሀሳቦች ለመተርጎም ብዙ ጊዜ የምንጠቀምበት ብላክስ ሎው የሕግ መዝገበ ቃላት ሙስና /corruption/ የሚለውን ቃል እንደሚከተለው ተርጉሞታል

> corruption is "the act of doing something with an intent to give some advantage inconsistent with official duty and the rights of others; a fiduciary's or official's use of a station or office to procure some benefit either personally or for someone else, contrary to the rights of others."[37]

በግርድፉ በአማርኛ ሲተረጎምም ጥቅም በመፈለግ ከሥልጣን ኃላፊነት ውጭ በሆነ ሁኔታ አንዱን ለመጥቀምና የሌላውን መብት ለመጉዳት የሚደረግ ተግባር፣ ለራስ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት ሲባል የያዘውን ሥልጣንና ኃላፊነት ሕገ ወጥና ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ የመጠቀም ወይም ከሥራ ኃላፊነት ውጭ በመሥራት የሌሎች ሰዎችን መብት መንካት ሙስና ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

እንዲሁም በተሻረው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/93 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ ለሙስና ወንጀል ቀጥሎ በተመለከተው መልኩ ትርጉም ተሰጥቶት ነበር፡፡

[37] Black's Law Dictionary; 8th ed., 2004;p.371

“የሙስና ወንጀል ማለት ከመንግሥት ወይም ከሕዝብ አገልግሎት ወይም ከሕዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ የሚፈፀም ማናቸውም ወንጀል ሆኖ የተመደበበትን የመንግሥት ወይም የሕዝብ አገልግሎት ሥራ ያለአግባብ በመጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰው ወይም ለቡድን ጥቅም መጠየቅ፣ የተስፋ ቃል መቀበል ወይም ማግኘት ወይም ሌላውን ሰው መጉዳት ሲሆን መደለያ መቀበልን፣ ጉቦን፣ የማይገባ ጥቅም መቀበልን፣ በሥልጣን መነገድን፣ በሥልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣ የመንግሥት ሥራን ወይም የሕዝብ አገልግሎት ሥራን ለግል ጥቅም በሚያመች አኳኋን መምራትን፣ በሥራ ተግባር ላይ የሚፈፀም መውሰድና መሠወርን፣ በመንግሥት ሥራ ላይ ሆኖ በማስገደድ መጠቀምን እና ምስጢር ማባከንን እና የመሳሰሉትን ሌሎች ጉዳዮችን ይጨምራል።”

አዋጅ ቁጥር 236//93ትን በሻረው አዋጅ ቁጥር 434/97ትም ሆነ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ ላይ የሙስና ወንጀል ማለት ምን ማለት እንደሆነ አንድ ትርጉም ባያስቀምጡም የወንጀል ሕጉ የሙስና ወንጀሎች ተብለው የሚቆጠሩትን ወንጀል የሚያቋቋሙ ድንጋጌዎች በአንድ ክፍል ስር በመደንገግ “ቅንነትንና ታማኝነትን በማጓደል የመንግሥት ሠራተኞች የሚፈፅሟቸው የሙስና ወንጀሎች” በማለት አስቀምጧል። በተጠቀሰው ክፍል ስር በሕጉ ልዩ ክፍል የተመለከቱትን ወንጀል የሚያቋቋሙ ድንጋጌዎች በመተላለፍ አንድ ሰው የወንጀል ድርጊት ከፈፀመ የሙስና ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ የሚወሰድ ሲሆን በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የተፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶችን ለመመርመር እና/ወይም ለመክሰስ ሥልጣን ያለው አካልም (በፌዴራል ደረጃ ከሆነ) በፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 235/93 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ነው።

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው በኢትዮጵያ ሕግ የሙስና ወንጀሎች ናቸው ተብለው የተወሰዱት የወንጀል ድርጊቶች በወንጀል ሕጉ በአንድ የተለዩ ክፍል ውስጥ ተጠቃለው የሚገኙ ሲሆን በወንጀል ሕጉ ከአንቀጽ 407 እስከ አንቀጽ 419 ያሉትን ድንጋጌዎችን

ያካትታል። እነዚህም የሙስና ወንጀሎች በሥልጣን ያለ አግባብ መገልገል፣ ጉቦ መቀበል፣ የማይገባ ጥቅም መቀበል፣ የመንግሥት ሥራን በማያመች አኳኋን መምራት፣ አደራ በተሰጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ፣ በሥራ ተግባር ላይ የሚፈፀም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል፣ በሥልጣን መነገድ፣ በሕገወጥ መንገድ መሰብሰብ ወይም ማስረከብ፣ ያለ አግባብ ጉዳይን ማጓተት፣ ዋጋ ያለውን ነገር ያለ ክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት፣ ያለ አግባብ ፈቃድ መስጠት እና ማፅደቅ፣ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ በእጁ ይዞ መገኘት ወይም ኑሮውን በዚሁ ዓይነት ባልታወቀ ገቢ መምራት ናቸው።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ዓይነቶች የሙስና ወንጀሎች ሊፈፀሙ የሚችሉት በመንግሥት ሠራተኞች አማካኝነት ሲሆን "የመንግሥት ሠራተኛ" ማለት ደግሞ በመንግሥት መስሪያ ቤት ወይም በመንግሥት ልማት ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ፣ ተሹሞ፣ ተመድቦ፣ ወይም በሕዝብ ተመርጦ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ሥራን የሚያከናውን ማንኛውንም ሰው የሚመለከት ስለመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 402(2) ላይ ተመልክቷል።

በመሆኑም በመርህ ደረጃ የሙስና ወንጀሎች የሚመለከቷቸው የመንግሥት ሠራተኞችን ነው። ነገር ግን ስለ ወንጀሎችና ወንጀል አድራጊዎች በማስመልከት በሚደነግገው በወንጀል ሕጉ ጠቅላላው ክፍል ውስጥ አንቀጽ 33 ላይ እንደተመለከተው አንዳንድ ወንጀሎች በጠባያቸው የተነሳ በሁሉም ሰዎች የማይፈፀሙ ዓይነት ተደርገው ሊወሰዱ የሚችሉ ቢሆንም እንዲሁም አንድ ሰው እነዚህን የተለዩ ጠባይ ያላቸውን ወንጀሎች ለመፈፀም የሚያስችለው ሁኔታ ባይኖረውም በመላ አሳቡና ድርጊቱ እነዚህን ወንጀሎች ለመፈፀም የተለዩ ሁኔታ ካላቸው ሰው ጋር ከተባበረ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተጠያቂ ሊሆን ይችላል። በመሆኑም የመንግሥት ሠራተኛ ያልሆነ ሰውም በእነዚህ ወንጀሎች ውስጥ ተካፋይ ከሆነ በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን የሚችልበት ይኖራል ማለት ነው።

ከሙስና ወንጀሎች ጋር በተያያዘ ሌላው ሳይነሳ መታለፍ የሌለበት ነጥብ ማንም ሰው በሙስና ወንጀል ተካፋይ ከሆነ በኋላ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ስለተፈፀመው ድርጊትና ስለተካፋዮች ሚና ጠቃሚ መረጃ ከሰጠ ከክስ ነጻ ሊሆን

እንዲችል የወንጀል ሕጉ የፈቀደ መሆኑ ነው።[38] በተመሳሳይም የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 43 ላይ በሙስና ወንጀል ተሳታፊ የሆነ ሰው ከክስ ነጻ ስለሚደረግበት ሁኔታ የተመለከተ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ ላይ እንደተመለከተው እንዲህ ዓይነት ከክስ ነጻ የማድረግ ውሳኔ የሚሰጠው በፌዴራል የስነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ወይም አግባብ ባለው አካል የበላይ ኃላፊ አማካኝነት ነው።

እንዲህ ዓይነት አሰራር ለምን ተፈቀደ የሚለውን በምናይበት ጊዜ በመሰረቱ ሙስና በባህሪው (በተለይም ግራንድ ኮራብሽን የሚባለው) በትምህርትና በሙያ የተለዩ ችሎታና ዕውቀት ባላቸው፣ መንግሥታዊ ሥልጣን በያዙ፣ በሥልጣናቸው ተዕዕኖ ሊያደርጉ በሚችሉ ሰዎች የሚፈፀም ድብቅ ተግባር ነው። በዚህ ወንጀል ተካፋይ የሆኑ ሰዎች ራሳቸው ማስረጃ እንዲሰጡ በማድረግ ሌሎችን ተጠያቂ ከማድረግ ውጭ አንዳንድ ጊዜ ምንም ዓይነት ማስረጃ ማግኘት አይቻልም ወይም ቢያንስ እጅግ በጣም አስቸጋሪ ነው። በመሆኑም ተጨባጭ የሆኑ ለጉዳዩ ጠቀሜታ ያላቸው ማስረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ሰዎችን ከክስ ነጻ እንዲሆኑ በማድረግ ሙስና በፈፀሙ ሌሎች ሰዎች ላይ ተገቢው ቅጣት እንዲጣል ማድረግ ጠቀሜታው የሰፋ ነው። ስለዚህም በተፈፀመው ሙስና የሚጠየቅ ሳይኖር ከሚቀር አንድ ሰው ነጻ ተደርጎ እርሱ በሚሰጠው ጠቃሚ መረጃ በመንተራስ ሌሎች እንዲጠየቁ ማድረግ የተሻለ ነው ተብሎ በሕጋችን ውስጥ እንዲካተት የተደረገ ይመስላል።

10.2. ስለ አስገድዶ መድፈር ወንጀል አንዳንድ ነጥቦች

በአዲሱ የወንጀል ሕግ የአስገድዶ መድፈር ወንጀልን ጨምሮ ሌሎች በግብረ ሥጋ ነፃነትና ንፅህና ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች የተደነገገው ከአንቀጽ 620 ጀምሮ እስከ አንቀጽ 628 ባሉት ድንጋጌዎች ሲሆን የአንቀጽ 620 ንዑስ ቁጥር 1 ድንጋጌ "ማንም ሰው የኃይል ድርጊት በመጠቀም ወይም በብርቱ ዛቻ ወይም ሕሊናዋን እንድትስት ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ መከላከል እንዳትችል በማድረግ ከጋብቻ ውጪ አስገድዶ ከአንዲት ሴት ጋር

[38] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 406፣

የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈፀመ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት ይቀጣል" ይላል፡፡

ከላይ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሠረት የአስገድዶ መድፈር ተግባር ተፈፅሟል ለማለት፡-

1. ተጠቂዋ ሴት መሆን አለባት፣ (አንዲት ሴት ወንድን አስገድዳ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከእርሷ ጋር እንዲፈፀም ያደረገች እንደሆነ በወንጀል የምትጠየቅ ሲሆን እንዲህ ዓይነት የወንጀል ድርጊት የሚሸፈነው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 621 ነው)፡፡

2. በማናቸውም መንገድ የሚደርስባትን ጥቃት መከላከል እንዳትችል የተደረገች መሆን አለባት፡፡ ማለትም በሴቷ ላይ ድርጊቱ የተፈፀመው ኃይልና ዛቻን በመጠቀም፣ ወይም ሕሊናዋን በማሳት እና በመሳሰለው መንገድ የመከላከል አቅሟን በማሳጣት ተደግፎ መሆን አለበት፡፡

4. የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም አለበት (ወይም ቢያንስ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈፀም መሞከር ይኖርበታል)፣

5. ድርጊቱ የተፈፀመው የጋብቻ ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል መሆን አለበት፡፡ በዚህም መሠረት የአስገድዶ መድፈር ወንጀል በጋብቻ ተሳስረው የሚገኙ ሰዎችን አይመለከትም ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 621 መሠረት አንዲት ሴት ወንድን አስገድዳ ከእርሷ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲፈፅም ያደረገች እንደሆነ በወንጀል የምትጠየቅ ቢሆንም ሕጉ ይህን የወንጀል ድርጊት "አስገድዶ የመድፈር" (rape) በሚለው ሀረግ (ቃል) አይጠራውም፡፡

አዲሱ የወንጀል ሕግ አስገድዶ መድፈርን በተመለከተ ያስቀመጣቸው ድንጋጌዎች ከቀድሞው የሚለዩባቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህ መሠረታዊ የሆኑ ልዩነቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ለመደበኛው የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ተቀምጦ የነበረውን እስከ አሥር ዓመት የሚደርስ የፅኑ እስራት ቅጣት መነሻውን ከአምስት ዓመት እንዳያንስ ያደረገው ሲሆን የቅጣቱን ጣራ ደግሞ ወደ አሥራ አምስት ዓመት ከፍ አድርጐታል፡፡ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ሲኖር ደግሞ በቀድሞው ሕግ እስከ አስራ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት ብቻ ያስቀጣ የነበረው በአዲሱ የወንጀል ሕግ መሠረት ወደ ሀያ ዓመት ፅኑ እስራት ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡

- በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ዕድሜዋ ከ15 ዓመት እስከ 18 ዓመት በሆነ ሴት ላይ የተፈፀመ አስገድዶ መድፈር የሚያስቀጣው በመደበኛው የአስገድዶ መድፈር ድንጋጌ መሠረት የነበረ ሲሆን (እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ የፅኑ እሥራት ብቻ ነበር የሚያስቀጣው) በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620(2) መሠረት ዕድሜዋ አስራ ሦስት ዓመት ሆኖ አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላት ሴት ልጅ ላይ የሚፈፀመው የአስገድዶ መድፈር ወንጀል የሚያስቀጣው ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት ነው፡፡

- አስገድዶ የመድፈር ድርጊት ከባድ የአካል ጉዳትን ወይም ሞትን ያስከተለ እንደሆነ ወንጀለኛው በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት እንደሚቀጣና ከአስገድዶ መድፈር ወንጀሉ ጋር ተያይዞ የመጥለፍ ተግባር ወይም በሽታ የማስተላለፍ ተግባር ሲፈፀም ስለተደራራቢ ወንጀሎች በተደነገጉት አንቀፆች መሠረት ቅጣት በወንጀለኛው ላይ እንደሚፈፀምበት በማስቀመጥ በቀድሞው ሕግ ያልነበሩ ድንጋጌዎችን አዲሱ የወንጀል ሕግ ጨምሯል፡፡

ከዚህ በላይ በተመለከቱት ሁኔታዎች አዲሱ የወንጀል ሕግ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ሲፈፀም የሚጣለውን የቅጣት ወለልም ሆነ ጣራውን ከፍ ያደረገ ሲሆን አንዲት ሴት ለአካለ መጠን ወይም ለጋብቻ የምትደርስበትን ዕድሜ (18 ዓመት) ጠብቆ ከዚህ ዕድሜ በታች ላይ የምትገኝን ሴት ልጅ አስገድዶ መድፈር ከፍ ባለ ቅጣት የሚያስቀጣ እንዲሆን አድርጓል፡፡